# ትንቢተ ዳንኤል

## መግቢያ

### ጸሐፊው፣ የተጻፈበት የመጽሐፉ እውነተኛነት

ጸሐፊው ዳንኤል እንደ ሆነ መጽሐፉ ራሱ ብዙ ቦታ ላይ ይገልጻል፤ ለምሳሌ ያህል 9፥2 እና 10፥2 ላይ ተጠቅሶ እናያለን:: ጌታ ኢየሱስ በዚህ ነጥብ የሚስማማ መሆኑን፣ "እንግዲህ በነቢዩ በዳንኤል የተባለውን 'የጥፋት ርኵሰት'..." በማለቱ ከ9፥27፤ ከ11፥31፤ ከ12፥11 ላይ መጥቀሱን እንረዳለን (ማቴ 24፥15):: መጽሐፉ ተጽፎ ያለቀው ቂሮስ በ539 ዓ.ቅ.ክ. ባቢሎንን ከማረከ በኋላ ብዙም ሳይቈይ በ530 ዓ.ቅ.ክ. ገደማ ሳይሆን አይቀርም::

የትንቢተ ዳንኤል አብዛኛው ክፍል ልብ ወለድ መጽሐፍ ነው የሚሉ አሉ፤ ይኸውም ጊዜው ይህን ያህል ሰፊ ዘመን ባካተተ ጉዳይ ላይ ትንቢት መናገር አይቻልም ከሚል አጉል ዘመናዊ ፍልስፍና የመጣ ስሕተት ነው:: ስለዚህ በዳንኤል ትንቢት መሠረት ስለ ተፈጸሙ ሁኔታዎች ሁሉ የተጻፈው ከመቃብያን ዘመን (ከሁለተኛው ምእተ ዓ.ቅ.ክ.) ቀደም ሲል መሆን አይችልም ይላሉ፤ ይህም ማለት ደግሞ መጽሐፉ የተጻፈው ተነገረ የተባለው ትንቢት መፈጸም ከጀመረ በኋላ ነው ማለት ነው:: ነገር ግን ተጨባጩ ማስረጃ ይህን መሠረት የለሽ ግንዛቤ በብዙ መንገድ ይሽረዋል:- (1) ትንቢተ ዳንኤል የተጻፈው በኋለኛው ዘመን እንደ ሆነ የሚያምኑት በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሰውን ይህን ያህል ሰፊ ዘመን ያካተተውን ትንቢት ፍጻሜ ለማስወገድ በም 2 እና 7 ላይ የተጠቀሱትን አራቱን መንግሥታት ማለት የባቢሎን፣ የሜዶን የፋርስና የግሪክ መንግሥታት እንደ ሆኑ ይናገራሉ:: ነገር ግን በጸሐፊው አመለካከት "ሜዶንና ፋርስ" በጥምር (5፥28) በአራቱ መንግሥታት ዝርዝር ውስጥ (2፥36-43) እንደ ሁለተኛ መንግሥታት የሚታዩ ናቸው:: ስለዚህ አራቱ መንግሥት የባቢሎን፣ የሜዶን-ፋርስ፣ የግሪክና የሮም መንግሥታት መሆናቸው ግልጽ ነው::

(2) የጽሑፉ የቋንቋ አጠቃቀም ራሱ መጽሐፉ ከሁለተኛው (ምእተ ዓ.ቅ.ክ.) ቀደም ብሎ እንደ ተጻፈ የሚያመለክት ነው:: በሁለተኛው ምእተ ዓ.ቅ.ክ. ላይ የነበረው የዕብራይስጥና የአረማይክ ቋንቋ ምን ቅርጽና ይዘት እንደ ነበረው ከሙት ባሕር ከተገኙት የብራና ጥቅልል ጽሑፎች ከብዙ በጥቂቱ መረዳት ይቻላል፤ በመሆኑም በትንቢተ ዳንኤል ላይ የሚገኙት በዕብራይስጥና በአረማይክ ቋንቋ የተጻፉት ምዕራፎች ከሁለተኛው ምእተ ዓ.ቅ.ክ. ዓመታት ቀደም ብለው እንደ ተጻፉ ከዚህ ጋር በማነጻጸር መገንዘብ ይቻላል:: ከዚህም በላይ በትንቢተ ዳንኤል ውስጥ የሚገኙት የፋርስና የግሪክ ቃላት የቅርብ ጊዜ ቋንቋ ሊሆኑ አይችሉም:: በምዕራፍ ሦስት ላይ የሚገኙት አንዳንድ ቃላት በሁለተኛው ምዕተ ዓ.ቅ.ክ ቀድሞውኑ ከጥቅም ውጭ ሆነው ስለነበር፣ ሰብዓ ሊቃናት ብሉይ ኪዳንን ወደ ግሪክ ቋንቋ በተረጐሙበት ጊዜ በዚህ ረገድ ተሳስተዋል::

(3) በዳንኤል ከተነገሩት ትንቢቶች ብዙዎቹ በሁለተኛው ምእተ ዓ.ቅ.ክ. ላይ አልተፈጸሙም በማለት ብቻ ትንቢትነቱን መሻር አይቻልም:: የአራተኛው መንግሥት ምሳሌ ሆኖ የቀረበው ምልክት ስለ ሮም መንግሥት አስቀድሞ የተነገረ መሆኑ ከቶ አያጠራጥርምና (2፥33፤ 7፥7፡9 ይመ)፤ የሮም መንግሥት እስከ 63 ዓ.ቅ.ክ. ድረስ ሶርያንና መካከለኛውን ምሥራቅ አልተቈጣጠረም:: ስለ "መሲሑ ገዥ" የተነገረው ትንቢትም "ኢየሩሳሌምን ለመጠገንና ለመሥራት ትእዛዝ ከወጣ" (9፥25)፣ ከአራት መቶ ሰማንያ ሦስት ዓመት በኋላ፣ ከጌታ ኢየሱስ የአገልግሎት ዘመን ጋር በትክክል ይገጥማል::

ስለዚህ መጽሐፉ የተጻፈው ወደ ኋለኛው ዘመን ላይ ነው የሚለውን ግምት ተጨባጩ ማስረጃ ይሽረዋል፤ መጽሐፉን የጻፈው ዳንኤል አይደለም የሚለውንም አባባል ያለ በቂ ምክንያት የተሰነዘረ ያደርገዋል::

### የመጽሐፉ መሪ ሐሳብ

የመጽሐፉ ትምህርተ መለኮታዊ መሪ ሐሳብ "የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት" ነው፤ "ልዑል አምላክ በሰዎች መንግሥት ላይ ሥልጣን እንዳለው..." (5፥21) ይገልጣል:: ለዳንኤል የተገለጡ ራእዮች ምን ጊዜም የእግዚአብሔርን አሸናፊነት የሚያሳዩ ናቸው (7፥11፡26-27፤ 8፥25፤ 9፥27፤ 11፥45፤ 12፥13):: ሉዓላዊነቱ ከሁሉ በላይ ጐልቶ የተገለጠው በዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ውስጥ ነው፤ "የዓለም መንግሥት ለጌታችንና ለክርስቶስ ሆነች፤ ለዘላለም እስከ ዘላለም ይነግሣል" (ራእ 11፥15 እና ዳን 2፥44፤ 7፥27 ያነጻጽሩ)::

### የሥነ ጽሑፉ ገጽታ

በመሠረቱ ይህ መጽሐፍ ታሪክ ነክና (በአብዛኛው ም 1-6 ላይ የሚገኝ) ራእይ ነክ (በአብዛኛው ም7-12 ላይ የሚገኝ) አጻጻፍ ይዟል:: ራእይ ነክ የተባለው ክፍል ትእምርታት፣ የመገለጥ ራእይና ትንቢታዊ ሥነ ጽሑፍ የሞላበት ሲሆን፣ በአስጨናቂ ወቅት የተጻፈና በትምህርተ መለኮት ይዘቱ አብዛኛው ስለ ዘመናት ፍጻሜ የሚተርክ ነው:: ራእይ ነክ ጽሑፍ በመሠረቱ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚያበረታታ ነው (በትንቢተ ዘካርያስ መግቢያ ውስጥ፣ 'የሥነ ጽሑፍ ገጽታ' የሚለውን ርእስ ይመ፤ በተጨማሪም በዮሐንስ ራእይ መግቢያ፣ 'የሥነ ጽሑፍ ገጽታ' የሚለውን ርእስ ይመ):: በራእይ ነክ ጽሑፍ ውስጥ ስለ ቍጥሮች ትእምርታዊ (አመልካችነት) አጠቃቀም በዮሐንስ ራእይ መግቢያ፣ "ልዩ ገጽታ"

በሚለው ርእስ ሥር የተጻፈውን ይመ::

**አስተዋጽኦ**

1. መግቢያ፤ መቼት (ም 1፤ በዕብራይስጥ)
    - ሀ. ታሪካዊ መግቢያ (1፥1-2)
    - ለ. ዳንኤልና ባልንጀሮቹ ተማርከው ሄዱ (1፥3-7)
    - ሐ. ወጣቶቹ በእምነታቸው ጸንተው ተገኙ (1፥8-16)
    - መ. ወጣቶቹ ለከፍተኛ ሥልጣን በቁ (1፥17-21)
2. የዓለም መንግሥታት ዕጣ ፈንታ (ም 2-7፤ በአራማይክ ቋንቋ ከ2፥4 አጋማሽ ጀምሮ)
    - ሀ. ናቡከደነፆር በሕልሙ ያየው ምስል (ም 2)
    - ለ. ናቡከደነፆር የወርቅ ምስል ማሠራቱና እንዲመለክ ማዘዙ (ም 3)
    - ሐ. ናቡከደነፆር በሕልሙ አንድ ግዙፍ ዛፍ አየ (ም 4)
    - መ. የንጉሥ ብልጣሶርና የባቢሎን ውድቀት ተገለጠ (ም 5)
    - ሠ. እግዚአብሔር ዳንኤልን ከአንበሶች አፍ አዳነው (ም 6)
    - ረ. ዳንኤል በሕልሙ አራት አውሬዎችን አየ (ም 7)
3. የእስራኤል መንግሥት ዕጣ ፈንታ (ም 8-12፤ በዕብራይስጥ ቋንቋ)
    - ሀ. ዳንኤል በራእዩ ያያቸው አንድ አውራ በግና አንድ አውራ ፍየል (ም 8)
    - ለ. የዳንኤል ጸሎትና በራእዩ ያያቸው ሰባ "ሳምንቶች" ራእይ (ም 9)
    - ሐ. ዳንኤል ስለ እስራኤል የወደፊት ሁኔታ ያየው ራእይ (ም 10-12)
        - (1) ወደ ፊት ስለሚሆኑ ነገሮች ያየው ራእይ (10፥1-3)
        - (2) በመልአኩ በኩል የተቀበለው ራእይ (10፥4-11፥1)
        - (3) ስለ ፋርስና ስለ ግሪክ የተነገሩ ትንቢቶች (11፥2-4)
        - (4) ስለ ግብፅና ስለ ሶርያ የተነገሩ ትንቢቶች (11፥5-35)
        - (5) ስለ ሐሰተኛው ክርስቶስ የተነገሩ ትንቢቶች (11፥36-45)
        - (6) መከራና ትድግና (12፥1)
        - (7) የሙታን ትንሣኤ (12፥2-3)
        - (8) ለዳንኤል የተሰጠ መመሪያ (12፥4)
        - (9) መደምደሚያ (12፥5-13)

## ዳንኤል በባቢሎን እንዲሠለጥን ተደረገ

1 የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአቄም በነገሠ በሦስተ
ኛው ዓመት የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደ
ነፆር ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ከበባት::
2ጌታም የይሁዳን ንጉሥ ኢዮአቄምን በእግዚ
አብሔር ቤተ መቅደስ ካሉት ዕቃዎች ከጥቂቶቹ
ጋር በእጁ አሳልፎ ሰጠው፤ ወደ አምላኩ
ቤት ወደ ባቢሎን[ሀ] ወሰዳቸው፤ በአምላኩም
ግምጃ ቤት ውስጥ አኖራቸው::
3ከዚያ በኋላ ንጉሡ የቤተ መንግሥቱን
ጃንደረቦች አለቃ አስፋኔዝን፣ ከንጉሣዊው
ቤተ ሰብና ከመሳፍንቱ ዘር የሆኑትን እስራ
ኤላውያንን እንዲያመጣ አዘዘው፤ 4እነርሱም
የአካል ጉዳት የሌለባቸው መልከ መልካሞች፣
ማንኛውንም ትምህርት የመማር ችሎታ ያላ
ቸው፣ ዕውቀት የሞላባቸው፣ ሁሉን ነገር
በፍጥነት መረዳት የሚችሉትንና በንጉሡም
ቤት ለማገልገል ብቃት ያላቸው ወጣት
ወንዶች ናቸው፤ የባቢሎናውያንንም[ለ] ቋንቋና
ሥነ ጽሑፍ እንዲያስተምራቸው አዘዘው:: 5ንጉ
ሡም በየዕለቱ የሚበሉትን ምግብና የሚጠጡ
ትን የወይን ጠጅ ከንጉሡ ማእድ ድርሻ እን
ዲሰጣቸው አደረገ፤ ለሦስት ዓመት ከሠለጠኑ
በኋላ በንጉሡ አገልግሎት ላይ የሚሰማሩ
ናቸው::
6ከነዚህም መካከል ከይሁዳ የመጡት ዳን
ኤል፣ አናንያ፣ ሚሳኤልና አዛርያ ነበሩ፤ 7የጃ
ንደረቦቹ አለቃም አዲስ ስም አወጣላቸው፤
ዳንኤልን ብልጣሶር፣ አናንያን ሲድራቅ፤ ሚሳ
ኤልን ሚሳቅ፣ አዛርያን አብድናጎ ብሎ ጠራ
ቸው::
8ዳንኤል ግን በንጉሡ ምግብና የወይን
ጠጅ እንዳይረክስ ወሰነ፤ በዚህ መንገድ ራሱን
እንዳያረክስም የጃንደረቦቹን አለቃ ፈቃድ ጠየ
ቀው:: 9እግዚአብሔርም ለዳንኤል በጃንደረቦቹ አለቃ
ፊት ሞገስንና መወደድን ሰጠው:: 10ሆኖም
የጃንደረቦቹ አለቃ ለዳንኤል፣ "መብሉንና መጠ
ጡን የመደበላችሁን ጌታዬን ንጉሡን እፈራ
ለሁ፤ በዕድሜ እንደ እናንተ ካሉ ወጣቶች
ይልቅ ከሲታችሁ ብትታዩ፣ በንጉሡ ዘንድ በራሴ
ላይ አደጋ ታስከትሉብኛላችሁ::" ብሎ ነገረው::
11ዳንኤልም የጃንደረቦቹን አለቃ በዳን
ኤል፣ በአናንያ፣ በሚሳኤልና በአዛርያስ ላይ
የሾመውን መጋቢ እንዲህ አለው፤ 12"እባ
ክህ አገልጋዮችህን ለዐሥር ቀን ያህል ፈት
ነን፤ ለመብል ከአትክልት፣ ለመጠጥም ከውሃ
በስተቀር ምንም አይሰጠን፣ 13ከዚያም የእ
ኛን መልክና የንጉሡን መብል የሚበሉትን
ወጣቶች መልክ አስተያይ፤ በአገልጋዮችህ
ላይ የወደድኸውን አድርግብን::" 14እርሱም በዚህ
ነገር ተስማማ፤ ለዐሥር ቀንም ፈተናቸው::
15ከዐሥር ቀን በኋላም የንጉሡን መብል
ከበሉት ከሌሎች ወጣቶች ይልቅ ጤናማ
ዎችና ሰውነታቸው የወፈረ ሆነው ተገኙ::
16ስለዚህ መጋቢው ምርጥ የሆነውን ምግብ
ቸውንና ሊጠጡት የሚገባውን የወይን ጠጅ
አስቀርቶ በምትኩ አትክልት ሰጣቸው::
17እግዚአብሔር ለእነዚህ አራት ወጣቶች
በማንኛውም ሥነ ጽሑፍና ትምህርት ዕውቀ
ትንና ማስተዋልን ሰጣቸው፣ ዳንኤልም ማንኛ
ውንም ራእይና ሕልም የመረዳት ችሎታ ነበረው::
18ወደ እርሱ እንዲመጡ ንጉሡ የወሰ
ነው ጊዜ ሲደርስ፣ የጃንደረቦቹ አለቃ ወደ
ናቡከደነፆር አቀረባቸው፤ 19ንጉሡም ባነጋገራ
ቸው ጊዜ ከመካከላቸው እንደ ዳንኤል፣ አና
ንያ፣ ሚሳኤልና አዛርያ ያለ ከቶ አልተገኘም፤
ስለዚህ በንጉሡ አገልግሎት ላይ ተሰማሩ::
20ንጉሡ በጠየቃቸው በማንኛውም የጥበብና
የማስተዋል ጉዳይ በመላ ግዛቱ ካሉት አስ
ማተኞችና ድግምተኞች ሁሉ ዐሥር እጅ

1፥1 2ነገ24፥1፤2ዜና 36፥6፤ኤር28፥14፤ 35፥11፤46፥2፤50፥1
1፥2 2ነገ24፥13፤2ዜና 36፥7፤ኤር27፥19-20፤ ዘካ5፥5-11
1፥3 2ነገ20፥18፤ 24፥15፤ኢሳ39፥7
1፥4 ቊ17፤ዘፍ3 9፥6፤ ዕዝ4፥7
1፥5 ቊ8፡10፡ 18፡19፤ አስ2፥5-6፡9
1፥6 ሕዝ14፥14፤ ዳን 2፥17፡25
1፥7 ኢሳ39፥7፤ ዳን 2፥26፡49፤ 3፥12፤4፥8፤5፥12፤10፥1
1፥8 ሕዝ4፥13-14
1፥9 ዘፍ39፥21፤ 1ነገ8፥50፤ ምሳ16፥7
1፥10 ቊ5
1፥12 ራእ2፥10
1፥13 ቊ16
1፥14 ራእ2፥10
1፥15 ዘፀ23፥25
1፥16 ቊ12-13
1፥17 ኢዮ12፥13፤ ዳን2፥19፡23፡30፤5፥1 1፤7፥1፤8፥1፤ቈላ1፥9፤ ያዕ1፥5
1፥18 ቊ5
1፥19 ዘፍ41፥46
1፥20 ዘፍ41፥8፤1ነገ 4፥30፤አስ2፥15፤ሕዝ 28፥3፤ዳን2፥13፡28፤ 4፥18፤6፥3

ሀ2 ዕብራይስጡ *ሺናር* ይላል
ለ4 ወይም *ከለዳውያን*

1፥1 *በሦስተኛው ዓመት፤* ኢዮአቄም በ608 ዓ.ቅ.ክ የነገሠበት የመጀመሪያው ዓመት የዋለው በአዲሱ ዓመት መጀመሪያ ላይ ነበር፤ በባቢሎናውያን የንግሥና ዘመን አቈጣጠር መሠረት የኢዮአቄም ሦስተኛው ዓመት የዋለው በ605 ዓ.ቅ.ክ ነው:: የንግሥና ዘመን ራሱ እንደ መጀመሪያ ዓመት በሚቈጠርበት በአይሁድ የአቈጣጠር ሥርዐት መሠረት ግን፣ ይህ ወቅት የንጉሡ አራተኛው የንግሥና ዘመን ነው (ኤር25፥1፤ 46፥2)::

1፥2 *ወሰዳቸው፤* ይሁዳ ከእግዚአብሔር ጋር የገባችውን ቃል ኪዳን ስላፈረሰች፣ ሰንበትን ስለሻረችና ጣዖትን ስላመለከች (ዘሌ25፥1-7፤26፥27-35፤2ዜና36፥14-21 ይመ) በናቡከደናፆር ተማርካ ወደ ባቢሎን ተወሰደች:: የመጀመሪያው ምርኮ ዳንኤልን (በ605 ዓ.ቅ.ክ)፣ ሁለተኛው ምርኮ (597 ዓ.ቅ.ክ.) ሕዝቅኤልን ያቀፈ ነበር:: በሦስተኛውም የምርኮ ጊዜ (586 ዓ.ቅ.ክ.) ባቢሎናውያን ኢየሩሳሌምንና በዚያ የነበረውን ቤተ መቅደስ አጠፉ::

1፥4 *የባቢሎናውያንን ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ፤* ውስብስብ በሆነ በሱሜራውያንና በአካዲያን የኪዩኒፎርም ፊደል የተጻፈውን ጥንታዊ ሥነ ጽሑፍ የሚያጠቃልል ነው:: ባቢሎን ብዙ ብሔረሰቦች የሚኖሩባት ስትሆን፣ የሕዝቧ መገናኛ ቋንቋም አራማይክ ነበር፤ የአራማይክ ቋንቋም በቀላሉ በሚለመድ ፊደል የሚጻፍ ነበር፤ (2፥4 ይመ)

1፥6 *ዳንኤል፤* "እግዚአብሔር ዳኛዬ ነው" የሚል ትርጒም አለው፤ አናንያ፤ "እግዚአብሔር ጸጋን ያሳያል" ማለት ነው:: ሚሳኤል፤ "እንደ እግዚአብሔር ያለ ማን ነው?" ማለት ነው:: *አዛርያ፤* "እግዚአብሔር ይረዳል" ማለት ነው::

1፥7 *ብልጣሶር፤* ምናልባት በባቢሎናውያን እምነት፣ "ቤል (ማርዱክ) ሕይወቱን ይጠብቃል" ማለት ነው:: *ሲድራቅ* "የአኩ ትእዛዝ" ማለት ሊሆን ይችላል፤ አኩ የሱሜራውያን የጨረቃ አምላክ ነው:: *ሚሳቅ፤* እንደ አኩ ያለ ማን ነው?" ማለት ሳይሆን አይቀርም:: *አብደናጎ፤* "የኔጎ ወይም የኔቦ አገልጋይ" ማለት ነው::

1፥8 *በንጉሡ ምግብና የወይን ጠጅ፤* ምግብ መጀመሪያ ለጣዖት መሥዋዕት ሆኖ የሚቀርብ በመሆኑ፣ በናቡከደናፆር ገበታ ላይ ያለ ምግብ ሁሉ በእስራኤሎች ፊት የረከሰ ነበር:: ከወይን ጠጁም በጣዖቱ መሠዊያ ላይ ይፈስ ነበር:: በሥርዐታቸው መሠረት ንጹሕ ያልሆኑ እንስሳት ለመብል ከመቅረባቸው በተጨማሪ አስተራረዳቸውና አዘገጃጀታቸው ሕጉ በሚያዘው መሠረት አልነበረም:: *ራሱን እንዳያረክስ...ፈቃድ ጠየቀው፤* እምነቱ የቱን ያህል ጽኑ እንደ ሆነ ገለጸ::

1፥9 *እግዚአብሔርም ለዳንኤል በጃንደረቦቹ አለቃ ፊት ሞገስን...ሰጠው፤* የዮሴፍና የዳንኤል የሥራ ኀላፊነት በብዙ መልክ ተመሳሳይነት ነበራቸው (ዘፍ39-41 ይመ)::

1፥12 *አገልጋዮችህን...ፈትነን፤* ዳንኤል ከዐመፅ ይልቅ አማራጭ የመፍትሔ ሐሳቦችን በማቅረብ አስተዋይነቱን ገለጸ:: ዐሥር ብዙውን ጊዜ ፍጹምነትን የሚያመለክት ቊጥር ነው::

*1፥17፤* ዳንኤልና ጓደኞቹ በእግዚአብሔር ርዳታ በኰከብ ቈጠራ ላይ የተመሠረተውን የባቢሎናውያንን ሥነ ጽሑፍና በሕልም አማካይነት የሚደረገውን የጥንቈላ አሠራር በሚገባ ዐወቁ:: ነገር ግን ዐቢይ የሆነ ጒዳይ እንዲተረጒሙና እንዲተነብዩ (2፥3-11፤ 4፥7 ይመ) ባስፈለገ ጊዜ የአረማውያን ሥነ ጽሑፍ ዋጋ ቢስ ሆኖ ተገኘ:: ዳንኤልም በትክክል ለመተርጐም የቻለው እግዚአብሔር ባደረገለት ልዩ መገለጥ ነበር (2፥17-28)::

1፥20 *አስማተኞች፤* የዘፍ 41፥8 ማብ ይመ:: *ዐሥር፤*

በልጠው አገኛቸው::
21ዳንኤልም፣ ንጉሥ ቂሮስ እስከ ነገሠ
በት እስከ መጀመሪያው ዓመት ድረስ እዚ
ያው ቈየ::

## ናቡከደነፆር ያለመው ሕልም

2 ናቡከደነፆር በነገሠ በሁለተኛው ዓመት
ሕልም አለመ፤ መንፈሱ ታወከ፤ እንቅ
ልፍም ከእርሱ ራቀ:: 2ያለመውንም ሕልም
እንዲነግሩት ንጉሡ ጠንቋዮችን፣ አስማተ
ኞችን፣ መተተኞችንና ኮከብ ቈጣሪዎችን[a]
እንዲጠሩ አዘዘ፤ እነርሱም ገብተው በፊቱ
ቆሙ፤ 3እርሱም፣ “አንድ ሕልም አለምሁ፤
ሕልሙም ምን እንደሆነ[b] ለማወቅ መንፈሴ
ተጨንቆአል” አላቸው::
4ከዚያም ኮከብ ቈጣሪዎቹ ለንጉሡ በአረ
ማይክ[c] ቋንቋ “ንጉሥ ሆይ፤ ለዘላለም ንገሥ!
ሕልምህን ለአገልጋዮችህ ንገረን፤ እኛም
እንፈታልሃለን” አሉት::
5ንጉሡም ለኮከብ ቈጣሪዎቹ እንዲህ ሲል
መለሰ፤ “ሕልሙንና ትርጕሙን ባትነግሩኝ
አካላችሁ እንዲቈራረጥና ቤቶቻችሁም የፍ
ርስራሽ ክምር እንዲሆኑ ወስኛለሁ 6ነገር
ግን ሕልሙንና ትርጕሙን ብትነግሩኝ፣ ስጦ
ታና ሽልማት፣ ታላቅ ክብርም ከእኔ ትቀበላላ
ችሁ፤ ሕልሙን ንገሩኝ፤ ትርጕሙንም አሳ
ውቁኝ::”
7እነርሱም እንደ ገና፣ “ንጉሥ ሕልሙን
ለአገልጋዮቹ ይንገረን፤ እኛም እንተረጕመዋ
ለን” ብለው መለሱ::
8ንጉሡም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው፤ “እኔ
ምን ብዬ እንደወሰንሁ ስለምታውቁ፣ ጊዜ
ለማራዘም እንደምትሞክሩ ተረድቼአለሁ፤
9ሕልሙን ባትነግሩኝ፣ አንድ ቅጣት ይጠብ
ቃችኋል፤ ሁኔታው ይለወጣል ብላችሁ በማ
ሰብ የሚያሳስቱ ነገሮችንና ክፉ ሐሳቦችን
ልትነግሩኝ አሢራችኋል፤ ስለዚህ ሕልሙን
ንገሩኝ፤ ትርጕሙንም ልትነግሩኝ እንደም
ትችሉ በዚህ ዐውቃለሁ::”
10ኮከብ ቈጣሪዎቹም ለንጉሡ እንዲህ
ብለው መለሱ፤ “ንጉሡ የጠየቀውን ጥያቄ
ሊመልስ የሚችል ሰው በምድር ላይ አይገ
ኝም! ማንም ንጉሥ ምንም ያህል ታላቅና
ኀያል ቢሆን፣ እንዲህ ዐይነት ነገር ማንኛ
ውንም ጠንቋይ፣ አስማተኛ ወይም ኮከብ
ቈጣሪን ጠይቆ አያውቅም:: 11ንጉሡ የሚ
ጠይቀው እጅግ አስቸጋሪ ነገርን ነው፤ በሰዎች
መካከል ከማይኖሩት ከአማልክት በቀር
ለንጉሡ የሚገልጽለት የለም::”
12ይህም ንጉሡን እጅግ አበሳጨው፤ እስ
ቈጣውም፤ በባቢሎን ያሉ ጠቢባን ሁሉ
እንዲገደሉም አዘዘ፤ 13ጠቢባን ሁሉ እንዲ
ገደሉም ዐዋጅ ወጣ፤ ዳንኤልንና ጓደኞቹን
ፈልገው እንዲገድሉ ሰዎች ተላኩ::
14የንጉሡ ዘበኞች አለቃ አርዮክ፣ የባቢ
ሎንን ጠቢባን ለመግደል በመጣ ጊዜ፣
ዳንኤል በጥበብና በዘዴ አነጋገረው::
15የንጉሡን መኰንን፣ “ንጉሡ እንዲህ ዐይ
ነት ከባድ ዐዋጅ ያወጣው ስለ ምንድነው?”
ሲል ጠየቀው፤ አርዮክም ነገሩን ለዳንኤል
ገለጠለት:: 16በዚህ ጊዜ፣ ዳንኤልም ገብቶ
ሕልሙን ይተረጕምለት ዘንድ ጊዜ እንዲ
ሰጠው ንጉሡን ጠየቀው::
17ከዚህ በኋላ ዳንኤል ወደ ቤቱ ተመልሶ
ለጓደኞቹ ለአናንያ፣ ለሚሳኤልና ለአዛርያ
ነገሩን ገለጠላቸው:: 18እርሱና ጓደኞቹ
ከቀሩት የባቢሎን ጠቢባን ጋር እንዳይገ
ደሉ፣ የሰማይ አምላክ ምሕረት ያደርግላ
ቸውና ምስጢሩንም ይገልጥላቸው ዘንድ
እንዲጸልዩ አሳሰባቸው:: 19ለዳንኤልም
ምስጢሩ በሌሊት በራእይ ተገለጠለት፤ ዳን
ኤልም የሰማይን አምላክ አመሰገነ፤ 20እንዲ
ህም አለ፤

“ጥበብና ኀይል የእርሱ ነውና፣
የእግዚአብሔር ስም ከዘላለም እስከ
ዘላለም ይባረክ::
21ጊዜንና ወቅትን ይለውጣል፤
ነገሥታትን በዙፋን ያስቀምጣል፣
ደግሞም ያወርዳቸዋል፤
ጥበብን ለጠቢባን፣
ዕውቀትንም ለሚያስተውሉ ይሰጣል::
22የጠለቀውንና የተሰወረውን ነገር ይገልጣል፤
በጨለማ ያለውን ያውቃል፤
ብርሃንም ከእርሱ ጋር ይኖራል::

1፥21 2ዜና36፥22፤ ዳን6፥28፤10፥1
2፥1 ቍ3፤ዘፍ20፥3፤ 41፥8፤አስ6፥1፤ኢዮ 33፥15:18፤ዳን4፥5
2፥2 ቍ10፤ዘፍ 41፥8፤ዘፀ7፥11፤ ኢሳ19፥3፤44፥25፤ኤር 27፥9፤ዳን4፥6
2፥3 ዳን4፥5
2፥4 ዕዝ4፥7፤ነህ2፥3
2፥5 ቍ12፤ዘፍ 41፥32፤ዕዝ6፥11፤ ዳን3፥29
2፥6 ቍ48፤ዳን 5፥7 :16
2፥9 አስ4፥11፤ኢሳ 41፥22-24
2፥10 ቍ2:27፤ዳን 3፥8፤4፥7፤5፥8
2፥11 ዘፍ41፥38
2፥12 ቍ5፤ዳን 3፥13:19
2፥13 ዳን1፥20፤ 5፥19
2፥17 ዳን1፥6
2፥18 ቍ23፤ዕዝ 1፥2፤ነህ1፥4፤ኢሳ 37፥4፤ኤር33፥3፤ዮና 1፥9፤ራእ11፥13
2፥19 ቍ28፤ኢሱ 22፥33፤ኢዮ 33፥15፤ ዳን1፥17
2፥20 ኢዮ9፥4፤ መዝ113፥2፤145፥ 1-2፤ኤር32፥19
2፥21 2ሳሙ14፥17፤ ኢዮ12፥19፤ መዝ 75፥6-7፤119፥34፤ ዳን4፥17፤7፥25፤ሮሜ 13፥1፤ያዕ1፥5
2፥22 ዘፍ40፥8፤ ኢዮ12፥22፤ መዝ139፥11-12፤ ኢሳ45፥7፤ኤር

[a]2 ወይም ከለዳውያንን እንዲሁም 4:5 እና 10
[b]3 ወይም ምን እንደ ነበር
[c]4 ይህ ምዕራፍ ከዚህ ጀምሮ እስከ ም 7 ድረስ የተጻፈው በአረማይስጥ ነው::

የቍ12፥ማብ ይመ::
1፥21 *ንጉሥ ቂሮስ እስከ ነገሠበት እስከ መጀመሪያው ዓመት፤* በባቢሎን ላይ ነግሦ በነበረበት ጊዜ ማለት ነው (539 ዓ.ቅ.ክ.):: ዳንኤል በ537 ዓ.ቅ.ክ እንኳ በዚያ ይኖር ስለ ነበር (10፥1) በባቢሎን ምድር ተግዘው የነበሩት አይሁድ ወደ አገራቸው ሲመለሱ አይቶአል::
2፥1 *ናቡከደነፆር...በሁለተኛው ዓመት፤* በ604 ዓ.ቅ.ክ. ማለት ነው::
2፥4 *በአረማይክ* ኮከብ ቈጣሪዎቹ ከተለያዩ ጐሣዎች የተውጣጡ ስለ ሆኑ፣ ሁሉ ሰው በሚረዳው በአረማይክ ቋንቋ ይናገሩ ነበር:: ከዚህ ምዕራፍ ጀምሮ እስከ ም 7 ድረስ ያለው ታሪክ የተጻፈውም በዚሁ ቋንቋ ነበር:: እነዚህ ስድስት ምዕራፎች ስለ ቅርብ ምሥራቅ ዐበይት የሆኑትን ጒዳዮች ለአሕዛብ ወገኖች ዐቅፈው የያዙ በመሆናቸው፣ ሁሉም ሰው በሚግባባበት ቋንቋ ተጽፈው ነበር:: የመጨረሻዎቹ አምስት ምዕራፎች ግን (8-12) ምርጥ የሆኑትን ሕዝብ ልዩ ጒዳዮች የያዙ በመሆናቸው ወደ ዕብራይስጥ ቋንቋ ተመልሰዋል::
2፥11 *በሰዎች መካከል ከማይኖሩት፤* በቀላሉ የሚገኙ አይደሉም ማለት ነው::
2፥14 *አርዮክ* የቃሉ ትርጕም በትክክል አይታወቅም:: ከብዙ ምእተ ዓመታት በፊት የነበረው የመስጴጦምያ ንጉሥ ስምም አርዮክ ነበር (ዘፍ14፥1:9)::
2፥18 *የሰማይ አምላክ* የዕዝ 1፥2 ማብ ይመ:: *ምስጢሩንም፤* በዳንኤል መጽሐፍ ተደጋግሞ የተጠቀሰ ቍልፍ ቃል ነው (2፥19:27-30: 47፤4፥9):: ከሙት ባሕር አቅራቢያ ቁምራን ከተባለ ስፍራ በተገኙ የጥንት ጽሑፎችም ላይ ይኸው ቃል በብዛት ተጠቅሶአል (“በሁለቱ ኪዳናት መካከል የነበረው ዘመን” የሚለውን ከገጽ 1421 ይመ):: በአዲስ ኪዳን በግሪክ ቋንቋ የገባው የዚህ ቃል አቻ ትርጕም፣ በእግዚአብሔር ለተመረጡ ነቢያትና ሐዋርያት (የሮሜ11፥25 ማብ ይመ) ብቻ የሚገለጠውን የእግዚአብሔርን ምስጢር የሚያመለክት ነው::
2፥22 *ብርሃንም ከእርሱ ጋር ይኖራል፤* መዝ36፥9 ይመ::

23የአባቶቼ አምላክ ሆይ፤ አመሰግንሃለሁ፤
አከብርሃለሁም፤
ጥበብንና ኀይልን ሰጥተኸኛልና፤
ከአንተ የጠየቅነውን ነገር አሳውቀኸኛል፤
የንጉሡን ሕልም አሳውቀኸናል።”

## ዳንኤል ሕልሙን ተረጐመ

24ዳንኤልም የባቢሎንን ጠቢባን እንዲ
ገድል ንጉሡ ወዳዘዘው ወደ አርዮክ ሄዶ፣
“የባቢሎንን ጠቢባን አትግደል፤ ወደ ንጉሡ
ውሰደኝ፤ እኔም ሕልሙን እተረጒምለታለሁ”
አለው።
25አርዮክም ዳንኤልን ወዲያውኑ ወደ
ንጉሡ በመውሰድ፣ “ሕልሙንና ትርጒሙን
ለንጉሡ መግለጥ የሚችል ሰው ከይሁዳ ምር
ኮኞች መካከል አግኝቻለሁ” አለው።
26ንጉሡም ብልጣሶር የተባለውን ዳንኤ
ልን፣ “ያየሁትን ሕልምና ትርጒሙን ልት
ነግረኝ ትችላለህን?” አለው።
27ዳንኤልም እንዲህ አለ፤ “አንድም ጠቢብ፣
አስማተኛ፣ ጠንቋይም ሆነ ቃላተኛ ንጉሡ
የጠየቀውን ምስጢር መግለጥ የሚችል
የለም፤ 28ነገር ግን ምስጢርን የሚገልጥ
አምላክ በሰማይ አለ፤ እርሱም በሚመጡት
ዘመናት የሚሆነውን ነገር ለንጉሥ ናቡከ
ደነፆር ገልጦአል፤ በዐልጋህ ላይ ተኝተህ ሳለ
በአእምሮህ የነበረው ሕልምና ራእይ ይህ ነው፦
29“ንጉሥ ሆይ፤ ተኝተህ ሳለ፣ አእምሮህ
ወደ ፊት ሊሆን ስላለው ነገር ያሰላስል ነበር፤
ምስጢርን ገላጭ የሆነውም ወደ ፊት የሚሆ
ነውን ነገር አሳየህ። 30ይህ ምስጢር ለእኔ
የተገለጠው፣ ከሰው ሁሉ ይልቅ ታላቅ ጥበብ
ስላለኝ አይደለም፤ ነገር ግን ንጉሥ ሆይ፤
አንተ ትርጒሙን እንድታውቅና በአእም
ሮህ ታሰላስለው የነበረው ነገር ምን እንደ
ሆነ ትረዳ ዘንድ ነው።
31“ንጉሥ ሆይ፤ በፊት ለፊትህ ግዙፍ
የሆነ፣ የሚያብረቀርቅና የሚያስፈራ ታላቅ
ምስል ቆሞ አየህ፤ 32የምስሉ ራስ ከንጹሕ
ወርቅ፣ ደረቱና ክንዶቹ ከብር፣ ሆዱና
ጭኖቹ ከናስ የተሠሩ ነበሩ፤ 33ቅልጥሞቹም
ከብረት፣ እግሮቹም ከፊሉ ከብረት፣ ከፊ
ሉም ከሸክላ የተሠሩ ነበሩ። 34ይህን በመ
መልከት ላይ ሳለህ፣ አንድ ድንጋይ የሰው
እጅ ሳይነካው ተፈንቅሎ ወረደ፤ ከብረትና
ከሸክላ የተሠሩትን የምስሉን እግሮች መታ
ቸው፤ አደቀቃቸውም። 35ወዲያውኑም ብረቱ፣
ሸክላው፣ ናሱ፣ ብሩና ወርቁ ተሰባበሩ፤ በበጋ
ወራት በዐውድማ ላይ እንደሚገኝ ዕብቅም
ሆኑ፤ ነፋስም አንዳች ሳያስቀር ጠራረጋቸው፤
ምስሉን የመታው ድንጋይ ግን ታላቅ ተራራ
ሆነ፤ ምድርንም ሞላ።
36“ሕልሙ ይህ ነበር፤ አሁን ትርጒሙን
ለንጉሥ እንናገራለን። 37ንጉሥ ሆይ፤ አንተ
የነገሥታት ንጉሥ ነህ፤ የሰማይ አምላክ መን
ግሥትንና ሥልጣንን፣ ኀይልንና ክብርን ሰጥ
ቶሃል፤ 38የሰው ልጆችን፣ የምድር አራዊት
ንና የሰማይ ወፎችን በእጅህ አሳልፎ ሰጥቶ
ሃል፤ በየትም ቦታ ቢሆኑ፣ በሁሉም ላይ ገዥ
አድርጎሃል፤ እንግዲህ የወርቁ ራስ አንተ
ነህ።
39“ከአንተም በኋላ ከአንተ የሚያንስ ሌላ
መንግሥት ይነሣል፤ ቀጥሎም በናስ የተመሰ
ለው ሦስተኛ መንግሥት ይነሣል፤ መላውን
ምድርም ይገዛል። 40በመጨረሻም ሁሉን ነገር
እንደሚቀጠቅጥና እንደሚሰብር ብረት ብርቱ
የሆነ አራተኛ መንግሥት ይነሣል፤ ብረት
ሁሉን ሰባብሮ እንደሚያደቅ ከእርሱ በፊት
የነበሩትን መንግሥታት ሁሉ ሰባብሮ ያደቃ
ቸዋል። 41እግሮቹና ጣቶቹ ከፊል ብረትና
ከፊል ሸክላ ሆነው እንዳየህ፣ እንዲሁ የተከ
ፋፈለ መንግሥት ይሆናል፤ ነገር ግን ብረ
ትና ሸክላ ተደባልቀው እንዳየህ በከፊል
የብረት ጥንካሬ ይኖረዋል። 42የእግሮቹ ጣቶች
ከፊሉ ብረት ከፊሉ ሸክላ እንደ ሆኑ ሁሉ፣
ይህም መንግሥት በከፊሉ ብርቱ በከፊሉ
ደካማ ይሆናል። 43ብረትና ሸክላ ተደባልቀው
እንዳየህ ሁሉ ሕዝቡም ድብልቅ ይሆናል፤
ብረትና ሸክላ እንደማይዋሐድ ሁሉ ሕዝቡም
በአንድነት አይኖሩም።
44“በነዚያ ነገሥታት ዘመን፣ የሰማይ
አምላክ ፈጽሞ የማይፈርስና ለሌላም ሕዝብ
የማይሰጥ መንግሥት ይመሠርታል፤ እነዚ
ያን መንግሥታት ሁሉ ያደቃል፤ እስከ መጨ
ረሻውም ያጠፋቸዋል፤ ይህ መንግሥት ራሱ
ግን ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል። 45የሰው እጅ
ሳይነካው ከተራራ ተፈንቅሎ የወረደውና ብረ
ቱን፣ ናሱን፣ ሸክላውን፣ ብሩንና ወርቁን ያደ
ቀቀው ድንጋይ ራእይ ትርጓሜ ይህ ነው፦
“ታላቁ አምላክ ወደ ፊት የሚሆነውን
ለንጉሡ አሳይቶታል፤ ሕልሙ እውነት ነው፤
ትርጓሜውም የታመነ ነው።”
46ከዚያም ንጉሥ ናቡከደነፆር በግንባሩ
ተደፍቶ ለዳንኤል ሰገደለት፤ አከበረውም፤

23፥24፤ዳን5፥11፤ 1ቆሮ2፥10፤ዕብ4፥13፤ ያዕ1፥17
2፥23 ዘፍ31፥5፤ ዘፀ3፥15፤ሕዝ28፥3፤ ዳን1፥17
2፥24 ቊ14
2፥25 ዘዳ21፥10፤ ዳን1፥6፤5፥13፤6፥13
2፥26 ዳን1፥7
2፥27 ቊ10፤ዘፍ 41፥8
2፥28 ዘፍ40፥8፤ 49፥1፤መዝ4፥4፤ ኤር 10፥7፤ ሕዝ28፥3፤ ዳን1፥20፤4፥5፤ 10፥14፤አሞ4፥13፤ ማቴ24፥6፤ራእ1፥1፤ 22፥6
2፥29 ዘፍ41፥25
2፥30 ኢሳ45፥3፤ዳን 1፥17፤አሞ 4፥13
2፥31 ኢሳ25፥3-5፤ ዕን1፥7
2፥34 ቊ44-45፤ ኢዮ12፥19፤ 34፥24፤ መዝ2፥9፤ኢሳ60፥12፤ ዳን8፥25፤ዘካ4፥6
2፥35 መዝ1፥4፤ 37፥10፤ኢሳ2፥3፤ 17፥13፤41፥15-16፤ ሚክ4፥1፤ዘካ12፥3
2፥36 ዘፍ40፥12
2፥37 ዕዝ7፥12፤ኤር 27፥7፤ዳን 4፥26
2፥38 ኤር27፥6፤ዳን 4፥21-22፤5፥18
2፥39 ዳን7፥5
2፥40 ዳን7፥7
2፥44 ዘፍ27፥29፤ 1ሳሙ9፥20፤መዝ2፥9፤ 110፥5፤145፥13፤ ኢሳ9፥7፤ዳን 4፥34፤ 6፥26፤7፥14:27፤ አብ1፥21፤ሚክ4፥7:13፤ ሐጌ2፥22፤ማቴ21፥ 43-44፤ሉቃ1፥33፤ 1ቆሮ15፥24፤ራእ11፥ 15
2፥45 ዘፍ41፥25፤ ኢሳ28፥16፤ዳን8፥25፤ ራእ22፥6
2፥46 ዳን8፥17፤ ሐሥ10፥25፤14፥13

*2፥32-43*፤ በዚህ መጽሐፍ ቅዱስ መጨረሻ የሚገኘውን ካርታ 7ለ እና ካርታ 12 ይመ። የወርቁ ራስ አዲሱን የባቢሎንን መንግሥት (ቊ38፤ ኤር51፥7ይመ)፣ ከብር የተሠሩት ደረቱና ክንዶቹ ባቢሎን ከወደቀች በኋላ በቂሮስ የተመሠረተውን የሜዶንና የፋርስ መንግሥት፣ ከናስ የተሠሩት የምስሉ ሆድና ጭኖቹ በግምት በ330 ዓ.ቅ.ክ. በታላቁ እስክንድር የተቋቋመችውን የግሪክ መንግሥት፣ ከብረት የተሠሩት ቅልጥሞቹና እግሮቹ ደግሞ የሮምን መንግሥት ያመለክታል። አንዳንዶች በቍ41 ላይ የተጠቀሱት የእግር ጣቶቹም ቀደም ሲል በሮም መንግሥት ቍጥጥር ሥር የነበሩትን፣ በኋላ ግን ፌደራል መንግሥታት የሆኑትን እንደሚያሳዩ ይገልጻሉ። ምስሉ የተሠራበት ማዕድን ከወርቅ ወደ ብር፣ ከብር ወደ ናስ፣ ከናስ ወደ ብረት እየወረደ መሄዱ የገገሮች ኀይልና ገናናነት (ቊ39) ከፈላጭ ቈራጩ የናቡከደነፆር መንግሥት ተነሥቶ በተወካዮችና በመማክርት ጉባኤ ይተዳደር ወደ ነበረውና ዲሞክራሲያዊ ወደ ሆነው የሮም መንግሥት መድረሱን ያሳያል። በተጨማሪም ብረቱ ወደ ኋላ የመጡ መንግሥታት በጥንካሬና በዕድሜ ዘመን ረገድ ቀድመዋቸው ከመጡት መንግሥታት የላቁ መሆናቸውን ያመለክታል።

2፥35 *ተሰባበሩ፤* ማቴ21፥44 ይመ።

2፥44፤ አምስተኛው መንግሥት በኀጢአት በተበከለውና በሚፈርሰው የዚህ ዓለም መንግሥት ላይ የሚገነባውን ዘላለማዊውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ያመለክታል። ሥልጣኑም በምድር ሁሉ ላይ ይንሰራፋል (ቊ35)፤ በመጨረሻም በአዲስ ሰማይና በአዲስ ምድር ላይ ይሰፍናል (ራእ21፥1)።

መሥዋዕትና ዕጣንም እንዲያቀርቡለት አዘዘ። [47]ንጉሡም ዳንኤልን፣ "ይህን ምስጢር ልትገልጥ ችለሃልና፣ በእውነት አምላካችሁ የአማልክት አምላክና የነገሥታት ጌታ፣ ምስጢርንም ገላጭ ነው" አለው።

[48]ንጉሡም ዳንኤልን በከፍተኛ ሥልጣን ላይ አስቀመጠው፤ እጅግ ብዙ ስጦታዎችንም ሰጠው፤ የመላው ባቢሎን አውራጃ ገዥ አደረገው፤ በባቢሎን ጠቢባን ሁሉ ላይም አለቃ አድርጎ ሾመው። [49]ከዚህም በላይ በዳንኤል አሳሳቢነት ንጉሡ ሲድራቅን፣ ሚሳቅንና አብደናጎን የባቢሎን አውራጃ አስተዳዳሪዎች አድርጎ ሾማቸው፤ ዳንኤል ግን በቤተ መንግሥት ተቀመጠ።

## የወርቁ ምስልና የእቶን እሳት

**3** ንጉሡ ናቡከደነፆር ከፍታው ሥልሳ ክንድ፣ ወርዱ ስድስት ክንድ የሆነ የወርቅ ምስል አሠራ፤ በባቢሎንም አውራጃ በዱራ ሜዳ አቆመው። [2]ከዚያም መኳንንትን፣ ሹማምንትን፣ አገረ ገዦችን፣ አማካሪዎችን፣ የግምጃ ቤት ኀላፊዎችን፣ ዳኞችን፣ ሌሎች የሕግ ዐዋቂዎችንና በየአውራጃው ያሉትን ሹማምንት ሁሉ ላቆመው ምስል ምረቃ በዓል እንዲመጡ ጠራ። [3]መኳንንቱ፣ ሹማምንቱ፣ አገረ ገዦችን፣ አማካሪዎችን፣ የግምጃ ቤት ኀላፊዎቹ፣ ዳኞቹ፣ ሌሎች የሕግ ዐዋቂዎችና በየአውራጃው ያሉ ሹማምንት ሁሉ ንጉሥ ናቡከደነፆር ላቆመው ምስል ምረቃ በዓል ተሰበሰቡ፤ በምስሉም ፊት ቆሙ።

[4]ከዚያም ከፍ ባለ ድምፅ እንዲህ የሚል ዐዋጅ ታወጀ፤ "ሕዝቦች ሆይ፤ መንግሥታትና ልዩ ልዩ ቋንቋ የምትናገሩ ሰዎች ሁሉ፤ እንድታደርጉ የታዘዛችሁት ይህ ነው፦ [5]የመለከትና የእንቢልታ፣ የመሰንቆና የክራር፣ የበገናና የዋሽንት እንዲሁም የዘፈን ሁሉ ድምፅ ስትሰሙ፣ ንጉሥ ናቡከደነፆር ላቆመው የወርቅ ምስል ተደፍታችሁ መስገድ አለባችሁ፤ [6]ተደፍቶ የማይሰግድ ማንም ሰው ቢኖር፣ ወዲያውኑ በሚንበለበለው የእሳት እቶን ውስጥ ይጣላል።"

[7]ስለዚህ የመለከትና የእንቢልታ፣ የመሰንቆና የክራር፣ የበገናና የዋሽንት፣ የዘፈንም ሁሉ ድምፅ በሰሙ ጊዜ ወዲያውኑ ሕዝቡ ሁሉ፣ መንግሥታትና ልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩ ሰዎች፣ ንጉሥ ናቡከደነፆር ላቆመው የወርቅ ምስል ተደፍተው ሰገዱ።

2፥47 ቍ22:28፤ ዘዳ10፥17፤ዳን4፥9:25፤ 11፥36፤1ቆሮ14፥25፤ 1ጢሞ6፥15
2፥48 ቍ6፤ንን25፥ 28፤አስ8፥2፤ዳን1፥20፤ 4፥9፤5፥11፤8፥27
2፥49 ዳን1፥7፤3፥30፤ 6፥2
3፥1 ቍ14፤ኢሳ 46፥6፤ኤር16፥20፤ ዕን2፥19
3፥2 ቍ27፤አስ 1፥1፤ዳን6፥7
3፥4 ዳን4፥1፤6፥25፤ ራእ10፥11
3፥5 ቍ10:15፤ ዘፍ4፥21፤ራእ13፥12
3፥6 ቍ11:15:21፤ ኤር29፥22፤ዳን5፥19፤ 6፥7፤ማቴ13፥42:50፤ ራእ13፥15
3፥7 ቍ5
3፥8 ኢሳ19፥3፤ ዳን2፥10
3፥9 ነህ2፥3፤ዳን 5፥10፤6፥6
3፥10 ቍ4-6፤ ዳን6፥12
3፥12 አስ3፥3፤ ዳን2፥49፤6፥13
3፥13 ዳን2፥12
3፥14 ቍ1፤ኢሳ 46፥1፤ኤር50፥2
3፥15 2ዜና32፥15፤ ኢሳ36፥18-20
3፥16 ዳን1፥7
3፥17 ዘፍ48፥16፤ ኢዮ5፥19፤መዝ 18፥48፤27፥1-2፤ኤር 1፥8፤ዳን6፥20
3፥18 ቍ28፤ዘፀ 1፥17፤ኢሱ24፥15
3፥19 ዘሌ26፥18-28
3፥20 ዳን1፥7

[8]በዚህ ጊዜ አንዳንድ ኮከብ ቈጣሪዎች[ሬ] ወደ ፊት ቀርበው አይሁድን ከሰሱ፤ [9]ንጉሥ ናቡከደነፆርንም እንዲህ አሉት፤ "ንጉሥ ሆይ፤ ለዘላለም ንገሥ! [10]ንጉሥ ሆይ፤ አንተ እንዲህ ብለህ ዐዋጅ አውጥተህ ነበር፤ የመለከትና የእንቢልታ፣ የመሰንቆና የክራር፣ የበገናና የዋሽንት፣ የዘፈንም ድምፅ የሰማ ሁሉ ለወርቁ ምስል ተደፍቶ መስገድ አለበት፤ [11]ማንም ተደፍቶ ለወርቁ ምስል ባይሰግድ በሚንበለበለው የእሳት እቶን ውስጥ ይጣላል። [12]ነገር ግን ንጉሥ ሆይ፤ በባቢሎን አውራጃ አስተዳዳሪዎች አድርገህ የሾምሃቸው ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብደናጎ የሚባሉት አንዳንድ አይሁድ ትእዛዝህን አይቀበሉም፤ አማልክትህን አያገለግሉም፤ አንተም ላቆምኸው የወርቅ ምስል አይሰግዱም።"

[13]ንጉሥ ናቡከደነፆር በታላቅ ቍጣ ሲድራቅን፣ ሚሳቅንና አብደናጎን አስጠራቸው፤ እነዚህንም ሰዎች በንጉሡ ፊት አቀረቧቸው፤ [14]ናቡከደነፆርም እንዲህ አላቸው፤ "ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብደናጎ ሆይ፤ እኔ ላቆምሁት ምስል አለመስገዳችሁ፣ አማልክቴንም አለማገልገላችሁ እውነት ነው? [15]አሁንም ቢሆን የመለከቱንና የእምቢልታውን፣ የመሰንቆውንና የክራሩን፣ የበገናውንና የዋሽንቱን፣ የዘፈኑንም ሁሉ ድምፅ ስትሰሙ፣ እኔ ላቆምሁት የወርቅ ምስል ተደፍታችሁ ለመስገድ ዝግጁ ከሆናችሁ መልካም! ባትሰግዱለት ግን ወዲያውኑ ወደ ሚንበለበለው የእቶን እሳት ውስጥ ትጣላላችሁ፤ ታዲያ ከእጄ ሊያድናችሁ የሚችል አምላክ ማን ነው?"

[16]ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብደናጎ ለንጉሡ እንዲህ ብለው መለሱ፤ "ናቡከደነፆር ሆይ፤ በዚህ ጕዳይ ላይ ስለ ራሳችን መልስ መስጠት አያስፈልገንም። [17]ንጉሥ ሆይ፤ በሚንበለበለው የእቶን እሳት ውስጥ ብንጣል፣ የምናመልከው አምላክ ሊያድነን ይችላል፤ ከእጅህም ያድነናል። [18]ነገር ግን ንጉሥ ሆይ፤ ባያድነንም እንኳ፤ አማልክትህን እንደማናገለግል፣ ላቆምኸውም የወርቅ ምስል እንደማንሰግድ ዕወቅ።"

[19]ከዚያም ናቡከደነፆር በሲድራቅ፣ በሚሳቅና በአብደናጎ እጅግ ተቈጣ፣ ፊቱም ተለወጠባቸው፤ የእቶኑ እሳትም ቀደም ሲል ከነበረው ሰባት ዕጥፍ ተደርጎ እንዲነድ አዘዘ፤ [20]ከሰራዊቱም ብርቱ የሆኑትን ጥቂት

[ሬ]8 ወይም *ከላዳውያን*

*2፥48፤* ከዮሴፍ ታሪክ (ዘፍ41፥41-43) ጋር ያነጻጽሩ።

3፥1 ***የወርቅ ምስል፤*** እንዲህ ዐይነቱ ሐውልት ከሌላ ነገር ተሠርቶ በወርቅ የተለበጠ እንጂ ከንጹሕ ወርቅ የተሠራ አልነበረም። ***ከፍታው ሥልሳ ክንድ፤*** ሐውልቱ የቆመበትን መሠረት ጨምሮ ማለት ነው። ***በዱራ፤*** ከባቢሎን በስተ ደቡብ አያሌ ኪሎ ሜትር ርቆ የሚገኝ ልዩ ምልክቱ የድንጋይ ክምር የሆነ ወይም፣ "ዙሪያው በቅጥር የተከበበ ቦታ" ማለት ነው።

*3፥2፤* እነዚህ የየሰባቱ ክፍላተ አገር መሪዎች፣ በምስሉ ፊት ቆመው ቃለ መሐላ በመፈጸም ለአዲሱ መንግሥት ያላቸውን ታማኝነት መግለጽ ነበረባቸው፤ ምስሉም፣ "ናቡ" በመባል የተሰየመ ሲሆን፣ ይኸውም የንጉሥ ናቡከደነፆር ስም የመጀመሪያዎቹ ሁለት ፊደላት ናቸው። የናቡከደነፆር ስም በአካዲያን ቋንቋ፣ "ናቡ-ኩዱሪ-ኡሱር" ሲሆን፣ ትርጕሙም "ናቡ ሆይ ልጄን ጠብቅልኝ" ወይም "ናቡ ሆይ የአገሬን ዳር ድንበር ጠብቅልኝ" ማለት ነው።

*3፥5፤* በዳንኤል መጽሐፍ ላይ ከግሪክ ቋንቋ የተወረሱት ቃላት፣ "መሰንቆ"፣ "በገና" እና "ዋሽንት" ብቻ ናቸው። የግሪክ ሙዚቀኞችና የሙዚቃ መሣሪያዎች ናቡከደነፆር ከመንገሡ በፊት በነበሩ የአሦራውያን ጽሑፎችም ላይ ተጠቅሰዋል።

3፥12 ***አማልክትህን አያገለግሉም.....ምስል አይሰግዱም፤*** ከንጉሡ ቃል ይልቅ ለእግዚአብሔር ቃል ታዘዙ (ዘፀ20፥3-5)።

*3፥17፤* ዕብ11፥34 ይመ።

3፥18 ***ባያድነንም፤*** እግዚአብሔር ይታደጋቸው ዘንድ ፈቃደኛ ቢሆንም ባይሆንም፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም በእምነታቸው ጸኑ(ቍ17)።

*3፥19፤* የአካባቢው አየር በብዙ ወናፎች ተገፍቶ እሳቱ ወዳለበት እንዲገባ ተደርጎአል፤ እሳቱም በሰባት ወናፎች በመ

ወታደሮች፣ ሲድራቅን፣ ሚሳቅንና አብደናጎን
አስረው ወደሚንበለበለው የእቶን እሳት ውስጥ
እንዲጥሏቸው አዘዘ። 21እነርሱም መጐናጸፊ
ያቸውን፣ ሱሪያቸውን፣ የራስ ጥምጥማቸውንና
ሌሎች ልብሶቻቸውን እንደ ለበሱ ታስረው
በሚንበለበለው የእቶን እሳት ውስጥ ተጣሉ።
22የንጉሡ ትእዛዝ አስቸኳይ ስለነበረና የእቶ
ኑም እሳት እጅግ ስለነደደ፣ የእሳቱ ወላፈን
ሲድራቅን፣ ሚሳቅንና አብደናጎን ወስደው
የጣሏቸውን ወታደሮች ገደላቸው። 23ሦስቱ
ሰዎች ግን ተጠፍረው እንደ ታሰሩ በሚንበ
ለበለው የእቶን እሳት ውስጥ ወደቁ።
24ከዚህ በኋላ ንጉሥ ናቡከደነፆር በአድና
ቆት ከተቀመጠበት ዘሎ በመነሣት አማካሪዎ
ቹን "አስረን በእሳት ውስጥ የጣልናቸው ሰዎች
ሦስት አልነበሩምን?" ሲል ጠየቀ።
እነርሱም፣ "ንጉሥ ሆይ፤ እውነት ነው" አሉ።
25እርሱም፣ "እነሆ፤ ያልታሰሩና ያልተጐዱ
አራት ሰዎች በእሳቱ ውስጥ ሲመላለሱ አያ
ለሁ፤ አራተኛውም የአማልክትን ልጅ ይመ
ስላል" አላቸው።
26ናቡከደነፆርም ወደሚነደው የእቶን
እሳት በር ቀረብ ብሎ ከፍ ባለ ድምፅ፣
"እናንተ የልዑል አምላክ አገልጋዮች ሲድራቅ፣
ሚሳቅና አብድናጎ፤ ኑ ውጡ! ወደዚህ ኑ!"
አላቸው።
ስለዚህ ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብድናጎ
ከእሳቱ ወጡ፤ 27መኳንንቱ፣ ሹማምንቱ፣
አገረገዦቹና የቤተ መንግሥት አማካሪዎ
ችም በዙሪያቸው ተሰበሰቡ፤ እነርሱም እሳቱ
ሰውነታቸውን እንዳልጐዳው፣ ከራሳቸውም
ጠጕር አንዲቷ እንኳ እንዳልተቃጠለች
አዩ፤ የመጐናጸፊያቸው መልክ አልተለወጠም፤
የእሳትም ሽታ በላያቸው አልነበረም።
28ከዚያም ናቡከደነፆር እንዲህ አለ፤
"መልአኩን ልኮ አገልጋዮቹን ያዳነ፣ የሲድ
ራቅ፣ የሚሳቅና የአብደናጎ አምላክ ይባረክ፤
በእርሱ በመታመን የንጉሡን ትእዛዝ ጥሰው፣
ከአምላካቸው በቀር ሌላ አምላክ ለማገልገ
ልም ሆነ ለእርሱ ለመስገድ ፈቃደኛ ባለ
መሆን ሕይወታቸውን አሳልፈው ሰጥተ
ዋልና። 29ስለዚህ እንደዚህ የሚያድን ሌላ
አምላክ የለምና በሲድራቅ፣ በሚሳቅና በአ
ብደናጎ አምላክ ላይ ማናቸውንም ቃል
የሚናገሩ ሕዝቦችም ሆኑ ልዩ ልዩ ቋንቋ
የሚናገሩ ሁሉ ይቈራረጣሉ፤ ቤቶቻቸ
ውም የፍርስራሽ ክምር ይሆናሉ ብዬ አዝ
ዣለሁ።"

3፥22 ዳን1፥7
3፥26 ዳን4፥2፡34
3፥27 ቍ2፤መዝ 91፥3-11፤ኢሳ43፥2፤ ዳን6፥7፡23፤ዕብ 11፥ 32-34
3፥28 ቍ18፤ዘዳ 31፥20፤ኢዮ13፥15፤ መዝ26፥1፤34፥7፤84፥ 12፤97፥10፤ዳን6፥22፤ ሐሥ5፥19፤12፥11
3፥29 ዕዝ6፥11፤ ዳን6፥26፡ዕ27
3፥30 ዳን2፥49
4፥1 ዳን3፥4፤6፥25
4፥2 መዝ74፥9፤ ዳን3፥26
4፥3 መዝ105፥27፤ ዳን2፥44፤6፥27
4፥4 መዝ30፥6፤ ኢሳ32፥9
4፥5 ቍ19፤ዘፍ 41፥8፤ኢዮ3፥26፤ መዝ4፥4፤ዳን2፥1፡3፡2 8፤5፥6
4፥6 ዳን2፥2
4፥7 ዘፍ41፥8፤ኢ ሳ44፥25፤ዳን2፥2፡10
4፥8 ዘፍ41፥38፤ ዳን1፥7
4፥9 ዳን2፥48፤ 5፥11-12
4፥10 ቍ5፤መዝ 4፥4፤ሕዝ31፥3-4
4፥11 ሕዝ19፥11፤ 31፥5
4፥12 ሕዝ17፥23፤ ማቴ13፥32

30ከዚያም ንጉሡ ሲድራቅን፣ ሚሳቅንና
አብደናጎን በባቢሎን አውራጃ ላይ ሾማቸው።

## ናቡከደነፆር በሕልሙ ዛፍ አየ

4 ከንጉሥ ናቡከደነፆር፣ በምድር ሁሉ
ለሚኖሩ ሕዝቦች፣ መንግሥታትና ልዩ
ልዩ ቋንቋዎችን ለሚናገሩ ሰዎች ሁሉ፤ ሰላም
ይብዛላችሁ!
2ልዑል አምላክ ያደረገልኝን ታምራዊ ምል
ክቶችንና ድንቅ ሥራዎች ስነግራችሁ እጅግ
ደስ እያለኝ ነው።

3ምልክቱ እንዴት ታላቅ ነው!
ድንቁስ እንዴት ብርቱ ነው!
መንግሥቱ የዘላለም መንግሥት ነው፤
ግዛቱም ከትውልድ እስከ ትውልድ
ይኖራል።

4እኔ ናቡከደነፆር በቤቴ ደልቶኝ በቤተ
መንግሥቴም ተመችቶኝ እኖር ነበር፤ 5አንድ
ያስፈራኝ ሕልም አየሁ፤ በዐልጋዬ ላይ ተኝቼ
ሳለሁ፣ ወደ አእምሮዬ የመጡት ምስሎችና
ራእዮች አስደነገጡኝ። 6ስለዚህ የባቢሎን
ጠቢባን ሁሉ ወደ እኔ መጥተው ሕልሜን
እንዲተረጕሙልኝ አዘዝሁ። 7ጠንቋዮቹ፣
አስማተኞቹ፣ ኮከብ ቈጣሪዎቹና[a] መተተ
ኞቹ በመጡ ጊዜ ሕልሙን ነገርኋቸው፤ ነገር
ግን ሊተረጕሙልኝ አልቻሉም። 8በመጨረ
ሻም በአምላኬ ስም ብልጣሶር ተብሎ የተጠ
ራውና የቅዱሳን አማልክት መንፈስ ያለ
በት ዳንኤል ገብቶ በፊቴ ቆመ፤ ሕልሜንም
ነገርሁት።
9እኔም እንዲህ አልሁት፤ "የጠቢባን አለቃ
ብልጣሶር ሆይ፤ የቅዱሳን አማልክት መን
ፈስ በአንተ ውስጥ እንዳለ ዐውቃለሁ፤
ምንም ዐይነት ምስጢር አያስቸግርህም፤
ያየሁት ሕልም እነሆ፤ ተርጕምልኝ። 10በዐ
ልጋዬ ላይ ተኝቼ ሳለሁ ያየሁት ራእይ ይህ
ነው፦ እነሆ በፊቴ በምድር መካከል ቁመቱ
እጅግ ረጅም የሆነ ዛፍ ቆሞ ተመለከትሁ።
11ዛፉም እጅግ አደገ፤ ጠነከረም፤ ጫፉም ሰማይ
ደረሰ፤ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስም ይታይ
ነበር። 12ቅጠሎቹ ያማሩ፣ ፍሬዎቹ የተን
ዠረገጉ ነበሩ፤ በላዩም ለሁሉ የሚሆን ምግብ
ነበረበት። የምድር አራዊት ከጥላው በታች
ያርፉ ነበር፤ በቅርንጫፎቹም ላይ የሰማይ
ወፎች ይኖሩ ነበር፤ ፍጥረትም ሁሉ ከእ
ርሱ ይመገብ ነበር።

[a]7 *ወይም ከለዳውያን*

ታግዞ ሰባት ዕጥፍ እንዲነድ ሆኖአል። "ቀድሞ ከነበረው ይልቅ ሰባት ዕጥፍ እንዲነድ ሆኖ" የሚለው አገላለጽ፣ "በሙሉ ኀይል ገሎ" የሚለውን ሐሳብ ለመግለጽ የገባ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው፤ ቍጥር ሰባት ፍጹምነትን ያመለክታልና።

*3፥25*፤ መዝ91፥9-12 ይመ። ***የአማልክትን ልጅ***፤ ናቡከደነፆር እዚህ ላይ የሚናገረው ብዙ አማልክትን እንደሚያመልክ ሰው ሲሆን፣ "አራተኛው" ሁሉን በሚችል የእስራኤል አምላክ የተላከ ነው ብሎ በማመን (ቍ28) ያለማመንታት ተቀበለ።

*3፥29*፤ 2፥5 ይመ።

*4፥1-3*፤ ናቡከደናፆር በቍ4-37 ላይ የተመለከተውን የሕይወት ልምድ ካገኘ በኋላ ይህን ማጠቃለያ ሐሳብ ሊናገር ችሏል፤ ንጉሡ ስለ እግዚአብሔር በተናገረ ጊዜ የተጠቀመባቸው ቃላት የዳንኤል ሕይወት ለእርሱ ምን ያህል አርአያ እንደ ነበረ የሚያመለክቱ ናቸው።

4፥8 ***በአምላኬ ስም***፤ የ1፥7 ማብ ይመ። "ቤል" (ጌታ) ማርዱክ ለተባለው አምላክ የተሰጠ የማዕረግ ስም ነው።

4፥10 ***ዛፍ***፤ በቍ22 ላይ ትርጓሜው ተሰጥቶአል።

4፥11 ***እጅግ አደገ፤ ጠነከረም***፤ በናቡከደናፆር ሕንጻዎች ላይ ከተጻፉት የቅርጽ ጽሑፎች አንዱ ባቢሎንን ከተንሰራፋ ዛፍ ጋር አነጻጽሮአታል (ከቍ22 ጋር ያነጻጽሩ)። ***ጫፉም ሰማይ ደረሰ***፤ በመስጴጦምያ የነበሩትን የቤተ ጣዖት ግንቦች የሚያመለክት ነው (የዘፍ 11፥4 ማብ ይመ)።

[13]“በዐልጋዬ ላይ ተኝቼ ሳለሁ ባየሁት
ራእይ አንድ ቅዱስ መልእክተኛ[ሀ] ከሰማይ
ሲወርድ አየሁ። [14]እርሱም ድምፁን ከፍ
አድርጎ እንዲህ አለ፤ ‘ዛፉን ቍረጡ፤ ቅርን
ጫፎቹን ጨፍጭፉ፤ ቅጠሎቹን አራግፉ፤
ፍሬውንም በትኑ፤ ከሥሩ ያሉት እንስሶች፣
በቅርንጫፎቹም ላይ ያሉት ወፎች ይሽሹ።
[15]ነገር ግን ጒቶውና ሥሩ በሜዳው ሣር ላይ
በብረትና በናስ ታስሮ በመሬት ውስጥ ይቈይ።
“ ‘በሰማይ ጠል ይረስርስ፤ በጥሻም ውስጥ
ከአራዊት ጋር ይኑር። [16]አእምሮው ከሰው
አእምሮ ይለወጥ፤ የእንስሳም አእምሮ ይሰጠው፤
ሰባት ዓመትም ይለፍበት።
[17]“ ‘ውሳኔው በመልእክተኞች ተገልጾአል፤
ፍርዱም በቅዱሳኑ ተነግሮአል፤ ይኸውም፣
ልዑል በሰዎች መንግሥታት ሁሉ ላይ እን
ደሚገዛና እነዚህንም መንግሥታት ለወደ
ደው እንደሚሰጥ፣ ከሰዎችም የተናቁትን በላ
ያቸው እንደሚሾም፣ ሕያዋን ሁሉ ያውቁ
ዘንድ ነው።’
[18]“እኔ ናቡከደነፆር ያየሁት ሕልም ይህ
ነው፤ አሁንም ብልጣሶር ሆይ፤ በመንግሥቴ
ካሉ ጠቢባን ሁሉ አንዳቸውም ሊተረጕሙ
ልኝ ስላልቻሉ፣ ምን ማለት እንደሆነ ንገ
ረኝ። አንተ የአማልክት መንፈስ በውስጥህ
ስላለ ልትተረጕምልኝ ትችላለህ።

4፥13 ቍ10:23፤ ዘዳ33፥2፤ዳን7፥1
4፥14 አዮ24፥20፤ ሕዝ31፥12፤ማቴ3፥10
4፥16 ቍ23፥32
4፥17 ቍ2:25፤ መዝ 83፥18፤ 103፥19፤ኤር27፥5-7፤ ዳን2፥21፤ 5፥18-21፤ 11፥21፤ ሮሜ13፥1፤ማቴ 23፥12
4፥18 ቍ7-9፤ ዘፍ41፥8፡ 15:38፤ ዳን 1፥20፤5፥8:15
4፥19 ቍ5፤ዘፍ 40፥12፤41፥8፤ዳን7፥15:28፤8፥27፤ 10፥16-17

## ዳንኤል ሕልሙን ተረጐመ

[19]ከዚያም ብልጣሶር የተባለው ዳንኤል
ለጥቂት ጊዜ በጣም ታወከ፤ ሐሳቡም አስደነ
ገጠው። ንጉሡም፣ “ብልጣሶር ሆይ፤ ሕልሙም
ሆነ ትርጕሙ አያስደንግጥህ” አለው።
ብልጣሶርም እንዲህ ብሎ መለሰ፤ “ሕልሙ
ለሚጠሉህ ይሁን፤ ትርጕሙም ለጠላቶችህ!
[20]እጅግ አድጎና ጠንክሮ ያየኸው ዛፍ፣

[ሀ]13 ወይም *ጕበኛ*፤ እንዲሁም፡ ቍ17 እና 23


4፥13 *መልእክተኛ*፤ የእግዚአብሔርን መልአክ ማለት ነው፤ አግራጭ ትርጕሙን ይመ።

4፥15 *ጒቶው…ይቆይ*፤ ዛፉ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንደሚ ለመልም ያመለክታል (ቍ26ይመ)።

4፥16 *ሰባት*፤ ፍጹምነትን የሚያመለክት ቍጥር ነው። *ዓመታት*፤ ቃሉ ወቅትን ወይም ሙሉ ዓመትን (7፥25 ይመ) ያሳያል፤ ለምሳሌ በየዓመቱ የሚመጣው የጸደይ ወራት፣ ካለፈው የጸደይ ወራት ጀምሮ እስከ አዲሱ የጸደይ ወራት ድረስ ያለው ጊዜ አንድ ዓመት መሙላቱን ያመለክታል።

4፥17 *በመልእክተኞች*፤ የሕልውና መሠረት የሆነው የእግዚአብሔር ተወካዮች ናቸው (ቍ24)፤

4፥19 *ዳንኤል…በጣም ታወከ* በሕልሙ አተረጓጐም ላይ



ጫፉም እስከ ሰማይ ደርሶ በምድር ሁሉ
የሚታየው፣ 21ቅጠሎቹ የሚያምሩ፣ ፍሬ
ውም ተንዠርግጎ ለሁሉ ምግብ የሆነው፣
የዱር አራዊት መጠለያ የሆነውና በቅርን
ጫፎቹ ላይ ለሰማይ ወፎች ጐጆ መሥሪያ
ያለው፣ 22ንጉሥ ሆይ፤ ያ ዛፍ አንተ ነህ፤ ታላ
ቅና ብርቱ ሆነህ፤ ታላቅነትህ አድጎ እስከ
ሰማይ ደረሰ፤ ግዛትህም እስከ ምድር ዳርቻ
ተንሰራፋ::

23"ንጉሥ ሆይ፤ አንተ፣ 'ዛፉን ቍረጡ፣
አጥፉትም፤ በብረትና በናስ የታሰረውን
ጕቶና ሥሩን በሜዳው ሣር ላይ በብረትና
በናስ ታስሮ በመሬት ውስጥ ይቈይ፤ በሰ
ማይ ጠል ይረስርስ፤ እንደ ዱር አራዊትም
ይኑር፤ ሰባት ዓመትም ይለፍበት' እያለ
ከሰማይ የወረደውን ቅዱሱን መልእክተኛ
አየህ::

24"ንጉሥ ሆይ፤ ትርጕሙ ይህ ነው፤ ልዑሉ
በንጉሡ በጌታዬ ላይ ያወጣው ዐዋጅ ይህ
ነው፤ 25ከሕዝብ ተለይተህ ትሰደዳለህ፤ ከዱር
አራዊትም ጋር ትኖራለህ:: እንደ ከብት ሣር
ትበላለህ፤ በሰማይ ጠልም ትረሰርሳለህ፤ ልዑሉ
በሰዎች መንግሥታት ሁሉ ላይ እንደሚገ
ዛና እነዚህንም መንግሥታት ለወደደው እን
ደሚሰጥ እስክታውቅ ድረስ ሰባት ዓመታት
ያልፉብሃል:: 26የዛፉ ጕቶ ከነሥሩ እንዲ
ቀር መታዘዙ፣ ሥልጣን ከሰማይ መሆኑን
ስታውቅ መንግሥትህ እንደሚመለስልህ ያመ
ለክታል:: 27ስለዚህ ንጉሥ ሆይ፤ ምክሬን ስማ፤
ኀጢአት መሥራትን ትተህ ትክክለኛ የሆነ
ውን አድርግ፤ ክፋትን ትተህ ለተጨቈኑት
ቸርነትን አድርግ፤ ምናልባት በሰላም የምት
ኖርበት ዘመን ይራዘምልህ ይሆናል::"

### ሕልሙ ተፈጸመ

28ይህ ሁሉ በንጉሡ በናቡከደነፆር ላይ
ደረሰ፤ 29ከዐሥራ ሁለት ወራት በኋላ፣ ንጉሡ
በባቢሎን ቤተ መንግሥት ሰገነት ላይ ሲመ
ላለስ ሳለ፣ 30"በብርቱ ኀይሌ፣ ለገናናው
ክብሬ ንጉሣዊ መኖሪያ ትሆን ዘንድ ያሠራ
ኋት ታላቂቷ ባቢሎን ይህች አይደለችምን?"
አለ::

31ንግግሩን ገና ከአፉ ሳይጨርስ፣ እንዲህ
የሚል ድምፅ ከሰማይ መጣ፤ "ንጉሥ ናቡከ
ደነፆር ሆይ፤ ስለ አንተ የታወጀው ይህ
ነው፤ መንግሥትህ ከአንተ ተወስዶአል፤

4፥21 ሕዝ31፥6
4፥22 2ሳሙ12፥7፤ ኤር27፥7፤ዳን5፥18-19
4፥23 ቍ13፤ሕዝ31፥34፤ዳን5፥21፤8፥13
4፥24 ኢዮ40፥12፤ መዝ107፥40፤ኤር40፥2
4፥25 ቍ17፤ኢዮ24፥8፤ኤር27፥5፤ዳን2፥47፤5፥21
4፥26 ቍ15፤ዳን2፥37
4፥27 ዘዳ24፥13፤ 1ነገ21፥29፤መዝ41፥3፤ ምሳ28፥13፤ኢሳ55፥6-7፤ኤር29፥7፤ሕዝ18፥22
4፥28 ዘኍ23፥19
4፥30 ኢሳ10፥13፤ 13፥19፤37፥24-25፤ ዳን5፥20፤ዕን1፥11፤2፥4
4፥31 2ሳሙ 22፥28፤ ዳን5፥20
4፥32 ኢዮ9፥12
4፥33 ኢዮ24፥8፤ ዳን5፥20
4፥34 ኢዮ12፥20፤ መዝ145፥13፤ኢሳ37፥16፤ዳን2፥44፤5፥21፤6፥26፤12፥7፤ ሉቃ1፥33
4፥35 ዘዳ21፥8፤ 32፥39፤ኢዮ9፥4፤ መዝ115፥3፤135፥6፤ ኢሳ14፥24፡27፤ 40፥17፤45፥9፤ ዳን5፥21፤ዮና1፥14፤ ሮሜ9፥20
4፥36 ምሳ22፥4፤ዳን5፥18
4፥37 ዘፀ15፥2፤ ዘዳ32፥4፤ኢዮ31፥4፤40፥11-12፤መዝ18፥27፤ 33፥4-5፤34፥3፤ 119፥21፤ኢሳ13፥11፤ ዳን5፥23፤ማቴ23፥12
5፥1 ቍ30፤ 1ነገ3፥15፤ኤር50፥35፤ ዳን7፥1፤8፥1
5፥2 2ነገ24፥13፤ 2ዜና36፥10፤እስ1፥7፤ 2፥14፤ኢሳ21፥5፤ ኤር52፥19፤ዳን1፥2

32ከሕዝብ መካከል ትሰደዳለህ፤ ከዱር አራ
ዊት ጋርም ትኖራለህ፤ እንደ ከብት ሣር
ትበላለህ፤ ልዑሉ በሰዎች መንግሥት ሁሉ
ላይ ሙሉ ሥልጣን እንዳለውና እነዚህንም
መንግሥታት ለወደደው እንደሚሰጥ እስክ
ታውቅ ድረስ ሰባት ዓመት ያልፋል::"

33ወዲያውኑ በናቡከደነፆር ላይ የተነገ
ረው ሁሉ ተፈጸመ፤ ከሕዝቡ መካከል ተሰ
ደደ፤ እንደ ከብትም ሣር በላ:: የራስ ጠጕሩ
እንደ ንስር ላባና፣ ጥፍሮቹም እንደ ወፍ
ጥፍሮች እስኪያድጉ ድረስ ሰውነቱ በሰማይ
ጠል ረሰረሰ::

34ጊዜው ከተፈጸመ በኋላ፣ እኔ ናቡከደነ
ፆር ዐይኖቼን ወደ ሰማይ አነሣሁ፤ አእም
ሮዬም ተመለሰልኝ፤ ልዑሉንም ባረክሁት፤
ለዘላለምም የሚኖረውን ወደስሁት፤ ክብር
ንም ሰጠሁት::

ግዛቱ የዘላለም ግዛት ነው፤
  መንግሥቱም ከትውልድ እስከ ትውልድ
    ይኖራል::
35የምድር ሕዝቦች ሁሉ፣
  እንደ ኢምንት ይቈጠራሉ፤
በሰማይ ኀይላት፣
  በምድርም ሕዝቦች ላይ፣
የወደደውን ያደርጋል፤
  እጁን መከልከል የሚችል የለም፤
  'ምን ታደርጋለህ?' ብሎ የሚጠይቀውም
    የለም::

36አእምሮዬ እንደ ተመለሰልኝ፣ ወዲያው
ለመንግሥቴ ክብር፣ ግርማዊነቴና ሞገሴ
ተመለሱልኝ፤ አማካሪዎቼና መኳንንቴ ፈለ
ጉኝ፤ ወደ ዙፋኔም ተመለስሁ፤ ከቀድሞ
ውም የበለጠ ታላቅ ሆንሁ:: 37የሰማይ አም
ላክ የሚያደርገው ሁሉ ትክክል፣ መንገዶቹም
ሁሉ ጽድቅ ስለ ሆኑ፣ አሁንም እኔ ናቡከ
ደነፆር እርሱን አወድሰዋለሁ፤ ከፍ ከፍ አደ
ርገዋለሁ፤ አከብረዋለሁም፤ እርሱም በትዕቢት
የሚመላለሱትን ማዋረድ ይችላል::

### በግድግዳው ላይ የታየው ጽሕፈት

5 ንጉሥ ቤልሻዛር ለሺህ መኳንንቱ ታላቅ
ግብዣ አደረገ፤ በሺሁም ፊት የወ
ይን ጠጅ ይጠጣ ነበር:: 2ቤልሻዛር የወ
ይን ጠጁን እየጠጣ ሳለ፣ አባቱ* ናቡከደነ
ፆር ከኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ያመጣቸ

*2 ወይም *አያት፤ ወይም ቀዳሚ ዘር* እንዲሁም ቍ11፡13 እና 18

ገራ ተጋብቶ እንደነበረ ግልጽ ነው::

4፥25 *ልዑሉ በሰዎች መንግሥታት ሁሉ ላይ እንደ ሚገዛ...እስክታውቅ፤* አዲስ ትምህርት አገኘ (ቍ30ን ከቍ37 ጋር ያነጻጽሩ)

4፥26 *ከሰማይ፤* አይሁድ ለእግዚአብሔር የሰጡት የማዕረግ ስም ነው፤ በኋላም በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት፣ "መንግሥተ ሰማ ያት" ተብሎአል (ማቴ5፥3ን ከሉቃ6፥20 ጋር ያነጻጽሩ)::

4፥28 *ይህ ሁሉ...ደረሰ* ናቡከደናፆር የዳንኤልን ምክር ባለመስማቱ ነው::

4፥30 *ታላቂቷ ባቢሎን፤* የከተማዋ ምሽጉች፣ ቤተ መን ግሥቷና "ሃንጊንግ ጋርደንስ" (የጣራ ላይ የአትክልት ስፍራ) ለታላ ቅነቷ ማስረጃዎች ናቸው (የኢሳ13፥19 ማብ ይመ)::

4፥31 *ንግግሩን ገና ከአፉ ሳይጨርስ* ሉቃ12፥19-20 ይመ::

4፥33 *የተነገረው ሁሉ ተፈጸመ፤* ምሳ16፥18 ይመ:: *ተሰ ደደ፤* ወደ ቤተ መንግሥቱ የአትክልት ቦታዎች ሳይሆን አይቀ ርም:: በዳንኤል መሪነት የንጉሡ አማካሪዎች(2፥48-49 ይመ) አገሩን በብቃት ሳያስተዳድሩ አልቀሩም::

4፥34 *ግዛቱ... ከትውልድ እስከ ትውልድ፤* ቍ3፤6፥26፤ 7፥14 ይመ::

*4፥36፤* ኢዮ42፥10፡12 ይመ::

4፥37 *በትዕቢት የሚመላለሱትን ማዋረድ ይችላል፤* ምሳ 3፥34፤ያዕ4፥10፤1ጴጥ5፥5-6 ይመ::

*5፥1-4፤* በዚህ ዐይነት ግብዣ ላይ መጨፈርና መደለቅ እንዲሁም የአማልክትን ስም ማስደብ፣ የተለመደ እንደ ነበረ ሄሮዶቱስና ዜኖፎን የተባሉ ግሪካውያን የታሪክ ሊቃውንት ጽፈዋል::

5፥1 *ንጉሥ፤* ቤልሻዛር የናቦኒዱስ ልጅና እንደራሴው

ውን የወርቅና የብር መጠጫዎችን እርሱና
መኳንንቱ፣ ሚስቶቹና ቁባቶቹ ይጠጡባ
ቸው ዘንድ እንዲያመጡለት አዘዘ። 3ከዚያም
በኢየሩሳሌም ከነበረው ከእግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ የተወሰዱትን የወርቅ መጠጫዎች
አመጡ፤ ንጉሡና መኳንንቱ፣ ሚስቶቹና ቁባ
ቶቹም ጠጡባቸው። 4የወይን ጠጁንም እየጠጡ
የወርቅና የብር፣ የናስ፣ የብረት፣ የዕንጨ
ትና የድንጋይ አማልክትን አመሰገኑ።

5በድንገትም የሰው እጅ ጣቶች ታዩ፤ በቤተ
መንግሥቱ ውስጥ በመቅረዙ ትይዩ ባለው
ግድግዳ ልስን ላይ ጻፉ፤ ንጉሡም ይጽፍ የነበ
ረውን እጅ አየ፤ 6በዚያ ጊዜ ንጉሡ በድን
ጋጤ ተሞላ፤ ፊቱም ተለዋወጠ፤ እጆቹና እግ
ሮቹ ከዱት፤ ጒልበቶቹም ተብረከረኩ።

7ንጉሡም ድምፁን ከፍ አድርጎ አስማተ
ኞችን፣ ኮከብ ቈጣሪዎችንና[ሀ] መተተኞችን
እንዲያስገቡለት አዘዘ፤ ለባቢሎናውያኑ ጠቢ
ባን እንዲህ አላቸው፤ "ይህን ጽሕፈት አንብቦ
ትርጒሙን የሚነግረኝን ሐምራዊ መጐናጸፊያ
አለብሰዋለሁ፤ የወርቅ ሐብልም በዐንገቱ ላይ
አጠልቅለታለሁ፤ በመንግሥቴም ላይ ሦስተኛ
ገዥ ይሆናል።"

8ከዚያም የንጉሡ ጠቢባን ሁሉ ገቡ፤ ነገር
ግን ጽሕፈቱን ሊያነብም ሆነ ትርጒሙ ምን
እንደ ሆነ ለንጉሡ ሊነግር የሚችል ማንም
አልነበረም። 9ንጉሥ ቤልሻዛር ከፊት ይልቅ
ፈራ፤ ፊቱም እጅግ ተለወጠ፤ መኳንንቱም ግራ
ገብቶአቸው ተደናገጡ።

10ንግሥቲቱም[†] የንጉሡንና የመኳንንቱን
ድምፅ ሰምታ ወደ ግብዣው አዳራሽ ገባች፤
እንዲህም አለች፤ "ንጉሥ ሆይ፤ ለዘላለም ንገሥ፤
አትደንግጥ፤ ፊትህም አይለዋወጥ! 11በመ
ንግሥትህ ውስጥ የቅዱሳን አማልክት መን
ፈስ ያለበት አንድ ሰው አለ፤ ይህ ሰው
በአባትህ ዘመን እንደ አማልክት ጥበብና ማስ
ተዋል፣ ዕውቀትም የሞላበት ሆኖ ተገኝቶ
አል፤ አባትህ ንጉሥ ናቡከደነፆርም የጠንቋ
ዮች፣ የአስማተኞች፣ የኮከብ ቈጣሪዎችና
የመተተኞች አለቃ አደረገው። 12ንጉሡ
ብልጣሶር ብሎ የጠራው ይህ ዳንኤል መል
ካም መንፈስ፣ ዕውቀትና ማስተዋል ያለው
ሆኖ ተገኘ፤ ሕልምን የመተርጐም፣ እንቆ
ቅልሽን የመፍታትና የተሰወረውን የመግ
ለጥ ልዩ ችሎታም ነበረው። ስለዚህ ዳንኤ
ልን አስጠራ፤ እርሱም የጽሕፈቱን ትርጒም
ይነግርሃል።"

13ዳንኤልንም ወደ ንጉሡ አቀረቡት፤ ንጉሡም
እንዲህ አለው፤ "ንጉሡ አባቴ ከይሁዳ ማርኮ
ካመጣቸው መካከል አንዱ የሆንኸው ዳንኤል
አንተ ነህን? 14የአማልክት መንፈስ በውስጥህ
እንዳለ፣ ዕውቀት፣ ማስተዋልና ልዩ ጥበብ
እንዳለህ ሰምቻለሁ፤ 15ይህን ጽሕፈት አን
ብበው ትርጒሙ ምን እንደ ሆነ ይነግሩኝ
ዘንድ ጠቢባንና አስማተኞች በፊቴ ቀርበው
ነበር፤ ነገር ግን ሊገልጡት አልቻሉም።
16አንተ ግን መተርጐምና አስቸጋሪ የሆነ
ውን ነገር መፍታት እንደምትችል ሰምቻ
ለሁ። ይህን ጽሕፈት አንብበህ ትርጒሙን
ብትነግረኝ፣ ሐምራዊ መጐናጸፊያ ያለብ
ሱሃል፤ የወርቅ ሐብል በዐንገትህ ያጠልቁል
ሃል፤ የመንግሥት ሦስተኛ ገዥም ትደረጋለህ።"

17ዳንኤልም ለንጉሡ እንዲህ ሲል መለሰ፤
"ስጦታዎችህን ለራስህ አድርግ፤ ሽልማቶች
ህንም ለሌላ ሰው ስጥ፤ ይሁን እንጂ ጽሕ
ፈቱን ለንጉሡ አነባለሁ፤ ትርጒሙ ምን
እንደ ሆነም እነግረዋለሁ።

18 "ንጉሥ ሆይ፤ ልዑል አምላክ ለአባትህ
ለናቡከደነፆር ገናናነትንና ታላቅነትን፣ ክብ
ርንና ግርማን ሰጠው። 19ከሰጠው ታላቅ
ሥልጣን የተነሣ ሕዝቦችና መንግሥታት፣
ልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩ ሰዎችም ሁሉ
ተንቀጠቀጡለት፤ ፈሩትም። ንጉሡም ሊገ
ድል የፈለገውን ይገድል፣ ሊያድን የፈለገ
ውን ያድን፣ ሊሾም የፈለገውን ይሾም፣ ሊያ
ዋርድ የፈለገውንም ያዋርድ ነበር። 20ነገር
ግን ልቡ በትዕቢት በጸናና በእብሪት በተሞላ
ጊዜ ከዙፋኑ ተወገደ፤ ክብሩም ተገፈፈ።
21ከሰው መካከል ተሰደደ፤ የእንስሳም አእምሮ
ተሰጠው፤ ከዱር አህዮች ጋር ኖረ፤ እንደ ከብ
ትም ሣር በላ፤ ልዑል አምላክ በሰዎች መንግ
ሥታት ላይ እንደሚገዛና እነርሱንም ለወደ
ደው እንደሚሰጥ እስኪያውቅ ድረስ ሰው
ነቱ በሰማይ ጠል ረሰረሰ።

22 "ቤልሻዛር ሆይ፤ አንተ ልጁ[‡] ሆነህ
ይህን ሁሉ ብታውቅም፣ ራስህን ዝቅ አላ
ደረግህም፤ 23ይልቁንም በሰማይ አምላክ ላይ
በመታበይ፣ ራስህን ከፍ ከፍ አደረግህ፤
የመቅደሱን መጠጫዎች አስመጣህ፤ አንተና
መኳንንትህ፣ ሚስቶችህና ቁባቶችህም የወ
ይን ጠጅ ጠጣችሁባቸው፤ ማየት፣ መስ
ማት፣ ማስተዋልም የማይችሉትን የብርና
የወርቅ፣ የናስና የብረት፣ የዕንጨትና የድ
ንጋይ አማልክትን አመሰገንህ። ሕይወትህ
ንና መንገድህን ሁሉ በእጁ የያዘውን ስምባክ

5፥4 መሳ16፥24፤ አስ1፥10፤መዝ135፥15-18፤ ዕን2፥19፤ ራእ9፥20
5፥6 ኢዮ4፥15፤መዝ22፥14፤ኢሳ7፥2፤ሕዝ7፥17፤ዳን4፥5
5፥7 ዘፍ41፥8:42፤ አስ10፥3፤ኢሳ19፥3፤44፥25፤ኤር50፥35፤ ዳን2፥5-6:48፤4፥6-7
5፥8 ዘፀ8፥18፤ ዳን 2፥10፤4፥18
5፥9 መዝ48፥5፤ ኢሳ 21፥4
5፥10 ነህ2፥3፤ ዳን 3፥9
5፥11 ቍ14፤ ዘፍ41፥38፤ዳን1፥17፤2፥22:47-48
5፥12 ቍ14-16፤ ዘኍ12፥8፤ሕዝ28፥3፤ ዳን1፥7፤6፥3
5፥13 አስ2፥5-6፤ዳን6፥13
5፥14 ዘፍ41፥38፤ ዳን2፥22
5፥15 ዳን4፥18
5፥16 ዘፍ41፥15:42፤አስ5፥3፤ዳን2፥6
5፥17 2ነገ5፥16
5፥18 ኤር27፥7፤ 28፥14፤ዳን2፥37-38፤4፥36
5፥19 ዳን2፥12-13፤3፥6፤4፥22
5፥20 ኢዮ40፥12፤ ኢሳ14፥13-15፤ ኤር13፥18፤43፥10፤ ሕዝ31፥10-11፤ ዳን4፥30:31፤8፥8
5፥21 ሕዝ17፥24፤ ዳን4፥16-17:35
5፥22 ዘፀ10፥3
5፥23 ኢዮ12፥10፤ 31፥4፤መዝ115፥4-8፤ኢሳ13፥11፤14፥13፤ ኤር10፥23፤44፥9፤ 48፥26፤50፥29፤ ዕን2፥19 ሐሥ17፥28፤ ራእ 9፥20

[ሀ]7 *ወይም ከለዳውያን፤* እንዲሁም ቍ:11 [†]10 *ወይም የንጉሡ እናት*
[‡]22 *ወይም ዘሩ ወይም ምትክ*

ነበር፤ የቤልሻዛር ስም ትርጒም፣ "ቤል ሆይ፤ ንጉሡን ጠብቅ" ማለት ነው። በቍ22 ላይ ግን የናቡከደናፆር "ልጅ" ተብሎአል። "ልጅ" ለሚለው የተሰጠው የአረማይክ ቃል፣ "የልጅ ልጅ" ወይም፣ "ከእርሱ የዘር ግንድ የተገኘ" ወይም፣ "ወራሹ" ማለት ሊሆን ይችላል፤ የቍ10 ማብ ይመ፤ የቍ2 አማራጭ ትርጒም ይመ (የቍ2፡22 አማራጭ ትርጒም ይመ)።

5፥5 *በድንገትም*፤ የ4፥31፤ የ1ተሰ5፥3 ማብ ይመ።

5፥7 *በመንግሥቴም ላይ ሦስተኛ ገዥ፤* የመጀመሪያው ናቡኒዱስ ሲሆን፣ ሁለተኛው ቤልሻዛር ነበር።

5፥10 *ንግሥቲቱም*፤ አማራጭ ትርጒሙን ይመ። (1) የናቡከደነፆር ሚስት ወይም (2) የናቡከደነፆር ሴት ልጅና የናቦኒዱስ ሚስት ወይም (3) የናቡከደነፆር ልጅ ያልሆነች የናቦኒደስ ሚስት ልትሆን ትችላለች።

5፥11 *በአባትህ ዘመን*፤ ናቡከደነፆር የሞተው በ562 ዓ.ቅ.ክ ነበር፤ ይህ የቤልሻዛር ዘመን ግን 539 ዓ.ቅ.ክ. ነበር።

5፥17 *ስጦታዎችህን ለራስህ አድርግ*፤ ዘፍ14፥23 እና ማብ ይመ።

5፥21 *እስኪያውቅ ድረስ*፤ የ4፥25 ማብ ይመ።

*5፥22-23፤* ቤልሻዛር የተከሰሰባቸው ጒዳዮች ሦስት ናቸው፤ (1) ኀጢአት የሠራው ባለማወቅ ሳይሆን በዐመፅና በትዕቢት በመሆኑ (ቍ22)፤ (2) የቤተ መቅደሱን ዕቃዎች በማርከስ እግዚ

ላክ ግን አላከበርህም። [24]ስለዚህ እርሱ ጽሕ
ፈቱን የጻፈውን እጅ ላከ።

[25]"የተጻፈውም ጽሕፈት፣
'ማኔ፣ ማኔ፣ ቴቄል፣ ፋሬስ'[ገ] ይላል።
[26]"የቃሉም ትርጒም ይህ ነው፤
'ማኔ'[ነ] ማለት እግዚአብሔር
የመንግሥትህን ዘመን ቈጠረው፤
ወደ ፍጻሜም አደረሰው ማለት ነው።
[27]'ቴቄል'[ኘ] ማለት በሚዛን ተመዘንህ፤
ቀለህም ተገኘህ፣ ማለት ነው።
[28]'ፋሬስ'[አ] ማለት መንግሥትህ ተከፈለ፣
ለሜዶናውያንና ለፋርስ ሰዎች ተሰጠ
ማለት ነው።

[29]ከዚህ በኋላ በቤልሻዛር ትእዛዝ ዳንኤልን
ሐምራዊ መጐናጸፊያ አለበሱት፣ የወርቅ
ሐብል በዐንገቱ ላይ አጠለቁለት፤ የመንግ
ሥቱም ሦስተኛ ገዥ ሆኖ ተሾመ።
[30]በዚያኑ ሌሊት የባቢሎናውያን[ከ] ንጉሥ
ቤልሻዛር ተገደለ፤ [31]የሥልሳ ሁለት ዓመት
ዕድሜ የነበረው ሜዶናዊው ዳርዮስም መንግ
ሥቱን ወሰደ።

## ዳንኤል በአንበሶች ጕድጓድ ውስጥ

6 ዳርዮስ በመንግሥቱ ሁሉ ላይ እንዲገዙ
አንድ መቶ ሃያ መሳፍንትን መሾም
ፈለገ፤ [2]በእነዚህም ላይ ሦስት የበላይ አስተ
ዳዳሪዎችን አደረገ፤ ከእነርሱም አንዱ ዳንኤል
ነበረ። ንጉሡ ጕዳት እንዳይደርስበት፣ መሳፍ
ንቱ ተጠሪነታቸው ለሦስቱ የበላይ አስተዳ
ዳሪዎች እንዲሆን ተደረገ። [3]ከመሳፍንቱና
ከበላይ አስተዳዳሪዎቹ ሁሉ ይልቅ ዳንኤል
ልዩ የጥበብ መንፈስ የሞላበት ሆኖ በመ
ገኘቱ፣ ንጉሡ በመላው ግዛቱ ላይ ሊሾ
መው አሰበ። [4]በዚህ ምክንያት የበላይ አስ
ተዳዳሪዎቹና መሳፍንቱ ዳንኤል በሚያከና
ውነው የመንግሥት ሥራ ሊከሱት ሰበብ
ፈለጉ፤ ነገር ግን አላገኙበትም፤ ዳንኤል ታማኝ፣
ጠንቃቃና በሥራው እንከን የሌለበት ስለ
ነበር፣ በእርሱ ላይ ስሕተት ሊያገኙ አልቻ
ሉም። [5]እነዚህም ሰዎች፣ "ከአምላኩ ሕግ
ጋር በተያያዘ ጕዳይ ካልሆነ በቀር፣ ይህን
ሰው የምንከስበት ምንም ሰበብ አናገኝበትም"
አሉ።
[6]ከዚያም የበላይ አስተዳዳሪዎቹና መሳፍ
ንቱ በአንድነት ወደ ንጉሡ ሄደው እንዲህ
አሉ፤ "ንጉሥ ዳርዮስ ሆይ፤ ለዘላለም ንገሥ!
[7]ንጉሥ ሆይ፤ እስከ ሠላሳ ቀን ድረስ ወደ
አንተ ካልሆነ በቀር ማንም ሰው ወደ ሌላ
ሰውም ሆነ ወደ ሌላ አምላክ መጸለይ እን
ደሌለበት ንጉሡ ዐዋጅ እንዲያወጣ፣ ትእ
ዛዙም እንዲፈጸም፣ ይህንም የተላለፈ ወደ
አንበሶች ጕድጓድ እንዲጣል፣ የመንግሥት የበ
ላይ አስተዳዳሪዎች፣ መኳንንት፣ መሳፍ
ንት፣ አማካሪዎችና አገረ ገዦች ሁሉ በአን
ድነት ተስማምተዋል። [8]ንጉሥ ሆይ፤
ይህን ዐዋጅ አውጣ፤ እንደማይሻረውና እን
ደማይለወጠው የሜዶንና የፋርስ ሕግ እን
ዲሆን ትእዛዙን በጽሑፍ አድርገው።" [9]ስለ
ዚህ ንጉሥ ዳርዮስ ዐዋጁ ተጽፎ እንዲወጣ
አደረገ።
[10]ዳንኤልም ዐዋጁ እንደ ወጣ ባወቀ ጊዜ
ወደ ቤቱ ሄደ፤ መስኮቶቹ በኢየሩሳሌም
አንጻር ተከፍተው ባሉበት በሰገነቱ ቀድሞ
ያደርግ እንደ ነበረው በቀን ሦስት ጊዜ
ተንበርክኮ ጸለየ፤ አምላኩንም አመሰገነ።
[11]ሰዎቹም በአንድ ላይ ሄደው፣ ዳንኤልን
ሲጸልይና አምላኩን ሲማጸን አገኙት።
[12]ወደ ንጉሡም ሄደው፣ "ንጉሥ ሆይ፤ በሚ
ቀጥሉት ሠላሳ ቀናት ማንም ሰው ወደ
አንተ ካልሆነ በቀር ወደ ሰውም ሆነ ወደ
ማንኛውም አምላክ ቢጸልይ፣ በአንበሶች ጕድ
ጓድ ውስጥ እንደሚጣል ዐዋጅ አውጥተህ
አልነበረምን?" ሲሉ እርሱ ስላወጣው ዐዋጅ
ጠየቁት።
ንጉሡም፣ "ዐዋጁ እንደማይሻረው እንደ
ሜዶንና እንደ ፋርስ ሕግ የጸና ነው" ሲል
መለሰ።

[13]እነርሱም ንጉሡን፣ "ንጉሥ ሆይ፤ ከይ
ሁዳ ምርኮኞች አንዱ የሆነው ዳንኤል፣
አንተንም ሆነ በጽሑፍ ያወጣኸውን ዐዋጅ
አያከብርም፤ አሁንም በቀን ሦስት ጊዜ
ወደ አምላኩ ይጸልያል" አሉት። [14]ንጉሡ
ይህን በሰማ ጊዜ እጅግ አዘነ፤ ዳንኤልን ለማዳን

5፥26 ኢሳ13፥6፤ ኤር27፥7
5፥27 ኢዮ6፥2፤መዝ 62፥9
5፥28 ኢሳ13፥17፤ ኤር27፥7፤50፥41-43፤ዳን6፥28
5፥29 ዘፍ41፥42፤ ዳን2፥6
5፥30 ቍ1፤ኢሳ 21፥9፤ኤር50፥35፤51፥31
5፥31 ኢሳ13፥3፤ ኤር50፥41፤ዳን6፥1፤9፥1፤11፥1
6፥1 አስ1፥1፤ዳን 5፥31
6፥2 ዕዝ4፥22፤ ዳን2፥48-48
6፥3 ዘፍ41፥41፤አስ 10፥3፤ዳን1፥20፤5፥12-14
6፥4 ኤር20፥10
6፥5 ሐሥ24፥13-16
6፥6 ነህ2፥3
6፥7 መዝ59፥3፤ 64፥2-6፤ዳን3፥2፡6
6፥8 አስ1፥19
6፥10 1ነገ8፥29፤ መዝ95፥6፤ ማቴ6፥6፤ሐሥ5፥29
6፥11 1ነገ8፥48-50፤ መዝ55፥17፤1ተሰ5፥17-18
6፥12 አስ1፥19፤ ዳን3፥8-12
6፥13 አስ3፥8፤ ሕዝ14፥14፤ዳን2፥25
6፥14 ማር6፥26

[ገ]25 በአረማይክ ኢፋርሲን (ይኸውም ፋርሲንና ማለት ነው)
[ነ]26 ማኔ ማለት የተቈጠረ ወይም ምናን (ራሱን የቻለ አንድ የገንዘብ ክፍል)
[ኘ]27 ቴቄል ማለት የተመዘነ ወይም ሰቅል ሊሆን ይችላል።
[አ]28 ፋሬስ፡የፋርሲን ነጠላ ቍጥር ሲሆን ተከፈለ ወይም ፐርሺያ ወይም የሰቅል እኩሌታ ማለት ሊሆን ይችላል።
[ከ]30 ወይም ከለዳውያን

አብሔርን በማቃለሉ (ቍ23 ሀ)፤ እና (3) አማልክትን እንጂ እግዚአብሔርን ባለማክበሩ ነው (ቍ23 ለ)።

*5፥26-28፤* አማራጭ ትርጒሞቹን ይመ። ሦስቱ መመዘኛዎች ማለትም ምናን፣ ሰቅልና ግማሽ ምናን፣ ምናልባት ሦስቱን ነገሥታት ያመለክቱ ይሆናል፤ እነርሱም በቅደም ተከተል፦ (1)ናቡከደነፆር፣ (2) ክፉው ዮርማሮዴቅ (2ነገ25፥27፤ኤር52፥31) ወይም ናቡኒዱስ እና (3) ቤልሻዛር ናቸው።

5፥27 *በሚዛን ተመዘንህ፤* በትክክለኛው የእግዚአብሔር ሚዛን ማለት ነው (ከኢዮ31፥6፤ መዝ62፥9፤ ምሳ24፥12 ጋር ያነጻጽሩ)።

5፥28 *ለሜዶናውያንና ለፋርስ ሰዎች፤* በም2 ላይ ከተተነበዩት አራት መንግሥታት ሁለተኛው ነው። ከመጽሐፉ መግቢያ "እሳፊውቾ የተጻፈበት ጊዜ" የሚለውን ይመ።

5፥30 *በዚያኑ ሌሊት፤* ምሳ29፥1፤ ሉቃ12፥20 ይመ።

5፥31 *ሜዶናዊው ዳርዮስም፤* ቂሮስ አዲስና ተጨማሪ የባቢሎን ክፍለ ሀገሮች አድርጎ በጠቀለላቸው ግዛቶች ላይ ሹም ለነበረው ጉባሩ ለተባለ ገዥ የሰጠው ስም መሆኑ በጥንቱ የባቢሎናውያን የቅርጽ ጽሑፍ ላይ ተገልጾአል፤ በሌላም በኩል ይህ መጠሪያ በባቢሎን ምድር የራሱ የቂሮስ የዙፋን መጠሪያ ሊሆን ይችላል፤ ወይም፣ "ሜዶናዊው ዳርዮስ" የሚለው በባቢሎን ምድር የቂሮስ የዙፋን መጠሪያው ሊሆን ይችላል (የ6፥28 አማራጭ ትርጒም ይመ፤ እንዲሁም ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነውን 1ዜና 5፥26 ይመ)። *መንግሥቱን ወሰደ፤* በ2፥39 ላይ የተተነበየው የወርቅ ራስ ካሁን በኋላ አይኖርም።

6፥1 *አንድ መቶ ሃያ መሳፍንት፤* የንጉሥ ዳርዮስ ረዳቶች ናቸው።

*6፥7፤* ሜሬኞቹ፣ ዳንኤል ከሦስቱ ዐበይት ባለሥልጣኖች መካከል የበላይ መሆኑን ያውቁል ስለ ነበረ፣ ሁሉም የንጉሡ ሹማምንት ዐዋጁን እንደተቀበሉት በማስመሰል ዋሹ፤ ዳንኤል ግን ስለ ዐዋጁ ያወቀውም ሆነ የሰማው ምንም ነገር አልነበረም።

6፥10 *በኢየሩሳሌም፤* 2ዜና6፥38-39 ይመ። *በቀን ሦስት ጊዜ፤* መዝ55፥17 ይመ።

ወሰነ፤ ፀሓይ እስክትጠልቅም ድረስ የተቻ
ለውን ሁሉ አደረገ።
15ከዚያም ሰዎቹ በአንድ ላይ ወደ ንጉሡ
ቀርበው፣ "ንጉሥ ሆይ፤ በሜዶንና በፋርስ ሕግ
መሠረት፣ አንድ ንጉሥ ያወጣው ዐዋጅም ሆነ
ትእዛዝ ሊለወጥ እንደማይችል ዕወቅ" አሉት።
16ስለዚህ ንጉሡ ትእዛዝ ሰጠ፤ እነርሱም
ዳንኤልን አመጡት፤ ወደ አንበሶችም ጉድ
ጓድ ጣሉት። ንጉሡም ዳንኤልን፣ "ሁልጊዜ
የምታመልከው አምላክህ ያድንህ" አለው።
17ድንጋይ አምጥተው በጕድጓዱ አፍ
ላይ ገጠሙበት፤ ንጉሡም፣ በዳንኤል ላይ
የተፈጸመው እንዳይለወጥ በራሱ የቀለበት
ማኅተምና በመሳፍንቱ ቀለበቶች አተመ
በት። 18ንጉሡም ወደ ቤተ መንግሥቱ
ተመለሰ፤ በዚያም ሌሊት ምግብ ሳይበላ፣
የሚያዝናናውም ነገር ሳይቀርብለት ዐደረ፤
እንቅልፍም ከእርሱ ራቀ።
19በማለዳም ገና ጎሕ ሲቀድ፤ ንጉሡ
ተነሥቶ ወደ አንበሶቹ ጕድጓድ እየተጣ
ደፈ ሄደ። 20ወደ ጕድጓዱም ቀርቦ በሐዘን
ድምፅ ዳንኤልን፣ "የሕያው አምላክ አገል
ጋይ ዳንኤል ሆይ፤ ሁልጊዜ የምታመልከው
አምላክህ ከአንበሶቹ ሊያድንህ ችሎአልን?"
ብሎ ተጣራ።
21ዳንኤልም እንዲህ ብሎ መለሰ፤ "ንጉሥ
ሆይ፤ ለዘላለም ንገሥ፤ 22ንጉሥ ሆይ፤ በፊቱ
ቅን ሆኜ ስለ ተገኘሁ፣ በአንተም ፊት
በደል ስላልተገኘብኝ፣ አምላኬ መልአኩን ልኮ
የአንበሶቹን አፍ ዘጋ፤ እነርሱም አልጐዱኝም።"
23ንጉሡ እጅግ ተደሰቶ፤ ዳንኤልን ከጕድጓዱ
እንዲያወጡት አዘዘ። ዳንኤል በአምላኩ
ታምኖ ነበርና ከጕድጓድ በወጣ ጊዜ፣ አን
ዳች ጕዳት አልተገኘበትም።
24በንጉሡ ትእዛዝ፣ ዳንኤልን በሐሰት
የከሰሱትን ሰዎች፣ ከሚስቶቻቸውና ከልጆ
ቻቸው ጋር አምጥተው፣ በአንበሶቹ ጕድ
ጓድ ውስጥ ጣሏቸው፤ ገና ወደ ጕድጓዱ
መጨረሻ ሳይደርሱም፣ አንበሶቹ በጫጪ
ቋቸው፤ ዐጥንቶቻቸውንም ሁሉ ሰባበሩ።
25ከዚያ በኋላ ንጉሥ ዳርዮስ፣ በምድር
ላይ ለሚኖሩ ሕዝቦች፣ መንግሥታትና ልዩ
ልዩ ቋንቋ ለሚናገሩ ሰዎች ሁሉ እንዲህ

6፥15 አስ8፥8
6፥16 ቍ7፤
ኢዮ5፥19፤
መዝ3 7፥39-40፤
97፥10
6፥17 ማቴ27፥66
6፥18 2ሳሙ12፥17፤
አስ6፥1፤ዳን10፥3
6፥20 ዳን3፥17
6፥21 ነህ2፥3፤ዳን 3፥9
6፥22 ቍ27፤ዘፍ
32፥1፤መዝ91፥11-13፤
ዳን3፥28፤ሐሥ 12፥11፤
2ጢሞ4፥ 17፤ዕብ11፥33
6፥23 1ዜና5፥20፤
ኢሳ12፥2፤ዳን3፥27
6፥24 ዘዳ19፥18-19፤
24፥16፤2ነገ14፥6፤አስ
7፥9-10፤መዝ54፥5፤
ኢሳ38፥13
6፥25 ዳን3፥4፤4፥1
6፥26 ኢሱ2፥11፤
3፥10፤አስ8፥17፤መዝ
5፥7፤99፥1-3፤ኤር
10፥10፤ዳን2፥44፤3፥
29፤12፥7፤ራእ1፥18
6፥27 ቍ22፤ዳን
3፥29፤4፥3
6፥28 2ዜና36፥22፤
ዳን1፥21፤5፥28
7፥1 መዝ4፥4፤ኤር
36፥4፤ሕዝ40፥2፤
ዳን1፥17፤4፥13
7፥2 ሕዝ37፥9፤ ዳን
8፥8፤11፥4፤ራእ 7፥1
7፥3 ራእ13፥1
7፥4 2ሳሙ124፥11
መዝ7፥2፤ኤር4፥7፤
ሕዝ17፥3፤ራእ13፥2
7፥5 ዳን2፥39
7፥6 ራእ13፥2
7፥7 ሕዝ40፥2፤
ዳን 2፥40፤8፥7፡10፤
ራእ 12፥3

የሚል መልእክት ጻፈ፤
"ሰላም ይብዛላችሁ!
26"በማንኛውም የመንግሥቴ ግዛት ሰው
ሁሉ፣ የዳንኤልን አምላክ እንዲፈራና እን
ዲያከብር ይህን ዐዋጅ አውጥቻለሁ።
"እርሱ ለዘላለም የሚኖር፣
ሕያው አምላክ ነውና፣
መንግሥቱ አይጠፋም፤
ለግዛቱም መጨረሻ የለውም።
27እርሱ ይታደጋል፤ ያድናልም፤
በሰማይና በምድር፣
ምልክቶችንና ድንቆችን ያደርጋል፤
ዳንኤልን፣
ከአንበሶች አፍ አድኖታል።"
28ስለዚህ ዳንኤል በዳርዮስ ዘመነ መንግ
ሥትና በፋርሳዊው በቂሮስ ዘመነ መንግ
ሥት ሁሉ ኑሮው ተሳካለት።

## ዳንኤል ስለ አራቱ አራዊት ያየው ሕልም

7 የባቢሎን ንጉሥ ቤልሻዛር በነገሠ በመ
ጀመሪያው ዓመት ዳንኤል በዐልጋው ላይ
ተኝቶ ሳለ ሕልም አለመ፤ ራእይም አየ፤ የሕ
ልሙንም ዋና ሐሳብ ጻፈው።
2ዳንኤል እንዲህ አለ፤ "አራቱ የሰማይ
ነፋሳት ታላቁን ባሕር ሲያናውጡት ሌሊት
በራእይ አየሁ፤ 3እርስ በርሳቸው የማይመ
ሳሰሉ አራት ታላላቅ አራዊት ከባሕሩ ወጡ።
4"የመጀመሪያው፣ አንበሳ ይመስል ነበር፤
የንስርም ክንፎች ነበሩት፤ ክንፎቹ እስኪ
ነቃቀሉ ድረስ ተመለከትሁ፤ እንደ ሰው
በሁለት እግሩ እንዲቆም ከምድር ከፍ ከፍ
ተደረገ፤ የሰውም ልብ ተሰጠው።
5"እነሆም፤ ሁለተኛው አውሬ ድብ
ይመስል ነበር፤ በአንድ ጐኑ ከፍ ብሎአል፤
በአፉ ውስጥ በጥርሶቹ መካከል ሦስት የጐ
ድን ዐጥንቶች ነበሩት። እርሱም፤ 'ተነሥ፤
እስክትጠግብ ድረስ ሥጋ ብላ!' ተባለ።
6"ከዚያ በኋላ ተመለከትሁ፤ በፊቴ ነብር
የሚመስል ሌላ አውሬ ነበር፤ በጀርባውም
በኩል የወፍ ክንፍ የሚመስሉ አራት ክን
ፎች ነበሩት፤ ይህ አውሬ አራት ራስ ነበ
ረው፤ ለመግዛትም ሥልጣን ተሰጠው።
7"ከዚህ በኋላ በሌሊት ራእይ አየሁ፤ በፊ

6፥16 *ሁልጊዜ የምታመልከው፤* 1ቆሮ15፥58 ይመ።
6፥23 *በአምላኩ ታምኖ ነበርና፤* አንበሶቹ ክፉኛ ተርበው ነበር (ቍ24)፤ ጌታ ግን የአንበሶቹን አፍ ዘግቶ ጽኑ እምነት የነበረውን የዳንኤልን ሕይወት በማትረፍ እንደ ቸርነቱ የእምነቱን ዋጋ ከፈለው።
6፥24 *ከሚስቶቻቸውና ከልጆቻቸው ጋር፤* በፋርስ ልማድ መሠረት የተከናወነ ነበር።
7፥1፤ *ቤልሻዛር በነገሠ በመጀመሪያው ዓመት፤* በ553 ዓ.ቅ.ክ. ሳይሆን አይቀርም። በም 7 ላይ ያለው ታሪክ በም 5 ላይ ከሰፈረው ሐሳብ ይቀድማል።
7፥2 *ታላቁን ባሕር፤* መንግሥታትንና ሕዝቦቻቸውን የሚያመለክት ነው (ቍ3:17) ይመ።
7፥3 *አራዊት፤* የብዙ አሕዛብ መንግሥታት ዐርማ የዱር አራዊትና ለምግብ የሚሆኑ አዕዋፍ ምስል ነበረበት።
*7፥4-7፤* የንስር ክንፍ ያለው አንበሳ የአዲሲቷን ባቢሎን መንግሥት የሚያመለክት ኪሩብ (የዘፍ3፥24 ማብ ይመ) ነው። (የቀረው የቍ4 ክፍል በም4 ላይ እንደ ተገለጸው የናቡከደነፆርን መዋረድ የሚያንጸባርቅ ሳይሆን አይቀርም። በአንድ ጐኑ ከፍ ብሎ የሚታየው ድብ (ቍ5) በሜዶንና በፋርስ ጥምር ግዛት (ፌዴሬሽን) ውስጥ የፋርሶችን የበላይነት ያመለክታል። ሦስቱ የጐን ዐጥንቶች በፋርስ መንግሥት ድል የተደረጉትን ሦስት አገሮች ያመለክታል፤ እነርሱም:- ሊድያ (546 ዓ.ቅ.ክ.)፣ ባቢሎን (539 ዓ.ቅ.ክ.) እና ግብፅ (525 ዓ.ቅ.ክ.) ናቸው። አራት ክንፎች ያሉት ነብር (ቍ6) የትልቁን እስክንድር ፈጣን ድሎች (334-330 ዓ.ቅ.ክ.) ያመለክታሉ፤ አራቱ ራሶችም ትልቁ እስክንድር በ323 (8፥22 ይመ) በሞት በአጭር ከተቀጨ በኋላ መንግሥቱ የተከፈለባቸውን አራቱን ግዛቶች ያመለክታል፤ ግዛቶቹም:- መቄዶኒያና ግሪክ (በአንቲጳቴርና በካሳንደር አስተዳደር ሥር)፣ ትሬስና ትንሹ እስያ (በሊሲማኩስ አስተዳደር ሥር)፣ ሶሪያ (በቀዳማዊ ሰሉቂውስ አስተዳደር ሥር)፣ ፓሌስቲናና ግብፅ (በበጥሊሞስ አስተዳደር ሥር) ነበሩ። ኀይሉና ታላቅነቱ ከእርሱ በፊት ከነበሩት የላቀና ስሙም ያልታወቀው አራተኛ አውሬ (ቍ7) የሮማን መንግሥት የሚያመለክት ነው። ዐሥሩ ቀንዶቹም በ2፥41-42 ላይ ከተጠቀሱት የእግር ጣቶች ጋር ተመሳሳይነት አላቸው።

ቴም የሚያስፈራና የሚያስደነግጥ በጣም
ኀይለኛ የሆነ አራተኛ አውሬ ነበር፤ ትል
ልቅ የብረት ጥርሶች ነበሩት፤ ያደቅና ይበላ፣
የቀረውንም ሁሉ በእግሮቹ ይረጋግጥ ነበር።
ከእርሱ በፊት ከነበሩት አራዊት ሁሉ የተለየ
ሲሆን፣ ዐሥር ቀንዶች ነበሩት።
8"ስለ ቀንዶቹ ሳስብ ሳለሁ፣ ከመካከላ
ቸው አንድ ሌላ ትንሽ ቀንድ ብቅ ሲል አየሁ፤
ከመጀመሪያዎቹ ቀንዶች ሦስቱ ከፊቱ ተነ
ቃቀሉ፤ ይህም ቀንድ የሰው ዐይኖችን
የሚመስሉ ዐይኖች፣ በትዕቢትም የሚናገር
አፍ ነበረው።

9"እኔም ስመለከት፣
"ዙፋኖች ተዘረጉ፤
ጥንታዌ ጥንቱም ተቀመጠ፤
ልብሱ እንደ በረዶ ነጭ ነበረ፤
የራሱም ጠጕር እንደ ጥጥ ነጭ ነበረ፤
ዙፋኑ የእሳት ነበልባል፣
መንኰራኵሮቹም ሁሉ እንደሚነድ እሳት
ነበሩ።
10የእሳት ወንዝ፣ ከፊት ለፊቱ ፈልቆ

7፥8 መዝ12፥3፤ዳን 8፥9፤ራእ9፥7፤13፥5-6
7፥9 ቀ፦22፤1ነገ22፥19፤ 2ዜና18፥18፤ሕዝ1፥ 15፤ 10፥6፤ማቴ19፥28፤ 28፥3፤ ራእ1፥14፤4፥2፤ 20፥4
7፥10 ዘፀ32፥32፤ ዘዳ33፥2፤መዝ50፥3፤ 56፥8፤68፥17፤97፥3፤ ኢሳ30፥27፤ይሁ 1፥14፤ ራእ5፥11፤ 20፥11-15
7፥11 ራእ13፥5-6፤ 19፥20
7፥13 ዘዳ33፥26፤ ኢሳ13፥6፤ሕዝ1፥5፤ 2፥1፤ሶፎ1፥14፤ሚል 3፥2፤4፥1፤ማቴ8፥2፤ ራእ1፥7፡13፤14፥14
7፥14 መዝ72፥11፤ 102፥22፤ ኢሳ16፥5፤ ዳን2፥44፤ ማቴ28፥ 18፤ ዕብ12፥28፤ ራእ11፥15

ይፈስ ነበር፤
ሺህ ጊዜ ሺሆች ያገለግሉት ነበር፤
እልፍ ጊዜ እልፍ በፊቱ ቆመዋል፤
የፍርድ ጉባኤ ተሰየመ፤
መጻሕፍትም ተከፈቱ።
11"ቀንዱም ከሚናገረው የትዕቢት ቃል
የተነሣ፣ መመልከቴን ቀጠልሁ፤ አውሬው
እስኪታረድና አካሉ ደቆ ወደሚንበለበለው
እሳት እስኪጣል ድረስ ማየቴን አላቋረ
ጥሁም። 12ሌሎቹም አራዊት ሥልጣናቸው
ተገፎ ነበር፤ ነገር ግን ለተወሰነ ጊዜና ወቅት
በሕይወት እንዲኖሩ ተፈቀደላቸው።
13"ሌሊት ባየሁት ራእይ፣ የሰውን ልጅ
የሚመስል ከሰማይ ደመና ጋር ሲመጣ
አየሁ፤ ወደ ጥንታዌ ጥንቱ መጣ፤ ወደ
ፊቱም አቀረቡት። 14ሥልጣን፣ ክብርና
ታላቅ ኀይል ተሰጠው፤ በልዩ ልዩ ቋንቋ
የሚናገሩ ሰዎች፣ መንግሥታትና ሕዝቦች
ሰገዱለት፤ ግዛቱም ለዘላለም የማያልፍ
ነው፤ መንግሥቱም ፈጽሞ የማይጠፋ ነው።


7፥7 *ዐሥር ቀንዶች፤* የአውሬው ሥልጣን ምን ያህል ታላቅ እንደ ሆነ ያሳያል (የ1፥12 ማብ ይመ)።

7፥8 *አንድ ሌላ ትንሽ ቀንድ፤* የክርስቶስን ተቃዋሚ ወይም የክርስቶስ ተቃዋሚ ባሕርይ ያለውን የዚህን ዓለም ሥልጣን ያመለክታል። *በትዕቢትም የሚናገር አፍ፤* 11፥36፤ 2ተሰ 2፥4፤ ራእ13፥5-6 ይመ።

7፥9 *ጥንታዌ ጥንቱም፤* እግዚአብሔር ማለት ነው። *ዙፋኑ... መንኰራኵሮቹም፤* ሕዝ1፥15-21፡26-27 ይመ።

7፥10 *ሺህ...እልፍ፤* 1ሳሙ18፥7 እና ማብ ይመ።

7፥13 *የሰውን ልጅ የሚመስል፤* ራእ1፥13 ይመ። መሲሑ ለመጀመሪያ ጊዜ፣ "የሰው ልጅ" በመባል የተጠቀሰው በዚህ ስፍራ ነው፤ ይህንም ጌታ ኢየሱስ የራሱ መጠሪያ አድርጎታል። እርሱ የዓለም ሁሉ ገዥ ሆኖ በዙፋኑ ላይ ይቀመጣል፤ መንግሥቱም በሰማይም ሆነ በምድር እንደ ጸና ይኖራል እንጂ ከቶ አይደመሰስም (ቍ14)። *ከሰማይ ደመና ጋር ሲመጣ፤* ማር14፥62፤ ራእ1፥7 ይመ።



### የሕልሙ ትርጒም

15“እኔ ዳንኤል በመንፈሴ ታወክሁ፤
ያየሁትም ራእይ እጅግ አስጨነቀኝ።
16በዚያ ከቆሙት ወደ አንዱ ቀርቤ፣ የዚህ
ሁሉ እውነተኛ ትርጒም ምን እንደ ሆነ
ጠየቅሁት።

“እርሱም መለሰልኝ፤ የእነዚህንም ነገሮች
ትርጒም እንዲህ ሲል ነገረኝ፤ 17‘አራቱ ታላላቅ
አራዊት ከምድር የሚነሡ መንግሥታት ናቸው፤
18ነገር ግን የልዑሉ ቅዱሳን መንግሥቱን
ይወስዳሉ፤ ለዘላለምም ይይዙታል፤ አዎን፤
ለዘላለም ይይዙታል።’

19“ከዚያም የሚያደቅቀውንና የሚበላውን፣
የቀረውንም ሁሉ በእግሮቹ የሚረጋግጠውን፣
የብረት ጥርሶችና የናስ ጥፍሮች የነበሩትን፣
ከሌሎቹ አራዊት የተለየና እጅግ አስፈሪ
የሆነውን የአራተኛውን አውሬ እውነተኛ ትር
ጒም ማወቅ ፈለግሁ። 20ደግሞም በራሱ ላይ
ስላሉት ዐሥር ቀንዶች፣ ከመካከላቸው ብቅ
ስላለው ቀንድና ከዚሁ ቀንድ ፊት ስለ
ተነቃቀሉት ሦስት ቀንዶች፣ እንደዚሁም
ከሌሎች ስለ በለጠው የሰው ዐይኖች የሚ
መስሉ ዐይኖች፣ በትዕቢትም የሚናገር አፍ
ስለ ነበሩት ስለዚሁ ቀንድ ማወቅ ፈለግሁ።
21እነሆም፤ ይህ ቀንድ በቅዱሳን ላይ ጦርነት
ዐውጆ አሸነፋቸው፤ 22ይህም የሆነው ጥንታዌ
ጥንቱ እስኪመጣና ለልዑሉ ቅዱሳን እስኪ
ፈርድላቸው ድረስ ነበር፤ ከዚያም የልዑሉ
ቅዱሳን መንግሥቱን የሚወርሱበት ዘመን
መጣ።

23“እርሱም እንዲህ አለኝ፣ ‘አራተኛው
አውሬ በምድር ላይ የሚነሣ አራተኛው
መንግሥት ነው። ከሌሎች መንግሥታት
ሁሉ የተለየ ይሆናል፤ መላውንም ምድር
እየረገጠና እያደቀቀ ይበላል። 24ዐሥሩ
ቀንዶች ከዚህ መንግሥት የሚወጡ ዐሥር
ነገሥታት ናቸው፤ ከዚያም በኋላ ከእነርሱ
የተለየ ሌላ ንጉሥ ይነሣል፤ ሦስቱንም ነገ
ሥታት ያንበረክካል። 25በልዑል ላይ የዐ
መፅ ቃል ይናገራል፤ የልዑልንም ቅዱሳን
ያስጨንቃል፤ ለበዓላት የተመደበውን ጊዜና
ሕግን ለመለወጥ ይሞክራል፤ ቅዱሳንም ለዘ
መን፣ ለዘመናት፣ ለዘመን እኩሌታም[a] ለእ
ርሱ ዐልፈው ይሰጣሉ።

26“ነገር ግን የፍርድ ዘፋን ይዘረጋል፤
ሥልጣኑም ይወሰድበታል፤ ፈጽሞ ለዘላለም
ይደመሰሳል። 27ከዚያም ከሰማይ በታች ያሉ
መንግሥታት ልዕልና፣ ሥልጣንና ታላቅነት
ለልዑሉ ሕዝብ፣ ለቅዱሳን ይሰጣል። መንግ
ሥቱ የዘላለም መንግሥት ይሆናል፤ ገዦች
ሁሉ ያመልኩታል፤ ይታዘዙታልም።’

28“የነገሩ ፍጻሜ ይህ ነው፤ እኔም ዳንኤል
በሐሳቤ እጅግ ተጨነቅሁ፤ መልኬም ተለዋ
ወጠ፤ ይሁን እንጂ ነገሩን በልቤ ጠበቅሁት።”

### ዳንኤል በራእዩ ያየው አውራ በግና ፍየል

8 ንጉሥ ቤልሻዘር በነገሠ በሦስተኛው ዓመት፣
አስቀድሞ ከተገለጠልኝ ራእይ በኋላ እኔ
ዳንኤል ሌላ ራእይ አየሁ። 2በራእዩም፣ በኤ
ላም አውራጃ በሱሳ ግንብ ራሴን አየሁት፤ በራ
እዩም በኡባል ወንዝ አጠገብ ነበርሁ፤ 3ዐይ
ኔን አንሥቼ ስመለከት እነሆ፤ ሁለት ቀን
ዶች ያሉት አውራ በግ በወንዙ አጠገብ
ቆሞ አየሁ፤ ቀንዶቹም ረጃጅሞች ነበሩ፤
ከቀንዶቹም አንዱ ከሌላው ይረዝማል፤ የበ
ቀለው ግን ዘግይቶ ነበር። 4አውራ በጉም
ወደ ምዕራብ፣ ወደ ሰሜንና ወደ ደቡብ
በቀንዱ ሲጐሽም አየሁ። ምንም ዐይነት እን
ስሳ ሊቋቋመው አልቻለም፤ ከእጁም ሊያ
ድን የሚችል አልነበረም፤ የፈለገውን ሁሉ
አደረገ፤ ታላቅም ሆነ።

5ስለዚህም ነገር እያሰብሁ ሳለሁ፣ በዐ
ይኖቹ መካከል ትልቅ ቀንድ ያለው አውራ
ፍየል፣ መሬት ሳይነካ ምድርን ሁሉ እያቋ
ረጠ በድንገት ከምዕራብ መጣ፤ 6በወንዙ
አጠገብ ቆሞ ወዳየሁት፣ ሁለት ቀንድ ወዳ
ለው አውራ በግ ተንደርድሮ መጣበት፤ በታ
ላቅ ቍጣም መታው፤ 7እየወጋውና ሁለቱን
ቀንዶቹን እየሰበረ፣ በጭካኔ አውራውን
በግ ሲጐዳ አየሁ፤ አውራ በጉም ለመቋቋም
ጒልበት አልነበረውም። ፍየሉ በምድር ላይ
ጥሎ ረገጠው፤ አውራ በጉንም ከፍየሉ እጅ
ለማዳን የሚችል አልነበረም። 8ፍየሉም
ታላቅ ሆነ፤ ነገር ግን በኀይሉ በበረታ ጊዜ፣
ትልቁ ቀንዱ ተሰበረ፤ በቦታውም ወደ አራቱ
የሰማይ ነፋሳት የሚያመለክቱ አራት ታላ
ላቅ ቀንዶች በቀሉ።

9ከእነዚህም ቀንዶች መካከል በአንዱ
ላይ አንድ ሌላ ትንሽ ቀንድ በቀለ፤ ወደ

[a]25 ወይም ለአንድ ዓመት፣ ለሁለት ዓመት እንዲሁም ለግማሽ ዓመት
እኩሌታም

7፥15 ኢዮ4፥15፤ ዳን4፥19
7፥16 ዳን8፥16፤ 9፥22፤ዘካ1፥9
7፥18 መዝ16፥3፤ 49፥14፤ኢሳ60፥12-14፤ ሉቃ12፥32፤ዕብ12፥ 28፤ራእ2፥26፤20፥4
7፥20 ራእ13፥5-6፤ 17፥12
7፥21 ራእ13፥7
7፥22 ማር8፥35
7፥23 ዳን2፥40
7፥24 ራእ17፥12
7፥25 ኢሳ37፥23፤ ዳን2፥21፤8፥24፤11፥ 36፤12፥7፤ማር1፥15፤ ሉቃ21፥8 ሐሥ1፥ 6-7፤ራእ11፥ 2፤16፥6
7፥26 ራእ19፥20
7፥27 ዘፍ14፥18፤ 2ሳሙ7፥13፤መዝ22፥ 27፤72፥11፤86፥9፤14 5፥13፤ኢሳ14፥2፤ዳን 2፥44፤4፥34፤ሉቃ1፥ 33፤1ቆሮ6፥2፤ራእ 11፥15፤22፥5
7፥28 ኢዮ4፥15፤ መዝ13፥2፤ኢሳ21፥3፤ ዳን4፥19
8፥1 ዳን1፥17፤5፥1
8፥2 ዘፍ10፥22፤ዕዝ 4፥9፤አስ2፥8
8፥3 ዳን10፥5፤ራእ 13፥11
8፥4 ኢሳ41፥3፤ዳን 11፥3፡16
8፥7 ዳን7፥7፤ 11፥ 11፡16
8፥8 2ዜና26፥16-21፤ ዳን5፥20፤7፥2፤ራእ 7፥1
8፥9 ሕዝ20፥6፤ ዳን7፥8፤11፥16

7፥16 *በዚያ ከቆሙት ወደ አንዱ፤* የእግዚአብሔር መል
አክ ነው።

7፥18 *ቅዱሳን፤* በመሲሑ መንግሥት ዘመን የእርሱ ተከታ
ዮች እጅግ የላቀ በረከት ተካፋዮች ይሆናሉ (ማቴ19፥28-29፤
ሉቃ22፥29-30)፤ እንዲሁም ራእ1፥6፤20፥4-6 ይመ።

7፥24 *ዐሥር ነገሥታት፤* ከአራተኛው መንግሥት የሚ
ወጡ የፓለቲካ ኀይላት (የ1፥12 ማብ ይመ) ናቸው፤ ነገር ግን
ሁሉም በአንድ ጊዜ ላይነሡ ይችላሉ (2፥44 ይመ)። *ሦስቱንም ነገሥ
ታት፤* ከዐሥሩ ለማለት ነው፤ ብዙውን ጊዜ “ሦስት” ግልጽ ያልሆነ
ትንሽ ቍጥርን ያመለክታል።

*7፥25፤* የቍ8 ማብ ይመ። *ለዘመን፣ ለዘመናት፣ ለዘመን እኩሌታም፤*
አማራጭ ትርጒሙን ይመ።

7፥27 *ለቅዱሳን ይሰጣል፤* ለእነርሱ እንዲበጅ ሆኖ ነው፤
እግዚአብሔርና መሲሑ አብረው ይገዛሉ (ራእ19-22 ይመ)።

*8፥1-12፥13፤* እነዚህ ምዕራፎች በዕብራይስጥ ቋንቋ የተጻፉ
ናቸው (የ2፥4 ማብ ይመ)

8፥1 *በሦስተኛው ዓመት፤* ይህም በ551 ዓ.ቅ.ክ ገደማ
ነው። በም8 ላይ የሰፈረው ታሪክ በም5 ላይ ከሰፈረው ታሪክ
ይቀድማል።

*8፥3፤* አውራ በጉ የሜዶንንና የፋርስን መንግሥት ያመለክ
ታል (ቍ20)፤ ከሁለቱ የበጉ ቀንዶች ረጅሙ የፋርስን ገኖ መታ
የት ያመለክታል።

*8፥5፤* አውራ ፍየሉ የግሪክን መንግሥት፣ ትልቁ ቀንዱም
ትልቁ እስክንድርን ያመለክታል።

*8፥7 ሁለቱን ቀንዶቹን እየሰበረ፤* የግሪክ መንግሥትና የሜ
ዶን መንግሥት መደምሰሱን ያመለክታል።

8፥8 *ትልቁ ቀንዱ ተሰበረ፤* ትልቁ እስክንድር በብርታቱ
ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ ሳለ መሞቱን ያመለክታል (በ323 ዓ.ቅ.ክ.)።
*አራት ታላላቅ ቀንዶች፤* የ7፥4-7 ማብ ይመ።

*8፥9-12፤* “ሌላ...ቀንድ” (ቍ9) የተባለው፣ ለሦስተኛው

ደቡብ፣ ወደ ምሥራቅና ወደ መልካሚቱ
ምድር በኀይል አደገ:: 10ወደ ሰማይ ሰራዊት
እስኪደርስ ድረስ አደገ፤ ከከዋክብት ሰራዊ
ትም የተወሰኑትን ወደ ምድር ጣለ፤ ረጋገ
ጣቸውም:: 11ከሰማይ ሰራዊት አለቃ ጋር
እስኪተካከል ድረስ ራሱን ከፍ ከፍ አደረገ፤
የልዑሉንም የዘወትር መሥዋዕት ወሰደበት፤
የመቅደሱንም ስፍራ አረከሰ:: 12ከዐመፅ የተ
ነሣም የቅዱሳን ሰራዊት[m] ከዘወትሩ መሥዋዕት
ጋር ለእርሱ አልፎ ተሰጠ፤ የሚያደርገው
ሁሉ ተከናወነለት፤ እውነትም ወደ ምድር
ተጣለች::

13ከቅዱሳኑም አንዱ ሲናገር ሰማሁ፤ ሌላ
ውም ቅዱስ እንዲህ አለው፤ "ስለ ዘወትሩ
መሥዋዕት፣ ለጥፋት ምክንያት ስለ ሆነው
ዐመፅ፣ ከእግር በታች እንዲረገጡ ዐልፈው
ስለሚሰጡት መቅደስና ሰራዊት የታየው
ራእይ የሚፈጸመው መቼ ነው?"

14እርሱም፣ "እስከ ሁለት ሺህ ሦስት መቶ
ምሽቶችና ማለዳዎች ድረስ ይቈያል፤ ከዚ
ያም መቅደሱ እንደ ገና ይነጻል" አለኝ::

## የራእዩ ትርጓሜ

15እኔ ዳንኤል ራእዩን ስመለከትና ሳስተ
ውል ሳለ፣ ሰውን የሚመስል ከፊት ለፊቴ
ቆመ፤ 16ከኡባልም፣ "ገብርኤል ሆይ፤ ለዚህ
ሰው የራእዩን ትርጒም ንገረው" ብሎ የሚ
ጮኽ የሰው ድምፅ ሰማሁ::

17እኔ ወደ ቆምሁበት ስፍራ እየቀረበ ሲመጣ፣
ደንግጬ በግምባሬ ተደፋሁ፤ እርሱም፣
"የሰው ልጅ ሆይ፤ ራእዩ ስለ ዘመኑ ፍጻሜ
እንደ ሆነ አስተውል" አለኝ::

18እየተናገረኝ ሳለ፣ በምድር ላይ
በግንባሬ ተደፋሁ፤ በከባድ እንቅልፍም ተዋ
ጥሁ፤ እርሱ ግን ዳሰሰኝና በእግሮቼ አቆ
መኝ::

19እርሱም እንዲህ አለኝ፤ "ራእዩ በመጨ
ረሻው ዘመን[o] ሊሆን ያለውን የሚያመለ
ክት ስለ ሆነ፣ በኋላ በቍጣው ዘመን ምን

8፥10 ኢሳ14፥13፤ ዳን7፥7፤ራእ 8፥10፤12፥4
8፥11 ቍ25፤ሕዝ 46፥13-14፤ዳን11፥ 31፡ 36-37፤12፥11
8፥12 ኢሳ48፥1
8፥13 ዘዳ33፥2፤ኢሳ 28፥18፤ዳን4፥23፤12፥ 6፤ሉቃ21፥24፤ራእ 11፥2
8፥14 ዳን12፥11-12
8፥15 ቍ1፤ሕዝ 2፥1፤ዳን10፥16-18
8፥16 ቍ2፤ዳን7፥ 16፤9፥21፤ሉቃ1፥19
8፥17 ቍ19፤ሕዝ 1፥28፤44፥4፤ዳን2፥46፤ ዕን2፥3፤ራእ1፥17
8፥18 ሕዝ2፥2፤ዳን 10፥9፡16-18፤ዘካ4፥1
8፥19 መዝ102፥ 13፤ኢሳ10፥25፤ዕን 2፥3
8፥20 ሕዝ27፥10
8፥21 ዳን10፥20፤ 11፥3
8፥24 ዳን7፥25፤ 11፥36
8፥25 ዳን2፥34፤11፥ 21፡23፡26
8፥26 ኢሳ8፥16፤ 29፥11፤ዳን10፥1፡14፤ ራእ10፥4፤22፥10
8፥27 ኢሳ21፥3፤ዳን 2፥48፤4፥19፤10፥8
9፥1 ዕዝ4፥6፤ ዳን5፥31
9፥2 2ዜና36፥21፤ ኤር29፥10፤ ዘካ1፥12፤7፥5
9፥3 2ሳሙ13፥19፤ 2ዜና20፥3፤ነህ1፥4፤ ኤር 29፥12፤ዳን 10፥12፤ዮና3፥6

እንደሚሆን እነግርሃለሁ፤ 20ያየኸው ሁለት
ቀንዶች የነበሩት አውራ በግ፣ የሜዶንና
የፋርስን መንግሥታት ያመለክታል:: 21ጠጕ
ራሙ ፍየል የግሪክ ንጉሥ ሲሆን፣ በዐይኖ
ቹም መካከል ያለው ትልቁ ቀንድ የመጀ
መሪያው ንጉሥ ነው:: 22የተሰበረውን ቀንድ
የተኩት አራቱ ቀንዶች፣ ከመንግሥቱ የሚ
ወጡትን አራት መንግሥታት ያመለክ
ታሉ፤ ነገር ግን በኀይል አይተካከሉትም::

23"በዘመነ መንግሥታቸው በስተ መጨ
ረሻ፣ ዐመፀኞች ፍጹም እየከፉ በሚሄዱበት
ጊዜ፣ አስፈሪ ፊት ያለው አታላይ ንጉሥ
ይነሣል:: 24እጅግ ብርቱ ይሆናል፤ ነገር
ግን በገዛ ኀይሉ አይደለም:: አሠቃቂ
ጥፋት ይፈጽማል፤ የሚያደርገው ሁሉ ይከ
ናወንለታል፤ ኀያላን ሰዎችንና ቅዱሳኑን ሕዝበ
ያጠፋል:: 25እያጭበረበረ ይበለጽጋል፤ ራሱ
ንም ታላቅ አድርጎ ይቈጥራል:: በሰላም
ተደላድለን ተቀምጠናል ሲሉ፣ ብዙዎችን
ያጠፋል፤ በልዑላን ልዑልም ላይ ይነሣል፤
ይሁን እንጂ እርሱም ይጠፋል፤ ነገር ግን
በሰው ኀይል አይደለም::

26"የተሰጠህ የምሽቱና የማለዳው ራእይ
እውነት ነው፤ ነገር ግን ከብዙ ዘመን በኋላ
የሚሆነውን ስለሚያመለክት ራእዩን ዝጋው::"

27እኔ ዳንኤል ዐቅሜ ተሟጦ ነበር፤ ለብዙ
ቀናት ታመምሁ፤ ተኛሁም:: ከዚያም በኋላ
ተነሥቼ ወደ ንጉሡ ሥራ ሄድሁ:: ባየሁት
ራእይ ተደናግጬ ነበር፤ ነገሩም አልገባኝም::

## የዳንኤል ጸሎት

9የሜዶናዊው የአርጤክስስ[n] ልጅ ዳርዮስ
በባቢሎን[r] በነገሠ በመጀመሪያው ዓመት፣
2ብዘመነ መንግሥቱ በመጀመሪያው ዓመት፣
እኔ ዳንኤል ለነቢዩ ለኤርምያስ በተሰጠው
የእግዚአብሔር ቃል መሠረት፣ የኢየሩሳ
ሌም መፈራረስ ሰባ ዓመት እንደሚቈይ
ከቅዱሳት መጻሕፍት አስተዋልሁ:: 3ስለዚህ

[m]12 ወይም *ከሰማይ ሰራዊቱ* [o]19 ወይም *መጨረሻው በተወሰነው ጊዜ ስለሚሆን* [n]1 ወይም *አህሻሩስ* [r]1 ወይም *ከለዳውያን*

መንግሥት ከተሰጡት አራት ቀንዶች ከአንዱ የሚወጣ እንጂ፣ ለአራተኛው መንግሥት ከተሰጡት ዐሥር ቀንዶች (7፥8) የሚወጣ አይደለም:: የበቀለች ትንሿ ቀንድም ራብአዊውን አንጥያኮስ ኤጲፋኔዎስን ታመለክታለች:: እርሱም በዘመነ መንግሥቱ መጨረሻ (168-164 ዓ.ቅ.ክ) የአይሁድን ሃይማኖት ለማጥፋት ከፍተኛ ጥረት ያደረገ ንጉሥ ነበር:: በሌላም በኩል በ7፥8 ላይ፣ "ትንሹ" ቀንድ ከመባሉም በተጨማሪ፣ የመጨረሻው ዘመን የጨካኙ አውሬ ምሳሌ ሆኖ ተጠቅሶአል፤ አንጥያኮስ ግዛቱን፣ "መልካሚቱ ምድር" ወደ ተባለችው (ቍ9፤ ኤር3፥19 ይመ) ወደ እስራኤል ሊያስፋፋና በዚያ የሚገኘውን የእግዚአብሔርን ሕዝብ (በቍ10 ላይ "የሰማይ ሰራዊት" የተባለውን፤ ቍ12 ይመ) ሊያጠፋ ነበር፤ ብዙዎቹም ስለ እምነታቸው ሞተዋል:: አንጥያኮስ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ("ከሰማይ ሰራዊት" ቍ11) አደረገ፤ የየዕለቱ መሥዋዕትም እንዲቀር ትእዛዝ አስተላለፈ:: በመጨረሻም የይሁዳ መቃቢስ ሰራዊት ኢየሩሳሌምን መልሶ በመያዝ በ165 ዓ.ቅ.ክ በታኅሣሥ ወር ቤተ መቅደሱን እንደ ገና ለጌታ አነጻ (ቍ14):: እስከ ዛሬ ድረስ በአይሁድ ዘንድ በመከበር ላይ ያለው የቤተ መቅደስ መታደስ በዓል የተመሠረተውም በዚሁ ጊዜ ነበር::

8፥13 *ከቅዱሳኑም አንዱ፤* የእግዚአብሔር መልአክ ነበር::

*8፥14፤* ለሚቃጠል መሥዋዕትና (9፥21፤ ዘፀ29፥38-42) ለእስራኤል ሁሉ ቤዛ እንዲሆኑ የሚቀርቡት ሁለቱ መሥዋዕቶች የየዕለት ቍርባኖች ነበሩ:: 2,300 ጧትና ማታ ለ1,150 ቀኖች በተከታታይ የቀረቡትን ቍርባኖች ሊያመለክቱ ይችላሉ፤ እነዚህም ቀኖች በጌታ መሠዊያ መርከስና ይሁዳ መቃቢስ በከሴሉ 25 ቀን 165 ዓ.ቅ.ክ. ("ኪስሌቭ" በታሕሣሥና በጥር ወር መካከል ያለ የዕብራውያን ወር ነው) መሠዊያውን መልሶ በተከለበት መካከል ያለውን ጊዜ ያመለክታል:: አንጥያኮስ በኪሴሉ 25 ቀን 168 ዓ.ቅ.ክ ለባዕድ አምልኮ መሠዊያውን ያቆመው፣ የጌታ መሠዊያ በተወገደ በሁለተኛው ወር ነበር፤ ይህም በ1,150 ቀኖችና በ1,095 ቀኖች መካከል ላለው ልዩነት በቂ ምክንያት ይሆናል::

8፥17 *የሰው ልጅ፤* የሕዝ2፥1 ማብ ይመ::

*8፥23-25፤* የሲሌውሲድን ዙፋን ለመውረስ መብት ያልነበረው ራብዓዊው አንጥያኮስ በዐመፅ ሥልጣን ላይ እንደ ወጣ የሚገልጽ ክፍል ነው::

8፥25 *በልዑላን ልዑልም፤* እግዚአብሔር ራሱ ነው:: *ይጠፋል፣ ነገር ግን በሰው ኀይል አይደለም፤* አንጥያኮስ በ164 ዓ.ቅ.ክ በፋርስ ታባኤ በተባለ ስፍራ በሕመም ወይም በአደጋ ሞቶአል፤ እግዚአብሔር፣ "አጠፋው"::

9፥1 *በመጀመሪያው ዓመት፤* በ539-538 ዓ.ቅ.ክ. ማለት ነው:: *የአርጤክስስ፤* አማራጭ ትርጒሙን ይመ፤ ይህም በመጽሐፈ አስቴር ከተጠቀሰው አርጤክስስ ጋር አንድ አይደለም::

9፥2 *ለኤርምያስ...ለሰባ ዓመት፤* የኤር 25፥11-12 ማብ ይመ::

ማቅ ለብሼ፣ በራሴም ላይ ዐመድ ነስንሼ፣
በጾምና በጸሎት፣ በምልጃም ፊቴን ወደ
ጌታ ስምባክ አቀናሁ::
4ወደ ስምባኬ ወደ ስግዚስብሐር እንዲህ ብዬ
ጸለይሁ፤ ተናዘዝሁም፤
"ከሚወዱህና ትእዛዝህን ከሚፈጽሙ ሁሉ
ጋር የፍቅር ቃል ኪዳንህን የምትጠብቅ፣
ታላቅና የተፈራህ ስምባክ ጌታ ሆይ፤ 5እኛ ኀጢ
አት ሠርተናል፤ በድለናልም፤ ክፋትን አድ
ርገናል፤ ዐምፀናልም፤ ከትእዛዝህና ከሕግህ
ዘወር ብለናል:: 6ለንጉሦቻችን፣ ለልዑሎቻች
ንና ለአባቶቻችን እንዲሁም ለምድሪቱ ሕዝብ
ሁሉ በአንተ ስም የተናገሩትን አገልጋዮች
ህን ነቢያትን አልሰማንም::
7"ጌታ ሆይ፤ አንተ ጻድቅ ነህ፤ ነገር ግን
ለአንተ ታማኞች ባለመሆናችን እኛን በበተ
ንህባቸው አገሮች ሁሉ የምንገኝ የይሁዳ
ሰዎች፣ የኢየሩሳሌምና የመላው እስራ
ኤል ሕዝብ፣ በሩቅም ሆነ በቅርብ ያለን
በዚህ ቀን በኀፍረት ተከናንበናል:: 8እግዚአ
ብሔር ሆይ፤ እኛና ንጉሦቻችን፣ ልዑሎ
ቻችንና አባቶቻችን በአንተ ላይ ኀጢአት
ስለ ሠራን በኀፍረት ተከናንበናል:: 9ምንም
እንኳ በእርሱ ላይ ያመፅን ብንሆን፣ ጌታ
ስምባካችን ይቅር ባይና መሐሪ ነው:: 10እግዚ
አብሔር ስምባካችንን አልታዘዝነውም፤ ደግ
ሞም በአገልጋዮቹ በነቢያት በኩል የሰጠ
ንን ሕግ አልጠበቅንም፤ 11መላው እስራኤል
አንተን ባለመታዘዝ ሕግህን ተላልፎአል፤
ዘወርም ብሎአል::
"በአንተ ላይ ኀጢአትን ስለ ሠራን፣ በስግዚ
ስብሔር አገልጋይ በሙሴ ሕግ የተጻፈው
መሐላና ርግማን ፈሰሰብን:: 12ታላቅ ጥፋት
በእኛ ላይ በማምጣት፣ በእኛና በገዦቻችን
ላይ የተነገረውን ቃል ፈጸምህብን፤ በኢየሩ
ሳሌም ላይ የተደረገውን የሚያህል ከሰማይ
በታች ከቶ የለም::
13በሙሴም ሕግ እንደ ተጻፈው፣ ይህ
ሁሉ ጥፋት በእኛ ላይ ደረሰ፤ ሆኖም ከኀጢ
አታችን በመመለስና እውነትህን በመከተል
ከስምባካችን ከእግዚአብሔር ምሕረትን አል
ፈለግንም 14ስምባካችን እግዚአብሔር በሚያ
ደርገው ሁሉ ጻድቅ ነውና፣ በእኛ ላይ እግ
ዚአብሔር ጥፋት ከማምጣት አልተመለ
ሰም፤ እኛም አልታዘዝነውም::
15"አሁንም ሕዝብህን ከግብፅ ምድር በብ
ርቱ እጅ ያወጣህ፣ እስከዚህም ቀን ድረስ
ስምህ እንዲታወቅ ያደረግህ፣ ጌታ ስምባካ

9፥4 ዘዳ7፥9:21፤ 1ነገ8፥23:30
9፥5 ቍ11፤መዝ 106፥6፤ኢሳ53፥6፤ ኤር8፥14፤ሰቆ1፥20፤ 3፥42፤
9፥6 2ነገ18፥12፤ 2ዜና29፥6:36፥16፤ ኤር44፥5፤ያዕ5፥10፤ ራእ10፥7
9፥7 ዘዳ4፥27፤ 7፥3፤ ዕዝ9፥7:15፤ መዝ 44፥15፤ኢሳ42፥6፤ ኤር3፥25፤24፥9፤ ሕዝ 39፥23-24፤አሞ9፥9
9፥8 ነህ9፥33፤ኤር 14፥20፤ሕዝ16፥63
9፥9 ዘፀ34፥7፤ 2ሳሙ 24፥14፤ነህ9፥17፤ኤር 14፥7፤42፥12
9፥10 2ነገ17፥13-15፤ 18፥12፤ራእ10፥7
9፥11 ዘዳ11፥26፤ 13፥15፤28፥15፤2ነገ 17፥23፤22፥16፤ኢሳ 1፥4-6፤ኤር2፥29፤ 8፥8-10
9፥12 ኢሳ44፥26፤ ኤር30፥7፤44፥2:6:23፤ ሕዝ5፥9፤ዳን12፥1፤ ኢዩ2፥2፤ዘካ1፥6፤ 7፥12
9፥13 ዘዳ4፥29፤ኢሳ 9፥13፤31፥1፤ኤር2፥30
9፥14 ዘፍ18፥25፤ 2ዜና12፥6፤ነህ9፥33፤ ኤር12፥1፤18፥8፤32፥ 23፤40፥3፤44፥27
9፥15 ዘፀ3፥20፤ነህ 9፥10፤ኤር32፥21
9፥16 ዘፀ15፥17፤ መሳ5፥11፤መዝ31፥1፤ 39፥8፤48፥1፤85፥3፤ ኢሳ5፥25፤ኤር 32፥32፤ሕዝ5፥14
9፥17 ዘኍ6፥24-26፤ መዝ80፥19
9፥18 ዘዳ28፥10፤ መዝ 5፥1፤80፥14፤116፥1፤ ኢሳ37፥17፤ኤር7፥10-12፤25፥29፤ሉቃ18፥13
9፥19 1ሳሙ12፥22፤ መዝ44፥23
9፥20 ቍ3፤ዕዝ10፥1፤ መዝ145፥18፤ኢሳ58፥9
9፥21 ዘፀ29፥39፤ዳን 8፥16፤ሉቃ1፥19
9፥22 ዳን7፥16፤ 10፥14፤አሞ3፥7
9፥23 ኢሳ65፥24፤ ዳን10፥11-12:19፤ ማቴ24፥15፤ሉቃ1፥28
9፥24 ኢሳ1፥26፤ 53፥10፤56፥1፤ዕብ9፥12
9፥25 1ሳሙ13፥

ችን ሆይ፤ እኛ ኀጢአትን ሠርተናል፤ አን
ተንም በድለናል:: 16ጌታ ሆይ፤ ቀድሞ እን
ዳደረግኸው የጽድቅ ሥራህ ሁሉ፣ ከከተማህ
ከኢየሩሳሌም፣ ከቅዱሱም ተራራህ ቍጣህን
መልስ፤ በእኛ ኀጢአትና በአባቶቻችን
በደል ምክንያት ኢየሩሳሌምና ሕዝብህ በዙ
ሪያችን ባሉት ዘንድ መሣለቂያ ሆነዋል::
17"አሁንም ስምባካችን ሆይ፤ የአገልጋይህን
ጸሎትና ልመና ስማ:: ጌታ ሆይ፤ ስለ ስምህ
ስትል ፊትህን ወደ ፈረሰው መቅደስ መልስ።
18ስምባኬ ሆይ፤ ጆሮህን አዘንብለህ ስማ፤ ዐይ
ንህን ገልጠህ መጥፋታችንንና ስምህ የተጠ
ራበትን ከተማ ተመልከት:: ልመናችንን
የምናቀርበው ስለ ጽድቃችን ሳይሆን፣ ስለ
ታላቅ ምሕረትህ ነው:: 19ጌታ ሆይ፤ አድምጥ!
ጌታ ሆይ፤ ይቅር በል! ጌታ ሆይ፤ ስማ! አድ
ርግም፤ ስምህ በከተማህና በሕዝብህ ላይ
ተጠርቶአልና ስምባኬ ሆይ፤ ስለ ስምህ ስትል
አትዘግይ::"

## ሰባው ሱባዔ

20እኔም እየተናገርሁና እየጸለይሁ፣ የራ
ሴንና የሕዝቤን የእስራኤልን ኀጢአት እየ
ተናዘዝሁ፣ ስለ ቅዱስ ተራራውም እግዚአብሔር
ስምባኬን እየለመንሁ፤ 21እየጸለይሁም ሳለሁ፣
በመጀመሪያው ራእይ አይቼው የነበረው
ሰው ገብርኤል፣ በሠርክ መሥዋዕት ጊዜ
በፍጥነት እየበረረ ወደ እኔ መጣ:: 22እር
ሱም እንዲህ ብሎ አስረዳኝ፤ "ዳንኤል ሆይ፤
አሁን ጥበብንና ማስተዋልን ልሰጥህ መጥቻ
ለሁ:: 23አንተ እጅግ የተወደድህ ስለሆንህ፣
ገና መጸለይ ስትጀምር መልስ ተሰጥቶአል፤
እኔም ይህን ልነግርህ መጣሁ:: ስለዚህ መልእክ
ቱን ልብ በል፤ ራእዩንም አስተውል::
24"ዐመፃን ለማስቆም፣ ኀጢአትን ለማስወገድ፣
በደልን ለማስተስረይ፣ ዘላለማዊ ጽድቅን ለማ
ምጣት፣ ራእይንና ትንቢትን ለማተምና፣
እጅግ ቅዱስ የሆነውን ለመቀባት ስለ ሕዝ
ብህና ስለ ተቀደሰችው ከተማህ ሰባ ሱባዔ
ታውጇል::
25"ይህንን ዕወቅ፤ አስተውለውም፤ ኢየሩሳ
ሌምን ለማደስና ለመጠገን ዐዋጁ ከወጣ
በት ጊዜ ጀምሮ፣ ገዥው መሲሕ እስከሚ
መጣበት ጊዜ ድረስ፣ ሰባት ሱባዔና ሥልሳ
ሁለት ሱባዔ ይሆናል:: ኢየሩሳሌም ከጐዳ
ናዎቿና ከቅጥሮቿ ጋር ትታደሳለች፤ ይህ

24 ወይም ለማስቆም 24 ወይም እጅግ ቅዱስ ቤታ፤ ወይም እጅግ ቅዱስ የሆነውን 24 ወይም ሳምንታት እንዲሁም ቍ25 እና 26 25 ወይም ቃል 25 ወይም የተቀባው እንዲሁም ቍ26

*9፥3-19፤* የዳንኤል ጸሎት ትሕትናን (ቍ3)፣ አምልኮን (ቍ4)፣ ኑዛዜን (ቍ5-15) እና ምልጃን (ቍ16-19) ያካተተ ነው::

9፥3 *ማቅ...ዐመድ፤* የዘፍ37፥34 ማብ ይመ::

9፥11 *በ...ሕግ የተጻፈው ... ርግማን፤* ዘሌ26፥33፤ ዘዳ 28፥63-67 ይመ::

9፥18 *ስለ ታላቅ ምሕረትህ፤* እግዚአብሔር ጸሎታችንን የሚመልሰው ከጸጋው የተነሣ እንጂ ከበጎ ሥራችን የተነሣ አይደለም::

9፥20 *እየተናገርሁና፤* ኢሳ 65፥24 ይመ::

9፥24 *ሱባዔ፤* በሰባት የተከፈለ በአጠቃላይ 490 ዓመታት የሚይዝ ጊዜ ሳይሆን አይቀርም፤ ቍጥሩ ግን ቃል በቃል የሚተረጐም ሳይሆን እንደ ትእምርት የሚያገለግል ነው:: በሙሉ አማካይነት እንደሚፈጸሙ ከተጠቀሱት ስድስት ዐላማዎች የመጨረሻዎቹ ሦስቱ (ገና በምድር ላይ የሚመሠረተው ዘላለማዊ ጽድቅ፣ የራእዮችና የትንቢቶች ሙሉ በሙሉ መፈጸምና፣ "የቅዱሱ" መቀባት) በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ እንዳልተፈጸሙ የሚያምኑ አሉ::

*9፥25-27፤* ኢየሩሳሌም እንደ ገና እንድትገነባ ዐዋጅ ከወጣበት ጊዜ (ቍ25) አንሥቶ እስከ መሲሑ (የተቀባው) መምጣት ድረስ ያለው ዘመን ሥልሳ ዘጠኝ ሱባዔ (7 ሲደመር 62) ናቸው:: ሰባቶች ማለትም 483 ዓመታት (የዕዝ7፥11 ማብ ይመ) "ሰባቱ ሱባዔዎች" (በከፊል በዕዝራና በነህምያ እንደተገለጸው) የኢየሩሳሌም መልሶ ግንባታ የተጠናቀቀበትን ዘመን ሳያመለክቱ

የሚሆነው ግን በመከራ ጊዜ ነው:: 26ከሡልሳ
ሁለቱ ሱባዔ በኋላ መሲሑ ይገደላል፤ ምንም
አይቀረውም[ሠ]:: የሚመጣው አለቃ ሰዎ
ችም፣ ኢየሩሳሌምንና ቤተ መቅደሱን ይደ
መስሳል:: ፍጻሜውም እንደ ጐርፍ ይመጣል፤
ጦርነት እስከ መጨረሻው ይቀጥላል፤ ጥፋ
ትም ታውጆአል:: 27አለቃው ከብዙዎች ጋር
ለአንድ ሱባዔ[ሰ] ቃል ኪዳኑን ያጸናል፤ በሱ
ባዔውም እኩሌታ መሥዋዕትና ቍርባን
ማቅረብን ያስቀራል:: የታወጀው ፍርድ
በእርሱ ላይ እስኪፈስ ድረስ፣ ጥፋትን የሚያ
መጣ የጥፋት ርኵሰት በቤተ መቅደሱ ውስጥ[ረ]
ያቆማል[ሸ]::

## ዳንኤል በራእይ ያየው ሰው

10 የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ በነገሠ በሦስ
ተኛው ዓመት፣ ብልጣሶር ለተባለው
ዳንኤል ራእይ ታየው:: መልእክቱ እውነት
ነው፤ ስለ ታላቅ ጦርነትም የሚገልጽ ነበረ[ቀ]::
መልእክቱንም ይገነዘብ ዘንድ በራእይ ማስ
ተዋል ተሰጠው::
2በዚያ ጊዜ እኔ ዳንኤል ለሦስት ሳምንት
አለቀስሁ፤ 3ሦስቱም ሳምንት እስኪፈጸም
ድረስ ምርጥ ምግብ አልበላሁም፤ ሥጋም ሆነ
የወይን ጠጅ ወደ አፌ አልገባም፤ ቅባትም
አልተቀባሁም::
4በመጀመሪያው ወር በሃያ አራተኛው
ቀን፣ በታላቁ በጤግሮስ ወንዝ ዳር ቆሜ፣
5ቀና ብዬ ስመለከት፣ በፊቴ በፍታ የለበ
ሰና በወገቡም ላይ ምርጥ የወርቅ ቀበቶ
የታጠቀ አንድ ሰው አየሁ:: 6አካሉ እንደ
ዕንቍ፣ ፊቱ እንደ መብረቅ፣ ዐይኖቹ
እንደሚንበለበል ፋና፣ ክንዶቹና እግሮቹ
እንደ ጋለ ናስ የሚያብረቀርቁ፣ ድምፁም
እንደ ብዙ ሕዝብ ድምፅ ነበር::
7ራእዩን ያየሁት እኔ ዳንኤል ብቻ ነበርሁ፤
ከእኔ ጋር የነበሩት ሰዎች አላዩም፤ ነገር ግን
ታላቅ ፍርሀት ስለ ወደቀባቸው ሸሽተው
ተደበቁ:: 8ስለዚህ ይህን ታላቅ ራእይ እያየሁ
ብቻዬን ቀረሁ፤ ምንም ጕልበት አልነበረ
ኝም፤ መልኬ እጅጉን ገረጣ፤ ኀይልም አጣሁ::
9ከዚያም የቃሉን ድምፅ ሰማሁ፤ የቃሉንም
ድምፅ በሰማሁ ጊዜ፣ በግምባሬ በምድር
ላይ ተደፍቼ በከባድ እንቅ ልፍ ተዋጥሁ::

14፤ ዕዝ3፥3፤4፥24፤
6፥15፤ማቴ1፥17፤
ዮሐ 4፥25
9፥26 መዝ46፥8፤
ኢሳ28፥2፤53፥8፤
61፥1፤ሕዝ4፥5-6፤
ዳን 11፥10፤
ናሆ1፥8፤
ሐጌ 2፥23፤ዘካ4፥14፤
ማቴ16፥21
9፥27 ኢሳ10፥22
10፥1 ዳን1፥7፡21፤
8፥26
10፥2 ዕዝ9፥4
10፥3 ዳን6፥18
10፥4 ዘፍ2፥14፤ዳን
12፥5
10፥5 ኤር10፥9፤ሕ
ዝ9፥2፤ዳን8፥3፤ራእ
15፥6
10፥6 ዘፀ28፥20፤
ኢዮ41፥19፤ሕዝ 1፥7፤
24፤ማቴ17፥28፥3፤ራ
እ1፥15፡19፥12
10፥7 2ነገ6፥17-20፤
ሐሥ9፥7
10፥8 ዘፍ32፥34፤
ኢዮ4፥14፡15፤
ዳን 8፥27፤ዕን3፥16
10፥9 ዳን8፥18፤
ማቴ17፥6
10፥10 ኤር1፥9፤
ራእ1፥17
10፥11 ዘፍ6፥9፤
ሕዝ 2፥1፤ዳን9፥23
10፥12 ዘሌ16፥31፤
ኢሳ65፥24፤ዳን9፥3፡
20፤ማቴ14፥27
10፥13 ቍ21፤
ኢሳ 24፥21፤
ዳን12፥1፤ይሁ1፥9
10፥14 ሕዝ12፥27፤
ዳን2፥28፤8፥26፤9፥22
፤ዕን2፥3
10፥15 ሕዝ24፥27፤
ሉቃ1፥20
10፥16 ኢሳ6፥7፤
21፥3፤ኤር1፥9፤ዳን8፥
15-18
10፥17 ዳን4፥19
10፥18 ቍ16፤
ዳን 8፥18
10፥19 ኢሱ1፥9፤
መሳ6፥23፤ኢሳ6፥1-8፤
35፥4፤ዳን9፥23
10፥20 ዳን8፥21፤
11፥2

10እነሆም፣ አንድ እጅ ዳሰሰኝ፤ እየተን
ቀጠቀጥሁም በእጄና በጕልበቴ አቆመኝ፤
11እርሱም፣ "እጅግ የተወደድህ ዳንኤል ሆይ፣
አሁን ወዳንተ ተልኬአለሁና፣ የምነግርህን
አስተውል፤ ቀጥ ብለህም ቁም" አለኝ:: ይህን
ሲለኝም፣ እየተንቀጠቀጥሁ ተነሥቼ ቆምሁ::
12ደግሞም እንዲህ አለኝ፤ "ዳንኤል ሆይ፤
አትፍራ፣ ማስተዋልን ለማግኘትና በአምላክህም
ፊት ራስህን ለማዋረድ ከወሰንህበት ከመጀ
መሪያው ቀን አንሥቶ ቃልህ ተሰምቶ
አል፤ እኔም የቃልህን መልስ ይዤ መጥ
ቻለሁ:: 13ነገር ግን የፋርስ መንግሥት
አለቃ ሃያ አንድ ቀን ተቋቋመኝ፤ ከዋነኞቹ
አለቆች አንዱ የሆነው ሚካኤል ሊረዳኝ
መጣ፤ እኔም በዚያ ከፋርስ ንጉሥ ጋር ተው
ሁት:: 14ራእዩ ሊፈጸም ገና ብዙ ዘመን ስለ
ሚቀረው፣ ወደ ፊት በሕዝብህ ላይ የሚሆነውን
ልገልጽልህ አሁን ወደ አንተ መጥቻለሁ::"
15ይህን እየተናገረኝ ሳለ፣ ፊቴን ወደ ምድር
አቀረቀርሁ፤ የምናገረውንም አጣሁ:: 16ከዚ
ያም የሰው ልጅ የሚመስል[ተ] ከንፈሮቼን
ዳሰሰ፤ እኔም አፌን ከፈትሁ፤ መናገርም
ጀመርሁ፤ በፊቴ የነበረውንም እንዲህ
አልሁት፤ "ጌታዬ ሆይ፤ ከራእዩ የተነሣ ተሠ
ቃይቻለሁ፤ ኀይልም አጣሁ፤ 17ጌታዬ ሆይ፤
ጕልበቴ ከዳኝ፤ መተንፈስም አቅቶኛል፣
እኔ አገልጋይህ ከአንተ ጋር መነጋገር እንዴት
እችላለሁ?"
18እንደ ገናም፣ ሰው የሚመስለው ዳሰሰኝ፤
አበረታኝም:: 19እርሱም፣ "እጅግ የተወደ
ድህ ሰው ሆይ፤ አትፍራ፤ ሰላም ለአንተ
ይሁን፤ በርታ፤ ጽና" አለኝ::
እየተናገረኝም ሳለ፣ በረታሁና፣ "ጌታዬ
ሆይ፤ አበርትተኸኛልና ተናገር" አልሁት::
20እርሱም እንዲህ አለኝ፤ "ለምን ወደ
አንተ እንደ መጣሁ ታውቃለህ? የፋርስን
አለቃ ለመውጋት በቶሎ እመለሳለሁ፤ እኔም

ሠ26 ወይም *ይገደላል፤ ብቻውን ይቀራል፤ ወይም ይገደላል፤ ምንም አይቀረውም* ሰ27 ወይም *ሳምንት* ረ27 ወይም *በክፍ ላይ* ሸ27 ወይም *በፈረሰችው ከተማ ላይ የታወጀው ፍርድ እስኪፈስ መጨረሻው እስከሚሆን ጥፋት አምጪው በአሊያሬ በተ መቅደስ ጫፍ ላይ ይመጣል::* ቀ1 ወይም *እውነትና ከባድ ሸክም ነበር* ተ16 አብዛኛዎቹ ማሶሬቲክ የቁንት ቅጆች እንዲሁ ሲሆኑ፣ ከማሶሬ ቴክ አንድ የጥንት ቅጂ፣ የሙት ባሕር ጥቅልሎችና ሰብዓ ሊቃናት ግን *ከዚያም የሰው እጅ የሚመስል ነገር* ይላሉ::

አይቀሩም:: ሥልሳ ሁለቱ ሱባዔዎች ግን በግንባታው መጠናቀቅና በመሢሑ ወደ እስራኤል መምጣት መካከል ያለውን ጊዜ ያመለክታል:: የመጨረሻው ማለትም ሰባኛው፣ "ሰባት" ግን ኢየሩሳሌም በሚመጣው መሪ (በ70 ዓ.ም የነበረ ቲቶ) ሕዝብ እንደምትደመሰስ የተነገረውን ትንቢት በመከተል በግልጽ ተጽፎ የምናገኘው በቍ27 ላይ ብቻ ነው:: ስለዚህ ብዙዎች ሰባኛው፣ "ሰባት" የተፈጸመው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ባገለገለበት ዘመንና ከዚያም በኋላ ባለው ጊዜ ነው ይላሉ:: አንዳንዶች ግን በሥልሳ ዘጠነኛው፣ "ሰባትና" በሰባኛው፣ "ሰባት" መካከል ግልጽ ያልሆነ የጦርነትና የርኵሰት ወቅት ይሆናል ይላሉ (ቍ26):: በዚህ በኋለኛው አመለካከት መሠረት በሰባኛው፣ "ሰባት" ትንሹ ቀንድ ወይም የመጨረሻው ዘመን አውሬ፣ "የጥፋት ርኵሰት" የተባለውንና የሮሙ ቲቶ ምስያ የሆነውን ያመለክታል፤ ከአይሁድ ጋር ለሰባት ዓመት የሚጸና ቃል ኪዳን ያደርጋል፤ ሆኖም በገደቡ አጋማሽ ላይ ቃል ኪዳኑን ያፈርሳል:: የመሲሑ መገደልም (ቍ26) የክርስቶስን መስቀል ያመለክታል::

9፥27 *ቃል ኪዳኑን ያጸናል...መሥዋዕት... ያስቀራል፤* አንዳንዶቹ መሲሑ የብሉይ ኪዳኑን የመሥዋዕት ሥርዐት አስወግዶ በአዲስ ኪዳን መተካቱን ያመለክታል ሲሉ፣ ሌሎች ግን ወደ ፊት የሚመጣው የክርስቶስ ተቃዋሚ (ቍ26) ከአይሁድ ጋር በመስማማት የአምልኮ ሥርዐታቸውን የሚያበላሽ መሆኑን ያሳያል ይላሉ:: *የጥፋት ርኵሰት፤* የ11፥31 ማብ ይመ::

10፥1 *ቂሮስ በነገሠ በሦስተኛው ዓመት፤* በ539 ዓ.ቅ.ክ ባቢሎንን ካሸነፈ በኋላ ማለት ነው::

*10፥3፤* 1፥8-16 ይመ::

*10፥5-6፤* ራእ1፥12-16 ይመ::

*10፥7፤* ከሐሥ9፥7 ጋር ያነጻጽሩ::

10፥13 *የፋርስ መንግሥት አለቃ፤* ሰይጣንን ለማገልገል ሲል በፋርስ አገር ውስጥ እንቅስቃሴ የሚያደርግ ክፉ መንፈስ (ቍ20 ይመ) ነው:: መንፈሱም በመጨረሻ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በሚጠብቀው በታላቁ አለቃ በሚካኤል (12፥1) ድል ተነሥቶአል::

10፥20 *የግሪክ አለቃ፤* የቍ13 ማብ ይመ:: ይህም

ስሄድ የግሪክ አለቃ ይመጣል። 21አስቀ
ድሜ ግን በእውነት መጽሐፍ ውስጥ የተጻ
ፈውን እነግርሃለሁ፤ ከእነዚህ አለቆች ጋር
ለመዋጋት ከአለቃችሁ ከሚካኤል በስተቀር
የሚረዳኝ የለም።

11 እኔም፣ ሜዶናዊው ዳርዮስ በነገሠ
በመጀመሪያው ዓመት፣ እርሱን ለማ
ገዝና ለማበረታታት በአጠገቡ ቆሜ ነበር።

## የሰሜንና የደቡብ ነገሥታት

2"አሁንም እውነቱን እነግርሃለሁ፤ እነሆ፣
ሦስት ሌሎች ነገሥታት በፋርስ ይነሣሉ፤
አራተኛውም ከሌሎቹ ሁሉ ይልቅ እጅግ
ባለጠጋ ይሆናል። በባለጠግነቱም እጅግ
በበረታ ጊዜ፣ ሌላውን ሁሉ አሳድሞ
በግሪክ መንግሥት ላይ ያስነሣል። 3ከዚያም
በታላቅ ኀይል የሚገዛና የወደደውንም ሁሉ
የሚያደርግ ኀያል ንጉሥ ይነሣል። 4በኀይል
እየገነነ ሳለም፣ መንግሥቱ ይፈርሳል፤ ወደ
አራቱ የሰማይ ነፋሳትም ይከፋፈላል። መን
ግሥቱ ተወስዶ ለሌሎች ስለሚሰጥ፣ ለዘሩ
አይተላለፍም፤ ኀይሉም እንደ መጀመሪያው
አይሆንም።

5"የደቡቡ ንጉሥ ይበረታል፤ ነገር ግን
ከጦር አዛዦቹ አንዱ ከእርሱ የበለጠ የበ
ረታ ይሆናል፤ ግዛቱም ታላቅ ይሆናል።
6ከጥቂት ዓመታት በኋላም አንድነት ይፈ
ጥራሉ። የደቡቡ ንጉሥ ሴት ልጅ ስምምነት
ለማድረግ ወደ ሰሜኑ ንጉሥ ትሄዳለች፤ ነገር
ግን ኀይሏን ይዛ መቈየት አትችልም፤ እር
ሱም ሆነ የእርሱ ኀይል[ሀ] አይጸናም። በእነ
ዚያ ቀናት እርሷ ከቤተ መንግሥት አጃቢ
ዎቿ፣ ከአባቷና[ለ] ከደጋፊዎቿ ጋር ዐልፋ
ትሰጣለች።

7"ከዘመዶቿ አንዱ ስፍራዋን ሊይዝ ይነ
ሣል፤ የሰሜንን ንጉሥ ሰራዊት ይወጋል፤
ምሽጎቹንም ጥሶ ይገባል፤ ከእነርሱም ጋር
ተዋግቶ ድል ያደርጋል። 8አማልክታቸውን፣
የብረት ምስሎቻቸውን፣ ከብርና ከወርቅ የተ
ሠሩ የከበሩ ዕቃዎቻቸውን ይማርካል፤ ወደ
ግብፅም ይወስዳል። ለጥቂት ዓመታትም
ከሰሜኑ ንጉሥ ጋር ከመዋጋት ይቈጠባል።
9የሰሜኑም ንጉሥ፣ የደቡቡን ንጉሥ ግዛት
ይወራል፤ ነገር ግን አፈግፍጎ ወደ ገዛ አገሩ
ይመለሳል። 10ወንዶች ልጆቹም ለጦርነት
ይዘጋጃሉ፤ እስከ ጠላት ምሽግ ደርሶ የሚዋ
ጋና ሊቋቋሙት እንደማይቻል ጐርፍ የሚጠ
ራርግ ታላቅ ሰራዊት ያሰባስባሉ።

11"ከዚያም የደቡቡ ንጉሥ በቍጣ ወጥቶ
የሰሜኑን ንጉሥ ይወጋል። የሰሜኑ ንጉሥ
ታላቅ ሰራዊት ቢያሰባስብም ይሸነፋል።
12የደቡቡ ንጉሥ ብዙ ሰራዊት በሚማርክ
በት ጊዜ ልቡ በትዕቢት ይሞላል፤ በብዙ
ሺህ የሚቈጠሩ ሰዎችንም ይገድላል፤ ነገር
ግን በድል አድራጊነቱ አይጸናም።

13የሰሜን ንጉሥ ከመጀመሪያው የሚበ
ልጥ ታላቅ ሰራዊት ያሰባስባል፤ ከብዙ ዓመ
ትም በኋላ በትጥቅ እጅግ ከተደራጀ ታላቅ
ሰራዊት ጋር ተመልሶ ይመጣል።

14"በዚያም ዘመን ብዙዎች በደቡብ
ንጉሥ ላይ ይነሣሉ፤ ራእዩ ይፈጸም ዘንድ፣
ከሕዝብህ መካከል ዐመፀኛ የሆኑ ሰዎች ይነ
ሣሉ፤ ነገር ግን አይሳካላቸውም። 15የሰሜኑም
ንጉሥ መጥቶ የዐፈር ድልድል ይከባል፤
የተመሸገችውንም ከተማ ይይዛል። የደቡቡ
ሰራዊትም ለመቋቋም ኀይል ያጣል፤ የተመ
ረጡት ተዋጊዎቻቸው እንኳ ጸንተው መዋ
ጋት አይችሉም። 16ወራሪው ደስ ያሰኘውን
ያደርጋል፤ ማንም ሊቋቋመው አይችልም።
በመልካሚቱ ምድር ላይ ይገዛል፤ እርሷን ለማ

10፥21 ቍ13፤ዳን 11፥2፤ይሁ1፥9
11፥1 ዳን5፥31
11፥2 ዳን10፥20:21
11፥3 ዳን8፥4:21
11፥4 ዳን7፥2፤ 8፥22፤ኤር42፥10
11፥7 ቍ6
11፥8 ኢሳ37፥19፤ 46፥1-2፤ ኤር43፥12፤ ዳን9፥26
11፥10 ኢሳ8፥8፤ ኤር46፥8፤ዳን9፥26
11፥11 ዳን8፥7-8
11፥15 ሕዝ 4፥2
11፥16 ኢሱ 1፥5፤ ዳን 8፥4:7:9

[ሀ]6 ወይም ዘሩ [ለ]6 ወይም ከልጇና (ቫልጌትንና ሱርስትን ይመ)

መንፈሳዊ ኀይል መመታት ነበረበት።

10፥21 *በእውነት መጽሐፍ፤* 12፥1 ይመ፤ የማንኛውም ሰው ማንነትና ዕድል ፈንታው የተጻፈበት መለኮታዊ የባሕር መዝገብ ሳይሆን አይቀርም (የዘፀ32፥32 ማብ ይመ)።

11፥1 *ሜዶናዊው ዳርዮስ፤* የ5፥31 ማብ ይመ።

11፥2 *ሦስት ሌሎች ነገሥታት፤* እነርሱም ካምቢሲስ (530-522 ዓ.ቅ.ክ)፣ ጽሱዶ ስሜርዲስ ወይም ጋውማታ (522) እና ቀዳማዊ ዳርዮስ (522-486) ናቸው። *አራተኛውም፤* በ480 ዓ.ቅ.ክ ግሪክን በኀይል ለመቈጣጠር የሞከረውን ቀዳማዊ ጠረክሲስን ያመለክታል (486-465)፤ የአስ 1፥1 ማብ ይመ።

11፥3 *ኀያል ንጉሥ፤* ትልቁ እስክንድር ነው(336-323)።

11፥4 *አራቱ...ነፋሳት፤* የ7፥4-7 ማብ ("አራት ራሶች") ይመ።

11፥5 *የደቡቡ ንጉሥ፤* የግብፁ ቀዳማዊ በጥሊሞስ ሶተር (323-285) ነው። *ከጦር አዛዦቹ አንዱ፣* ቀዳማዊ ሰሉ ቂውስ ኒካቶር (311-280) ነው። *ግዛቱም፤* የመጀመሪያ ግዛቱ ባቢሎን ብቻ ነበረች፤ በኋላ ግን ወደ ምሥራቅና ወደ ምዕራብ ዘልቆ በመግባት፣ ግዛቶችን ወደ ራሱ መንግሥት ጨምሮአል።

11፥6 *የደቡብ ንጉሥ ሴት ልጅ፤* የግብፁ የዳግማዊ በጥሊሞስ ፊላዴልፈስ (285-246 ዓ.ቅ.ክ.) ልጅ በርኒቄ ናት። *ስምምነት፤* በበርኒቄና በአንጥያኮስ ጋብቻ የተጠናከረ የወዳጅነት ውል ነው። *ወደ ሰሜኑ ንጉሥ፤* የሶሪያው ዳግማዊ አንጥያኮስ ቴኦስ (261-246) ነው። *ኀይሏን ይዛ መቈየት አትችልም፤ እርሱም... አይጸናም፤* የአንጥያኮስ የቀድሞ ሚስት የነበረችው ላኦዲቀ፤ በርኒቄንና አንጥያኮስን በተንኰሏ አስገደለቻቸው። *ከአባቷና፤* የበርኒቄ አባት በጥሊሞስም በዚያው ዓመት ሞተ።

11፥7 *ከዘመዶቿ አንዱ፤* ላኦዲቄን የገደለ የበርኒቄ ወንድም የግብፁ ሣልሳዊ በጥሊሞስ ኤዌርጌቴስን (246-221 ዓ.ቅ.ክ) ማለቱ ነው። *የሰሜንን ንጉሥ፤* የሶርያው ዳግማዊ ካሊኒከስ (246-226) ነው። *ምሽጎቹንም፤* (1)የአንፆኪያ ወደብ የነበረችው ሴሌውቅያ (ሐሥ13፥4 ይመ) ወይም (2) አንጾኪያ ራስዋ ልት ሆን ትችላለች።

11፥8 *አማልክታቸውን፤* የፋርሱ ንጉሥ ካምቢሲስ በ525 ዓ.ቅ.ክ ግብፅን ካሸነፈ በኋላ፣ ወደ አገሩ የወሰዳቸው የሶርያና የግብፅ አማልክት ምስሎች ናቸው።

11፥10 *ወንዶች ልጆቹም፤* ሣልሳዊ ስሉቂውስ ቄራውኒስ (226-223) እና ሣልሳዊው አንጥያኮስ {(ታላቁ አንጥያኮስ የተባለው ) (223-187)} የዳግማዊ ስሉቂውስ ልጆች ናቸው። *ጠላት ምሽግ፤* በደቡብ ፓሌስቲና ራፋ በተባለ ስፍራ የሚገኝ የበጥሊሞስ ምሽግ ነው።

11፥11 *የደቡቡ ንጉሥ፤* የግብፁ ራብዓዊ በጥሊሞስ ፊሎጳተር (221-203) ነው። *የሰሜኑን ንጉሥ፤* ሣልሳዊው አንጥያኮስን ነው። *ይሸነፋል፤* ራፋ ላይ በ217 ማለት ነው።

11፥12 *በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ሰዎችንም ይገድላል፤* ፓሊቢየስ የተባለው ታሪክ ጸሓፊ፣ አንጥያኮስ ራፋ ላይ ዐሥር ሺህ እግረኛ ወታደሮች እንደተገደሉበት ገልጾአል።

11፥14 *በደቡብ ንጉሥ፤* የግብፁ አምስተኛው በጥሊሞስ ኤጲፋኔዎስ (203-181)ነው። *ከሕዝብህም መካከል ዐመፀኛ የሆኑ ሰዎች፤* ከአንጥያኮስ ሰራዊት ጋር የተቀላቀሉትን አይሁድ ያመለክታል፤ *አይሳካላቸውም፤* የበጥሊሞስ ሰራዊት መሪ የነበረው ጀኔራል ስኮፓስ በ200 ዓ.ቅ.ክ የዐማፂያኑን ቡድን ደመሰሰ።

11፥15 *የተመሸገችውንም ከተማ፤* ሲዶና የተባለችው የሜድትራኒያን የባሕር ወደብ ናት።

11፥16 *ወራሪው፤* በ197 ዓ.ቅ.ክ. ፓሊስቲናን በቍጥጥሩ ሥር

ጥፋትም ኀይል ይኖረዋል:: 17በመንግሥቱ
ያለውን ሰራዊት ሁሉ ይዞ ለመምጣት ይወ
ስናል፤ ከደቡብም ንጉሥ ጋር ይስማማል፤ ይህ
ንም መንግሥት ለመጣል ሴት ልጁን ይድ
ርለታል፤ ይሁን እንጂ ዕቅዱ[*] አይሳካለትም፤
ያሰበውም ነገር አይጠቅመውም:: 18ከዚህም
በኋላ በባሕር ጠረፍ ወዳሉት አገሮች ፊቱን
በመመለስ ብዙዎቹን ይይዛል፤ ነገር ግን
አንድ አዛዥ ትዕቢቱን ያከሽፍበታል፤ በራ
ሱም ላይ ይመልስበታል:: 19በገዛ አገሩ ወዳ
ሉት ምሽጎችም ፊቱን ይመልሳል፤ ነገር ግን
ተሰናክሎ ይወድቃል፤ ዳግምም አይታይም::
20"በእርሱ ቦታ የሚተካውም የመንግሥቱን
ክብር ለማስጠበቅ ግብር አስገባሪ ይልካል፤
ይሁን እንጂ በቍጣ ወይም በጦርነት ሳይ
ሆን በጥቂት ዓመታት ውስጥ ይገደላል::
21"በእርሱም ፋንታ የተናቀ ሰው ይነግ
ሣል፤ ንጉሣዊ ክብርም አይሰጠውም፤ ሕዝቡ
በሰላም ተቀምጦ ሳለ በተንኰል መንግሥ
ቱን ይይዛል:: 22ከፊቱ የሚቆመውን ታላቅ
ሰራዊት፣ የቃል ኪዳኑንም አለቃ ሳይቀር
ይደመስሳል:: 23ከእርሱ ጋር ስምምነት ከተደ
ረገ በኋላ የማታለል ሥራውን ይሠራል፤ ከጥ
ቂት ሰዎች ጋር ሥልጣን ይበቃል:: 24የበለ
ጸጉትን ክፍለ አገሮች በሰላም ሳሉ በድን
ገት ይወርራቸዋል፤ አባቶቹም ሆኑ አያቶቹ
ያላደረጉትን ነገር ያደርጋል፤ ይከናወንለታ
ልም፤ ብዝበዛውን፣ ምርኮውንና የተገኘውን
ሀብት ሁሉ ለተከታዮቹ ያካፍላቸዋል፤ ምሽጎ
ችን ለመጣል ያሤራል፤ ይህን የሚያደርገውም
ለጥቂት ጊዜ ብቻ ነው::
25"ታላቅ ሰራዊት አደራጅቶ ኀይሉንና
ብርታቱን በደቡብ ንጉሥ ላይ ያነሣሣል፤
የደቡብ ንጉሥም ቍጥሩ እጅግ ብዙ የሆነ
ኀያል ሰራዊት ይዞ ጦርነትን ያውጃል፤
ነገር ግን ከተዶለተበት ሤራ የተነሣ መቋቋም
አይችልም:: 26ከንጉሥ ማእድ አብረውት
ሲበሉ የነበሩት ሊያጠፉት ያሤራሉ፤ ሰራ
ዊቱም ይደመሰሳል፤ ብዙዎቹም በጦርነት
ይወድቃሉ:: 27ልባቸው ወደ ክፋት ያዘነበ
ለው ሁለቱ ነገሥታት፣ በአንድ ገበታ አብ
ረው ይቀመጣሉ፤ እርስ በርሳቸውም ሐሰ
ትን ይነጋገራሉ፤ ነገር ግን የተወሰነው ጊዜ

*17 ወይም እርሷ

11፥17 መዝ20፥4፤ ኢሳ 66፥19፤ኤር 25፥22፤ሆሴ 12፥14
11፥19 መዝ27፥2፤ 37፥36፤46፥2፤ሕዝ 26፥21
11፥20 ኢሳ60፥17
11፥21 ዳን4፥17፤ 8፥25
11፥22 ኢሳ28፥15፤ ዳን8፥10-11
11፥23 ዳን8፥25
11፥24 ነህ9፥25
11፥27 መዝ12፥2፤ 64፥6፤ ኤር9፥5፤ዕን 2፥3

ያደረገውን አንጥያኮስን ነው:: *በመልካሚቱ፤* የ8፥9-12 ማብ ይመ::

11፥17 *ሴት ልጁን ይድርለታል፤* አንጥያኮስ በ194 ዓ.ቅ.ክ ሴት ልጁን ቀዳማዊት ክሊዮፓትራን ለአምስተኛው በጥሊሞስ ዳረለት::

11፥18 *በባሕር ጠረፍ ወዳሉት አገሮች፤* ትንሿ እስያና ግሪክ ሳይሆኑ አይቀሩም:: *አዛዥ፤* በ190 ዓ.ቅ.ክ በትንሿ እስያ በምትገኘው ማግኔዚያ በተባለች ስፍራ አንጥያኮስን ድል ያደረገውን የሮማ ቆንሲል ሉሲዮስ ቆርኔሌዎስ ሲፒዮ አስያቲኮስን ያመለክታል::

11፥19 *ተሰናክሎ ይወድቃል፤* አንጥያኮስ በ187 ዓ.ቅ.ክ. ኤሊ ማይዝ በተባለ ስፍራ ቤተ መቅደስን በመዝረፍ ላይ እንዳለ ተገደለ::

11፥20 *በእርሱ ቦታ የሚተካውም፤* የታላቁ አንጥያኮስ ወንድ ልጅና ተተኪው ራብዓዊው ሴሌቂውስ ፊሎፓተር (187-175 ዓ.ቅ.ክ) ነው:: *ግብር አስገባሪ፤* የሴሌቂውስ የገንዘብ ሚኒስትር የነበረውን ሄሊዮዶረስን ያመለክታል:: *ይገደላል፤* ሴሉቂውስ የተገደለው ሂሊዮደረስ በጠነሰሰው ሤራ ነበር::

11፥21 *የተናቀ ሰው፤* የሴሉቂውስ ታናሽ ወንድም የነበረውን ራብዓዊውን አንጥያኮስ ኤጲፋኔስን 175-164 ዓ.ቅ.ክ ለማለት ነው:: *ንጉሣዊ ክብርም አይሰጠውም፤* አንጥያኮስ ሥልጣን የጨበጠው ዙፋን ለመውረስ ባለ መብት የሆነውና በኋላም ቀዳማዊ ዲሜጥሮስ የተባ ለው የሴሉቆውስ ልጅ ገና ወጣት እያለ ነበር:: *መንግሥቱን፤* የሶሪያና የፓ ሌስቲና የጋራ መንግሥት ነው::

11፥22 *የቃል ኪዳኑንም አለቃ፤* በ170 ዓ.ቅ.ክ የተገደለውን ሊቀ ካህናት ሣልሳዊ አንያስን ወይም ለዚህ ሐረግ የተሰጠው የዕብራይስጥ ትርጕም፣ "የጥምር መንግሥት አለቃ" የሚል ከሆነ ሐረጉ ከ181-146 በግብፅ የነበረውን 6ኛውን በጥ ሊሞስ ፊሎሜትርን ሳያመለክት አይቀርም::


11፥24 *የበለጸጉትን ክፍለ አገሮች፤* ፓለስቲናን ወይም ግብፅን ለማ ለት ነው:: *ምሽጎችን፤* በግብፅ የነበሩትን ያመለክታል::

11፥25 *በደቡብ ንጉሥ፤* 6ኛው በጥሊሞስን ማለት ነው::

11፥26 *ሰራዊቱም፤* የበጥሊሞስን ሰራዊት ማለት ነው::

11፥27 *ሁለቱ ነገሥታት፤* አንጥያኮስንና በአንጥያኮስ ጥበቃ

## በጥሊሞስና ሴሊውሲድ



ገና ስለ ሆነ አይከናወንላቸውም:: [28]የሰሜን
ንጉሥ ብዙ ሀብት ይዞ ወደ ገዛ አገሩ ይመለ
ሳል፤ ነገር ግን ልቡ በተቀደሰው ኪዳን ላይ
ይነሣሣል፤ ክፉ ነገርም ያደርግበታል፤ ከዚ
ያም ወደ ገዛ አገሩ ይመለሳል::
[29]"በተወሰነው ጊዜ ደቡቡን እንደ ገና
ይወራል፤ በዚህ ጊዜ ግን ውጤቱ ከበፊቱ
የተለየ ይሆናል:: [30]የኪቲም° መርከቦች
ይቃወሙታል፤ ልቡም ይሸበራል:: ወደ ኋላም
ይመለሳል፤ ቍጣውን በተቀደሰው ኪዳን
ላይ ያወርዳል፤ ተመልሶም የተቀደሰውን
ኪዳን የተውትን ይንከባከባል::
[31]"የጦር ሰራዊቶቹም ቤተ መቅደሱንና
ቅጥሩን ያረክሳሉ፤ የዘወትሩንም መሥዋዕት
ያስቀራሉ፤ በዚያም ጥፋትን የሚያመጣውን
የጥፋት ርኩሰት ይተክላሉ፤ [32]ኪዳኑን የሚ
ተላለፉትን በማታለል ያስታል፤ ስምባላካቸ
ውን የሚያውቁ ሕዝብ ግን ጸንተው ይቃወ
ሙታል፤ ርምጃም ይወስዳሉ::
[33]"ለጊዜው በሰይፍ ቢወድቁም፣ ቢቃጠ
ሉም፣ ቢማረኩና ቢዘረፉም፣ ጥበበኛ የሆኑ
ሰዎች ብዙዎችን ያስተምራሉ:: [34]በሚወድቁ
በት ጊዜ መጠነኛ ርዳታ ያገኛሉ፤ እውነተኛ
ያልሆኑ ብዙ ሰዎችም ይተባበሯቸዋል:: [35]ጥበ
በኛ ከሆኑ ሰዎች አንዳንዶቹ ይሰናከላሉ፤
ይህም እስከ ፍጻሜ ዘመን ድረስ የጠሩ፣ የነጠ
ሩና እንከን የሌለባቸው ይሆኑ ዘንድ ነው፤ የተ
ወሰነው ጊዜ ገና አልደረሰምና::

## ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ንጉሥ

[36]"ንጉሡ ደስ እንዳለው ያደርጋል፤ ከአማል
ክት ሁሉ በላይ ራሱን እጅግ ከፍ በማድረግ
በአማልክት ስምባክ ላይ ተሰምቶ የማይታወቅ
የስድብ ቃል ይናገራል፤ የቍጣውም ዘመን
እስኪፈጸም ድረስ ይሳካለታል፤ የተወሰነው ነገር
ሁሉ መሆን አለበትና:: [37]ሴቶች ለሚወ
ዱትም ሆነ ለአባቶቹ አማልክት ክብርን
አይሰጥም፤ ማንኛውንም አምላክ አያከብ
ርም፤ ነገር ግን ራሱን ከእነዚህ ሁሉ በላይ
ከፍ ከፍ ያደርጋል:: [38]በእነርሱም ምትክ
የምሽጎችን አምላክ ያከብራል፤ አባቶች የማ
ያውቁትን አምላክ በወርቅ፣ በብር፣ በከ

11፥30 ዘፍ10፥4፤ 1ሳሙ17፥32፤ ኢዮ 15፥13
11፥31 ኤር19፥4፤ ዳን8፥11-13፤9፥27፤ ሆሴ3፥4፤ማቴ24፥15፤ ማር 13፥14
11፥32 ሚክ5፥7-9
11፥33 ዳን12፥3፤ ሚል2፥7፤ማቴ24፥9፤ ዮሐ16፥2፤ዕብ 11፥32-38
11፥34 ማቴ7፥15፤ ሮሜ16፥18
11፥35 ኢዮ28፥1፤ መዝ78፥38፤ኢሳ48፥10፤ዳን12፥10፤ዘካ13፥9፤ዮሐ15፥2
11፥36 ዘዳ10፥17፤ ኢሳ10፥25፤14፥13-14፤26፥20፤ሕዝ35፥13፤ ዳን7፥25፤8፥11-12፤ 24፤25፤2ተሰ2፥4፤ይሁ 1፥16፤ራእ13፥5-6

°30 *ወይም የምዕራብ ባሕር ዳር አገሮች*

ሥር የነበረውን በጥሊሞስን ማለቱ ነው::

11፥28 *በተቀደሰው ኪዳን ላይ፤* በ169 ዓ.ቅ.ክ አንጥያኮስ በኢየሩሳሌም የነበረውን ቤተ መቅደስ ከዘረፈ በኋላ ጠባቂዎችን በዚያ አቆመ፤ ብዙ አይሁድንም በከተማው ውስጥ ጨፈጨፈ::

11፥30 *የኪቲም መርከቦች፤* በፓፒሊየስ ላይነስ ትእዛዝ የሚመሩ የሮማ ግዛት መርከቦች ናቸው:: *የተቀደሰውን ቃል ኪዳን የተዉትን፤* ሃይማኖታቸውን የካዱ አይሁድን ማለት ነው(ቍ32 ይመ)::

11፥31 *የጥፋት ርኵሰት፤* 9፥27፤12፥11 ይመ፤በ168 ዓ.ቅ.ክ ዚየስ ኦሊምፒየስ ለተባለው የጣዖት አምላክ የሚሆን መሠዊያ በአንጥያኮስ ኤጲፋኔስ ተተከለ:: ይህም ጌታ ኢየሱስ በትምህርቱ ያመለከተውን እንዲሁም ወደ ፊት በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚተከለውን የጥፋት ርኵሰት የሚያሳይ ነው (የማቴ 24፥15 ማብ ይመ፤ እንዲሁም ሉቃ21፥20 ይመ)::

11፥33 *ጥበበኛ የሆኑ ሰዎች፤* ሐሲዲም ተብለው የሚታወቁና ቀና የሆኑ የአይሁድ ንቅናቄ አለቆች ናቸው:: *በሰይፍ ቢወድቁም፣ ቢቃጠሉም፣ ቢማረኩና ቢዘረፉም፤* ዕብ 11፥36-38 ይመ::

11፥34 *መጠነኛ ርዳታ፤* ከኢየሩሳሌም ሰሜን ምዕራብ 27 ኪሎ ሜትር ርቃ በምትገኘውና ሞዴይን በተባለች ስፍራ፣ በማታትያስና በልጁ በይሁዳ መቃቢስ መሪነት በ168 ዓ.ቅ.ክ በተካ ሄደው የደፈጣ ውጊያ የተገኘውን የመጀመሪያ ድል የሚያስታውስ ነው፤ ቤተ መቅደሱም በታኅሣሥ ወር በ165 ዓ.ቅ.ክ እንደ ገና ከርኵሰት ነጻ::

11፥35 *እስከ ፍጻሜ ዘመን ድረስ፤* ቍ40፤12፥4፡9 ይመ:: ዳንኤል ስለ አንጥያኮስ ኢጲፋኔስ የጀመረውን ትንቢት እዚህ ላይ በማጠቃለል፣ ወደ ፊት ከብዙ ዘመን በኋላ ሊመጣ ስላለው ነገር መተንበይ ይጀምራል::

*11፥36፤* ከዚህ ጀምሮ እስከ ም11 መጨረሻ ድረስ (የ7፥8፤ 9፥27 ማብ ይመ)፣ ስለ ክርስቶስ ተቃዋሚ በዝርዝር ይናገራል፤ የክፍሉ ሐሳብ ከአንጥያኮስ ኤጲፋኔዎስ ታሪክ ጋር አይገጣጠምም፤ 2ተሰ2፥4 ይመ፤ ከራዕ13፥5-8 ጋር ያነጻጽሩ::


11፥37 *ሴቶች ለሚወዱትም፤* ብዙውን ጊዜ ተሙዝ (የሕዝ 8፥14 ማብ ይመ) ወይም መሲሑ ተብሎ ይተረጐማል::

ታላቁ እስክንድር በ323 ዓ.ቅ.ክ. ከሞተ በኋላ የጦር መሪዎቹ ግዛቱን አራት ቦታ ከፋፈሉት፤ ግብፅ በበጥሊሞስ ሥር ሶሪያ ደግሞ በሴሌውሲድ ሥር ሆኑ:: ፍልስጥኤም ከ323 እስከ 198 ዓ.ቅ.ክ. በበጥሊሞስ ሥርወ መንግሥት ቍጥጥር ነበረች፤ በመቀጠልም ከ198 እስከ 142 ዓ.ቅ.ክ. በሶርያ ሴሌውሲድ ግዛት ሥር ሆነች::

ከእስክንድር በመቀጠል ገዥ የነበረው በግዛቱ ላይ የበላይ ለመሆን ከፉኛ ታግሎ ነበር:: በመጀመሪያ ቀዳማዊ በጥሊሞስ የራሱ የሆኑትን፣ ከፍተኛ ሀብትና በተፈጥሮ ጥቃትን ለመከላከል የሚያመች አቀማመጥ ያላቸውን ግብፅንና ሰሜን አፍሪካን ያዘ፤ በ301 ሊሲማኮስ ትሬስንና ትንሹን እስያ፣ ቈሳንደር ደግሞ መቄዶናን ያዘ:: በ277 በአንቲገነድስ (277 - 168) ሦስት የግሪክ ነገሥታት በግብፅ፣ በሶርያና በመቄዶንያ ያሉት ብቻ ሲጸኑ ይህ ሁኔታ ተቀየረ::

ዳን 11 «የደቡብ ንጉሥ» እና «የሰሜኑ ንጉሥ» በመካከላቸው ቅራኔ፣ ጦርነት ከዚያም አንድነት እንደሚኖር ይገልጻል:: በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የሚኖራቸው ጠላትነት የሚያ ይለው በአስጸያፊ ሥራቸው ምክንያት ስለ ተተዉ ነው፤ ይህም በራብዓዊ አንጥያኮስ ኤጲፋኔስ ዘመን (175 - 164) እንደ ሆነ ይገመታል:: በመቀጠል የመቃብያን ዐመፅ ሆነ፤ ይህም ለሐስሞኒያን ሥርወ መንግሥት መመሥረት ምክንያት ሆነ::

የድንበር መስመር 240 ዓ.ቅ.ክ. } በጥሊሞስ — — — — — / ሴሌውሲድ ..................



በሩ ድንጋዮችና በውድ ስጦታዎች ያከብ
ራል። 39 በባዕድ አምላክ ርዳታ ጽኑ ምሽጎ
ችን ይወጋል፤ ለእርሱ የሚገዙትን በእጅጉ
ያከብራቸዋል፤ በብዙ ሕዝብ ላይ ገዥዎች ያደ
ርጋቸዋል፤ ምድሩንም በዋጋ ያከፋፍላቸዋል።
40 "በመጨረሻው ዘመን የደቡብ ንጉሥ
ጦርነት ያውጅበታል፤ የሰሜን ንጉሥም
በፈረሰኞችና በሠረገሎች፣ በብዙ መርከቦ
ችም እንደ ማዕበል ይመጣበታል፤ ብዙ አገ
ሮችን ይወራል፤ እንደ ጐርፍም እየጠራ
ረገ በመካከላቸው ያልፋል። 41 መልካሚ
ቱንም ምድር ይወራል፤ ብዙ አገሮች በእጁ
ይወድቃሉ፤ ኤዶም፣ ሞዓብና የአሞን
መሪዎች ግን ከእጁ ያመልጣሉ። 42 ሥል
ጣኑን በብዙ አገሮች ላይ ያንሰራፋል፤ ግብ
ፅም አታመልጥም። 43 የወርቅና የብር ክምች
ትን፣ እንዲሁም የግብፅን ሀብት ሁሉ በቊ
ጥጥሩ ሥር ያደርጋል፤ የሊቢያና የኢት
ዮጵያ[ሠ] ሰዎችም ይገዙለታል። 44 ነገር ግን
ከምሥራቅና ከሰሜን የሚመጣ ወሬ
ያስደነግጠዋል፤ ብዙዎችንም ለማጥፋትና
ለመደምሰስ በታላቅ ቍጣ ይወጣል። 45 ንጉ
ሣዊ ድንኳኖቹን በባሕሮች መካከል[ረ] ውብ
በሆነው ቅዱስ ተራራ ላይ ይተክላል፤ ይሁን
እንጂ ወደ ፍጻሜው ይመጣል፤ ማንም አይ
ረዳውም።

**የመጨረሻ ዘመን**

12 "በዚያን ዘመን ስለ ሕዝብህ የሚቆ
መው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል።
መንግሥታት ከተመሠረቱበት ጊዜ ጀምሮ
እስከዚያ ዘመን ድረስ ታይቶ የማይታወቅ
ታላቅ የመከራ ጊዜ ይሆናል። ነገር ግን
በዚያን ጊዜ ስማቸው በመጽሐፉ ተጽፎ የተ
ገኘው ሕዝብህ ሁሉ ይድናሉ። 2 በም
ድር ዐፈር ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎች ይነ
ቃሉ፤ አንዳንዶቹ ለዘላለም ሕይወት፣
ሌሎቹም ለውርደትና ለዘላለም ጉስቍልና
ይነሣሉ። 3 ጥበበኞች[ሰ] እንደ ሰማይ ጸዳል፣
ብዙዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ
ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ። 4 ዳንኤል
ሆይ፤ አንተ ግን፣ እስከ ፍጻሜው ዘመን
ድረስ የመጽሐፉን ቃል ዝጋ፤ አትመውም።
ብዙዎች ወዲያ ወዲህ ይራወጣሉ፤ ዕውቀትም
ይበዛል።
5 እኔም ዳንኤል ተመለከትሁ፤ እነሆ ከፊት
ለፊቴ ሌሎች ሁለት ቆመው ነበር፤ አንዱ
ከወንዙ በዚህኛው ዳር፣ ሌላው ደግሞ ከወ
ንዙ በዚያኛው ዳር። 6 ከእነርሱም አንዱ፣
ከወንዙ ውሃ በላይ የነበረውንና በፍታ የለበ
ሰውን ሰው፣ "እነዚህ አስደናቂ ነገሮች ሊፈ
ጸሙ ምን ያህል ጊዜ ይቀራል?" አለው።
7 ከወንዙ ውሃ በላይ የነበረው በፍታ የለ
በሰው ሰው፣ ቀኝ እጁንና ግራ እጁን ወደ ሰማይ
አንሥቶ፣ "ለዘመን፣ ለዘመናት፣ ለዘመንም
እኩሌታ[ሸ] ይሆናል፤ የተቀደሰው ሕዝብ ኀይል
መሰበር ሲያከትም፣ እነዚህ ሁሉ ነገሮች
ይፈጸማሉ" ብሎ ለዘላለም በሚኖረው በእርሱ
ሲምል ሰማሁ።
8 እኔም ሰማሁ፤ ነገር ግን አላስተዋልሁ
ትም፤ ስለዚህ፣ "ጌታዬ ሆይ፤ የዚህ ሁሉ
ፍጻሜ ምንድነው?" ብዬ ጠየቅሁ።
9 እርሱም እንዲህ አለኝ፤ "ዳንኤል ሆይ፤
ቃሉ እስከ ፍጻሜው ዘመን ድረስ የተዘጋና
የታተመ ስለ ሆነ ሂድ፤ 10 ብዙዎች ይነጻሉ፤
ይጠራሉ፤ እንከን አልባም ይሆናሉ፤ ክፉዎች
ግን በክፋታቸው ይጸናሉ፤ ከክፉዎች አንዳ
ቸውም አያስተውሉም፤ ጠቢባን ግን ያስ
ተውላሉ።
11 "የዘወትሩ መሥዋዕት ከተቋረጠበትና
ጥፋት የሚያመጣው አስጸያፊ ርኵሰት
ከተተከለበት ጊዜ ጀምሮ አንድ ሺህ ሁለት
መቶ ዘጠና ቀን ይሆናል። 12 የሚታገሥና
እስከ አንድ ሺህ ሦስት መቶ ሠላሳ አም
ስት ቀን ፍጻሜ የሚደርስ የተባረከ ነው።
13 "አንተ ግን እስከ ፍጻሜው ድረስ ሂድ፤
ታርፋለህ፤ በቀኖቹ መጨረሻም ተነሥተህ
የተመደበልህን ርስት ትቀበላለህ።"

11፥40 ኢሳ5፥28፤ 8፥7፤21፥1፤ሕዝ38፥4
11፥41 ኢሳ11፥14፤ ኤር48፥47፤ሕዝ 20፥6፤ሚል3፥12
11፥43 2ዜና12፥ 3፤ ሕዝ 30፥4፤ናሆ3፥9
11፥45 ኢሳ2፥2-4፤ ዳን8፥9
12፥1 ዘፀ32፥32፤ መዝ56፥8፤ኤር17፥13፤ 30፥7፤ዳን9፥12፤10፥13፤ ማቴ24፥21፤ማር13፥ 19፤ሉቃ10፥20፤ይሁ 1፥9፤ራእ16፥18
12፥2 ኢሳ26፥19፤ ማቴ25፥46፤ዮሐ11፥24
12፥3 ምሳ4፥18፤ ኢሳ6፥7፤ዳን11፥33፤ ማቴ13፥43፤ዮሐ5፥35፤ 1ቆሮ15፥42፤ፊል2፥15
12፥4 ቍ9፡13፤ኢሳ 8፥16፤ኤር5፥1፤ራእ 22፥10
12፥5 ዳን10፥4
12፥6 ዳን8፥13፤ሕዝ 9፥2
12፥7 ዘፍ14፥22፤ ዳን6፥26፤7፥25፤8፥24፤ ሉቃ21፥24፤ራእ 10፥5-6፤7፤11፥2
12፥9 ቍ4፤ኢሳ 29፥11
12፥10 ኢሳ1፥25፤ 32፥7፤ዳን11፥35፤ ሆሴ14፥9፤ ራእ 22፥11
12፥11 ዘፀ29፥38፤ ዳን8፥11፤9፥27፤ ማቴ24፥15፤ማር13፥ 14፤ራእ11፥2
12፥12 ኢሳ30፥ 18፤ሕዝ4፥5-6፤ ዳን8፥14
12፥13 ቍ4፤መዝ 16፥5፤ኢሳ57፥2፤ ማቴ 10፥22፤ያዕ1፥12፤ራእ 14፥13

[ሠ] 43 ወይም የኑብያ ወይም የኩሽ [ረ] 45 ወይም በባሕርና ውብ.... መካከል [ሰ] 3 ወይም ጥበብን የሚገልጡ [ሸ] 7 ወይም ለዓመት፣ ለሁለት ዓመታት፣ ለዓመትም እኩሌታ

*11፥40-45፤* በክርስቶስ ተቃዋሚና በፖለቲካ ጠላቶቹ መካከል የሚነሣ ጦርነት ነው፤ "ውብ በሆነው ቅዱስ ተራራ" (ቍ 45) ላይ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ የሕይወቱ ፍጻሜ ይሆናል፤ ይህም ከአርማጌዶን ጦርነት (ራእ16፥13-16) ጋር የተያያዘ ነው።

12፥1 *ሚካኤል፤* የ10፥13 ማብ ይመ። *ታላቅ የመከራ ጊዜ፤* ኤር30፥7፤ ማቴ24፥21 እና ማብ ይመ። ከራእ16፥18 ጋር ያነጻ ጽሩ። *በመጽሐፉ፤* 10፥21 ይመ እንዲሁም መዝ9፥5፤ 51፥1፤ 69፥28 ማብ ይመ።

*12፥2፤* የጻድቃንና የኃጥአን ትንሣኤ መኖሩን በግልጽ የሚናገር የመጀመሪያው ክፍል ነው፤ ከዮሐ 5፥24-30 ጋር ያነጻጽሩ። *ለዘላለም ሕይወት፤* በብሉይ ኪዳን በዚህ ስፍራ ብቻ የሚገኝ ሐረግ ነው።

12፥5 *ሌሎች ሁለት፤* በሙሴ ሕግ ምስክርነት የሚሰጡ ሰዎች ብዛት የመጨረሻው አነስተኛ ቍጥር ሁለት ነበር (ቍ7፤ ዘዳ19፥15 ይመ)።

12፥7 *ለዘመን፣ ለዘመናት፣ ለዘመንም እኩሌታ፤* አማራጭ ትርጒሙን ይመ፤ ከ7፥25 ጋር ያነጻጽሩ።

*12፥11-12፤* በአንጥያኮስ ኤጲፋኔስ ዘመን የተፈጸመውን ስደት (8፥14፤11፥28 እና ማብ ይመ) ወይም የመጨረሻውን ዘመን ሊያመለክት ይችላል።

12፥13 *ታርፋለህ፤* ትሞታለህ ማለት ነው (ኢዮ3፥17 ይመ)።